# የሥነ - ጥበባት ትምህርት

# የተማሪው መጽሐፍ

# ስድስተኛ ክፍል

**አፋን ኦሮሞ አዘጋጆች** **አፋን ኦሮሞ ኤዲተሮች**

ከበቡሽ ላሜሳ ዳሜ ቶሊና

ላሚ ቤኛ ሉባባ ጃማል

ዳንዳአ ቦጋለ ታደሰ ድንቁ

**በአፋን ኦሮሞ ገምጋሚዎች**

ድርባ ማሞ

ደቀቦ ጉዬ

እስማኤል ሐሳን

**ተርጓሚዎች** **ኤዲተሮች**

እስማኤል ሐሳን ደቀቦ ጉዬ

ሳላማዊት ጣፋ ሙሉቀን አብራሐም

**ግራፊክስ**

ታደሰ ድንቁ

© የኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ፣ 2014/2021

ይህ መጽሐፍ በኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ እና በአሰላ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ትብብር በ2014/2021 ተዘጋጀ፡፡

የዚህ መጽሐፍ የባለቤትነት መብት በህግ የተጠበቀ ነው፡፡ ከኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ ፈቃድ ውጪ በሙሉም ሆነ በከፊል ማሳተምም ሆነ አባዝተው ማሰራጨት በህግ ያስጠይቃል፡፡

# መውጫ

ይዝት ገጽ

ምዕራፍ 1_የስነ ጥበባት ሥራ ባህሪያት.......................................1
1.1 የስነ-ጥበብ መሠረታዊ ንድፍ............................................2
1.2 የሜጀር እና ማይነር ቁልፍ..................................................9
1.3 ስነ-ትያትር እና ስነ-ፊልም............................................. 20
1.4 ስነ - ፊልም.......................................................................... 41
ምዕራፍ 2_የፈጠራ ችሎታ ................................................52
2.1 ቀለል ያሉ ዜማን ምት ክሌፎች ላይ መጻፍ.......................... 53
2.2 የቀለም ቅብ እና የህትመት ንድፍ...................................... 62
የትያትር እና የቪዲዮ የሀሳብ ገለጻ............................................ 68
ምዕራፍ 3_የባህል እና የታሪክ ተጨባጭ ሁኔታ ....................... 76
3.1 የባህል ትርክትን ወደ ትያትር በመቀየር ማሳየት ..................77
3.2. የባህል ሙዚቃ መስረያዎች............................................... 81
3. 3 ስነ-ስዕል በመጠቀም ተረትን አስመስሎ ማሳየት................. 85
ምዕራፍ 4_የስነ-ጥበብ መስህብ ..............................................91
4.1 የማህበረሰብን ብርቅዬ እውቀትን በትያትር ሙያ ማድነቅ...... 92
4.2. የማህበረሰቡን ሀገር በቀል እውቀት በስነ-ጥበብ ማድነቅ...... 100
4.3 ሀገር በቀል የማህበረሰብን እውቀትን በሙዚቃ ማድነቅ......... 108
ምዕራፍ 5_የስነ-ጥበባት ግንኙነት .......................................114
5.1. ስነ-ጥበባት የተፈጥሮ ሀብትን በመጠበቅ እናበመንከባከብ ውስጥ ያለው ጠቀሜታ ..............................................................118
5.2.1ስነ-ስዕል ከተለያዩ ነገሮች ጋር መተሳሰር ........................126

# ምዕራፍ 1

## የስነ ጥበባት ሥራ ባህሪያት

**የዚህ ምዕራፍ ትምህርት** ውጤት፡-
በዚህ ምዕራፍ መጨረሻ ላይ:

- የንድፍን ምንነት ትገነዘባላችሁ፡፡
- በስነ-ጥበብ እና በንድፍ አይነቶች መካከል ያለውን ትስስር በማየት ታደንቃላችሁ፡፡
- በንድፊ ሐሳብና በሌሎች ስነ-ጥበባት ውስጥ ያለውን ጥቅም ትለያላችሁ፡፡
- የሜጀርና የማይነር ቁልፎችን ለይታችሁ ታውቃላችሁ፡፡
- የድምጽ ከፍታና ዝቅታ (ፒች) እንዲሁም የቁልፍ ምልክት ምን እንደሆነ ለይታችሁ ታውቃላችሁ፡፡
- የትያትር ጥበብና የፊልም ጥበብ ትገልጻላችሁ፡፡
- የትያትር እስክሪፕት የአፃፃፍ ሂደትን ትማራላችሁ፡፡
- የትወና ምንነት ተረዳላችሁ፡፡

# መግቢያ

ንድፍ የስነ-ጥበብ ስራ መነሻ ነው፡፡ አንድ ሰው የስነ-ጥበብ ስራ ከመስራቱ በፊት ንድፈ ሀሳቡን ማጠናከር አለበት፡፡

ንድፈ ሀሳብ በአካባቢያችን በተፈጥሮ ሆነ ሰው ሠራሽ በምናገኛቸው ነገሮች ላይ፣ ትርጉም ባላቸው ወይም መልእክት ማስተላለፍ በሚችሉ መንገድ በወረቀትም ሆነ በሌላ ነገሮች ላይ ንድፈ ሀሳቡን ማስቀመጥና በሌላ መንገድ በሰው አዕምሮ ውስጥ ያላቸውን ሚና እና ጥቅም ተምራቸዋል፡፡ በዚህ ምዕራፍ ትምህርት ውስጥ ደግሞ የሜጀርና ማይነር ቁልፍ እንዲሁም የድምፅ ከፍታና ዝቅታ የቁልፍ ምልክት ትርጉም እና ጥቅማቸውን ትማራላችሁ፡፡ በተጨማሪ ለትያትር እስክሪፕት የሚያስፈልጉትን ክፍልፋዮች ተምራችኋል፡፡ ባለፈው ክፍል ውስጥ የተማርከውን ማስታወስ በዚህ ክፍል ውስጥ ለምትማረው ትምህርት መሠረት ይሆናል፡፡

በዚህ ርዕስ ይዘት ስር፡- የስነ-ጥበብ ምንነት፣ጨዋታ፣ዝግጅት፣ድርሰት አጻጻፍና የስነ- ትያትር የምትማሩበት ነው፡፡

## 1.1 የስነ-ጥበብ መሠረታዊ ንድፍ

ተማሪዎች ቢያንስ መጎናፀፍ የሚገባቸው የመማር ብቃት

ከዚህ ርዕስ ትምህርት በኋላ፡

- የንድፍ ምንነተ ትናገራላችሁ፡፡
- የንድፍ አይነቶችን ትዘረዝራላችሁ፡፡
- ንድፍን በመጠቀም ቀለል ያሉ ስራዎችን ትሠራላችሁ፡፡
- ንድፍ ከሌሎች ስነ-ጥበብ አይነቶች ጋር ያለውን ግንኙነት ታብራራላችሁ፡፡

### 1.1.1.ንድፍ

**ተግባር 1**

ሰዎች ስዕል በዕርሳስ ወይም በብዕር (እስክሪብቶ) ሲስሉ አይታችሁ ታውቃላችሁ? እነንተስ ሠርታችሁ ታውቃላችሁ? አይታችሁ ከሆነ እንዴት? እንዴትስ ይሠራል?

ንድፍ የስነ-ስዕል ስራ ከሚሰራበት ዘዴ ውስጥ አንዱ ሆኖ በመስመርና በቅርፅ ላይ ትኩረት በማድረግ የሚሰራ ነው፡፡ ንድፍ የሚባለው ቃል ከጣሊያን ቃል የተወሰደ ነው ትርጉሙም ቀለም አልባ ባህሪ ያለው ስራ ሆኖ በመስመር የሚሰራ ማለት ነው፡፡ ንድፍ ማለት በአካባቢያችን በተፈጥሮ ወይም በሰው ሰራሽ የሚገኝ ነገር ሆኖ ትርጉም ባለው መልክ በወረቀትና በሌሎች ነገር ላይ በስዕል የሚሳል ነው፡፡

ንድፍ ማለት በሰው አእምሮ ውስጥ ተፈጥሮ ወደ ተጨባጭነት የሚቀየር ሆኖ ጠጣር የሆኑ መሳሪያዎች እንደ እርሳስ፣ከሰል፣ጠመኔ፣እስክሪብቶ እና በመሳሰሉት በመጠቀም የሚሰራ ነው፡፡ ንድፍ ቁመትና ስፋት ብቻ ያለውና በአንድ አቅጣጫ ብቻ የሚታይ ነው፡፡ ስለዚህ ዝርግ ቦታ ስላለው ማንሳት አይቻልም፡፡

የስነ-ስዕል ንድፍ ተወዳጅና መሠረታዊ የሆኑ ሠዎች ሀሳባቸው ደስታ፣ ሀዘን፣ ምኞት፣ ስሜትን፣ ታሪኩን፣ ባህሎችንና የመሳሰሉትን የሚገልፅበት ነው፡፡ ንድፍ ታሪክን ይናግረናል፣ ያስገነዝበናል፣ ያነቃቃናል፣ ያዝናናል በቂ የሆነ መረጃ ይሰጠናል፡፡

የሰው ልጅ በዋሻ ውስጥ በሚኖርበት ጊዜ በዋሻው ግድግዳ ላይ፣ለጥ ባለ ድንጋይ ላይ በሹል ድንጋይና ከሰል በመጠቀም ሀሳቡን ይገልፁ ነበር፡፡ ንድፍ የሁሉም ስነ-ጥበብ አይነቶች መነሻ ነው፡፡ አንድ ሰው ንድፍን በደንብ የማይነድፍ ከሆነ የቀለም ቅብ፣የቅርፅ ህትመት በደንብ ለመስራት ይቸግራል፡፡ ስለዚህ ንድፍን በደንብ መንደፍ አስፈላጊ ነው፡፡

ይህ ማለት ለስዕል አይነቶች እንደ ቀለም ቅብ፣ግራፊክስ፣ኮላጅ፣ሞዛይክና ቅርጻ ቅርጽ የመሳሰሉትን ንድፍ መሰረታዊ ነው፡፡ ይህም አንድ ሰው አንድን ቃል/ዓረፍተ ነገር/ ለመጻፍ ያሉትን ፊደላት ማወቅ እንዳለበት ሁሉ አንድ የተቀናበረ የስነ-ጥበብ ስራ በቀለም ማስመር ወይም በቅርጻ ቅርጽ በመስራት ንድፍ መለማመድ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡

ንድፍ በሁለት ቦታ ይከፈላል እነርሱም፡

1. መለኪያ ያለውን መሳሪያ በመጠቀም የሚሠራ ንድፍ

መለኪያ ያለው መሣሪያ ማለት፤ በአንድ መስመር መለካት ማስመሪያን በመጠቀም ሲሆን፤ እንደዚሁም አንድ ክብን ነገር ለማክበብ ሌላ መሣሪያዎችን መጠቀም ይኖርብናል፡፡ ለምሳሌ፡- እንደ ካርታ ያሉ ሥዕሎችን ለማንሳት በእስኬዌር ዘዴ በመጠቀም የሚናነሳ ከሆነ ነው፡፡

2. መለኪያ የሌላውን መሳሪያ በመጠቀም የሚሠራ ንድፍ

መለኪያ የሌለውን መሳሪያ መጠቀም ማለት፤ ማስመሪያና የመሳሰሉትን ሳንጠቀም በእጃችን በእርሳስ፣እስክሪብቶ፣ከሰልና ሌሎች ነገሮችን ተጠቅመን ስንሰራ ማለት ነው፡፡ ንድፍ በሚሠራበት ሁኔታ ላይ ተመስረተዉ ልዩነት አለው፡፡ እየታየ የሚነደፍ ንድፍ ከሚናስመስለው ንድፍ ጋር በይበልጥ እንዲመሳሰል የተመረጠ ዘዴ ነው፡፡ እየታየ የሚነደፈው ስዕል በሁለት መንገድ ይሠራል፡፡ እነሱም፡-

ሀ. በፍጥነት የሚሠራ ንድፍና

ለ. ቀስ ተብሎ/በዝግታ/ የሚሠራ ንድፍ ነው፡፡

## ሀ. በፍጥነት የሚሠራ ንድፍ

የዚህ ንድፍ አይነት በብዛት የሚጠቅመው በፍጥነት እንቅስቃሴ ላይ ያሉትን ነገሮች፤ በቅፅበት በዓይን ለማየት መስመሮችን ብቻ በመጠቀም መንደፍ ነው፡፡ እንዲሁም በሰዎች ሀሳብ ውስጥ ያለውን ሀሳብ በፍጥነት ያንን ሀሳብ ሳይጠፋብን (ሳንረሳ) ሀሳባችንን ወረቀት ላይ ማስቀመጥ

ማለት ነዉ፡፡

ይህ ንድፍ በፍጥነት በተወሰኑ ደቂቃዎች ውስጥ የሚሠራ ነው፡፡ በዚህ ዓይነት ሁኔታ የሚሠራው ንድፍ እንደታሰበው በሙሉ የሚሠራ አይነት አይደለም፡፡



ስዕል 1.1. በፍጥነት የተሠራን ንድፍ የሚያሳይ ስዕል

## ለ. ቀስ ተብሎ በማጥናት የሚሠራ ንድፍ

የዚህ ንድፍ አይነት የሚንስለውን ስዕል በትክክል ለማስመሰል ይጠቅማል፡፡

ይህ ንድፍ በዝግታ እና በጥናት እንዲሁም፤ በትኩረት ረጅም ግዜ ወስዶ ስለሚሰራ ሙሉ መልዕክት እንዲያስተላልፍ ታስቦበት የሚሠራ ነው፡፡ የዚህ ስራ ሁኔታ  የሚያተኩረው የሚናስመስለው ነገር በሚመጥን መልኩ የመለስለስና የመሻከር ባህሪ መጠበቅ ብርሃንና ጥላ በደንብ በሚያሳይ መልክና ትክክለኛ እየተፈጠሩ ያሉ እንቅስቃሴ በውስጡ ይዞ መገኘት ላይ የሚያተኩር ነው፡፡



ስዕል 1.2፡ በዝግታ የተሠራ ንድፍ የሚያሳይ ስዕል

**ልምምድ 1**

ከዚህ በታች በታች የተሰጠውን በፍጥነት የተሠራ ንድፍ በማየት ደጋግማችሁ በእርሳስ ስሩና ለክፍላችሁ አቅርቡ፡፡ ካቀረባችሁ በኋላ ከሌሎች ተማሪዎችና መምህራን የሚሰጣችሁ የመሻሻያ ሃሳብ ለሚቀጥለው ሥራችሁ ይተቅማቸዋል፡፡



**ልምምድ** 2

ከዚህ በታች ያለውን በዝግታ የተሠራ የስዕል ንድፍ አይታችሁ በእርሳስ ንደፉና ለክፍላችሁ አቅርቡ፡፡ ከዚያ በኋላ ከሌሎች ተማሪዎችና ከመምህራችሁ በመሰጣችሁ ሃሳብ መሠረት ጥንካሬያችሁና ድክመታችሁን ገምግሙ፡፡



## 1.2 የሜጀር እና ማይነር ቁልፍ

**ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎናጸፉ የሚገባቸው የመማር ብቃት**

**ከዚህ ርዕስ ትምህርት በኋላ፡**

- የሜጀርና ማይነር ቁልፎችን ለይታችሁ ትናገራላችሁ::
- የሚጀርና ማይነር እስኬልን ትመሠርታላችሁ::
- በሜጀር፣ ማይነርና በእስኬል መካከል ያለውን ግንኙነት ትገልፃላችሁ::

**የግንዛቤ ጥያቄ 1**

- የማይነር ቁልፍ ምን አይነት ስሜት መፍጠር የሚችል ሙዚቃ ለመመስረት ይጠቅማል?
- ስለ ሜጀርና ማይነር እስኬል ምን የምታውቁት ነገር አለ?

የሜጀርና የማይነር የሙዚቃ ቁልፍ ለይቶ ማወቅ የሙዚቃ መሠረታዊ ችሎታ ነው፡፡ ሙዚቀኛ ወይም ሙዚቃ የሚያቀናብር ሰው ትክክለኛውን ሙዚቃ ለመፍጠር በሁለቱ ቁልፎች መካከል ያለውን ልዩነት ማወቅ አስፈላጊ ነው፡፡ እነዚህን ቁልፎች በሁለት ቀላል መንገዶችን በመጠቀም መለየት ይቻላል፡፡

እነርሱም፡- የመጀመሪያው ሙዚቃን በሚናዳምጥበት ጊዜ ደምፅ በሚፈጥርብን ስሜት ላይ በመመስረት መለየት ይቻላል፡፡ ይህ ማለት፤የሜጀር ቁልፍ የምንለው ሙዚቃን ሲንጫወት ከፍ ያለ ድምፅ የደስታን ስሜት፣ሰውን የሚያበረታታ ስሜት፣በሰው ውስጥ ሞራል የሚፈጥርና ሰውን የሚያነሳሱ ናቸው፡፡

የማይነር ቁልፍ የምንለው ደግሞ ሙዚቃ በሚንጫወትበት ጊዜ ዝቅተኛ ድምፅ የሚፈጠርበትን ቦታ የሚያሳይ ነው፡፡ ሁለተኛው የሜጀርና የማይነር ቁለፍ ከመጀመሪያ ኖታና እስኬል በመነሳት መለየት ይቻላል፡፡

እስኬል የሙዚቃ ፒች ስብስብ በቅደም ተከተል እየጨመረ ወይም እየቀነሰ መሄዱን ለመሳየት የሚፃፍበት ወይም የምንጨወትበት ነው፡፡ ይህም ማለት እስኬል የተቀናጀ የድምፅ ቅደም ተከተል ነው፡፡


ተግባር 2

1. እስኬል ምንድን ነው?
3. ሜጀር እስኬል እና ማይነር እስኬልን እንዴ መለየት ይቻላል?

እስኬል የተቀናበረ የድምጽ ቅደም ተከተል ነው፡፡ እሱም እንደየ ሀገሩ ባህል የተለያዩ አይነቶች አሉ፡፡ ለምሳሌ በምዕራብያዊያን ዘንድ የሚታወቀው ድያቶኒክ እስኬል ሰባት የተለያዩ ፒችዎች አለው፡፡እነርሱም ሙሉ እርምጃ እና ግማሽ እርምጃ አለው፡፡

ኦክታቭ ማለት ደግሞ በስምንተኛ ድምፅ ዕራሱን የሚመስል(የሚደግም) ማለት ነው፡፡ የፒያኖን ቁልፍ እንደምሳሌ ቢንወስድ በነጭና በጥቁር ቁልፍ መሀል ያለው ርቀት ግማሽ እርምጃ ሲሆን በሁለቱ ነጭ መሀል ያለው ርቀት ደግሞ ሙሉ እርምጃ ነው፡፡ ነገር ግን በ B እና C እንዲሁም፣ በ E እና F መሀል ያለው ርቀት ግማሽ ነው፡፡ እንደዛውም ተከታትለው ባለት ሁለት ጥቁር ቁልፎች መካከል ያለው ርቀት ሙሉ ዕርምጃ ነው፡፡

እነርሱም የሜጀር ቁልፍ ሲመሠረት 3ኛ እና 4ኛ እንዲሁም 7ኛ እና 8ኛ ድምፅ መካከል ሁሌም ግማሽ እርምጃ (semiitoon) ሲሆን፣ የቀሩት ሁሉ ሙሉ እርምጃ ናቸው፡፡ እነርሱም በቅደም ተከተል ሂደት ሙሉ--ሙሉ--ግማሽ ሙሉ--ሙሉ--ሙሉ--ግማሽ ይሆናል ማለት ነው፡፡ ከዚህ በታች በተሰጠው ፒያኖ ላይ ያሉ የቁልፍ አይነቶችን በማየት ለዩዋቸው፡፡





ስዕል. 3 የኪቦርድን ቁልፍ ድምፅ በቅደም ተከተል የሚያሳይ ስዕል፡፡

ለምሳሌ፡- ለሜጀር እስኬል A-B-C-D-E-F-G-A ይሆናል፡፡ እንደ ሜጀር እስኬል ማይነር እስኬልም፤በተወሰነ እርምጃ በቅደም ተከተል በመከታተል ማቀናጀት ነው፡፡ እሱም ሙሉ-ግማሽ-ሙሉ-ሙሉ-ግማሽ-ሙሉ ሙሉ ነው፡፡ ለምሳሌ፡- የ A ማይነር እስኬል a-b-c-d-e-f-g-a ይሆናል፡፡ የሙሉ እና የግማሽ ኖታ እርምጃ መጀመሪያ/መነሻ ላይ ለመመስረት በተለያየ መልኩ ቅደም ተከተልና ጊዜ ሜጀር እስኬልና ማይነር እስኬል ሙዚቃው በልዩ ስሜት ድምፅ ከፍና ለስለስ ባለ መልኩ እንዲፈጠር እንደ ሜጀር ቁልፍ እና ማይነር ቁልፍ እንዲለያዩ ያደርጋል፡፡


### 1.2.1. የሜጀር ቁልፍ

ከዚህ በታች የተሰጠውን የሜጀር ኪቦርድ እና የሙዚቃ እስታፍ የቁልፍ አመሰራረት በማነፃፀር አጥኑ፡፡




ስዕል 4 የኪቦርድ እና የሙዚቃ እስታፍ ግንኙነት የሚያሳይ ስዕል

ከዚህ በታች ያለውን የሙዚቃ እስታፍ ቁልፍ በመጠቀም የ$B^b$ እርምጃን አጥኑ፡፡




ስዕል 5 $B^b$ ሜጀር እስኬል የሚያሳይ የሙዚቃ እስታፍ

ከዚህ በላይ ያለውን የሙዚቃ እስታፍና የኪቦርድ ቁልፍ በመመልከት፤ ከዚህ በታች የተሠጡትን እርምጃዎች አጥኑ፡፡


1. C-D መካከል አንድ ሙሉ እርምጃ (G) አለ፡፡
2. D-E መካከል አንድ ሙሉ እርምጃ (G) አለ፡፡
3. E-F መካከል ግማሽ እርምጃ (W) አለ፡፡
4. F-G መካከል አንድ ሙሉ እርምጃ (G) አለ፡፡
5. G-A መካከል አንድ ሙሉ እርምጃ (G) አለ፡፡
6. A-B መካከል አንድ ሙሉ እርምጃ (G) አለ፡፡


7. B-C መካከል ግማሽ እርምጃ (W) አለ፡፡

ከዚህ በታች በተቀመጡት የሙዚቃ እስታፍ ላይ የተፃፉ የኖታ ምልክቶች የቁልፍ ስም መነሻ ቦታ ነው፡፡

<u>ለምሳሌ</u>

C ሜጀር ቁልፍ






D ሜጀር ቁልፍ


F ሜጀር ቁልፍ



B♭ ሜጀር ቁልፍ



G ሜጀር ቁልፍ



A ሜጀር ቁልፍ



ተግባር 3

1. ከዚህ በታች የተሠጡትን የሜጀር ቁልፍ ስምና ኖታዎች የሙዚቃ ሠሌዳ ኪቦርድን በመሳል ኖታቸውን አሳይ፡፡

1. DM ➡ D E F# G A B C# D
2. AM ➡ A B C# D E F# G# A
3. GM ➡ G A B C D E F# G

1.

2. ከዚህ በታች የተሠጡትን የሙዚቃ ድምጽ መነሻ በማድረግ በሙዚቃ ሠሌዳ ላይ ሜጀር እስኬል ኖታ በመመስረት አሳይ፡፡


$E^b$ ሜጀር

E ሜጀር


$A^b$ ሜጀር

### 1.2.2. የማይነር ቁልፍ

የማይነር እስኬል ቁልፍ ሙሉ በሙሉ ሜጀር እስኬል ላይ ተጠግቶ ይገኛል፡፡ የዚህ ቁልፍ አመሠራረት (በድምጽ ቅደም ተከተል ስናስቀምጠው) እንደ ሜጀር ቁልፍ በሙሉ እርምጃና በግማሽ እርምጃ ተጠቅመን የሚንመሠርተው ነው፡፡ የግማሽ እርምጃው ማይነር ድምፅ ቁልፍ 2-3 እና 5-6 መካከል ይገኛል፡፡




ስዕል 6 የ C ማይነር ቁልፍ $cde^bfga^bb^bc$ የሚያሳይ ስዕል፡፡




ስዕል 7 የ e ማይነር ቁልፍ ef#gabcde የሚያሳይ ስዕል፡፡


ከዚህ በታች የተሠጡትን የማይነር ቁልፍ በተደጋጋሚ በማጥናት፤ ለክፍል ጓደኞችህ/ሽ ግለፅ/ጪ፡፡

ማሳሰቢያ፡- ከዚህ በታች የተሠጡትን የሙዚቃ ሰሌዳ ላይ የተጻፉትን የኖታ ምልክት የማይነር ቁልፍ የመነሻ ቦታ ስም ነው፡፡


a ማይነር ቁልፍ




b ማይነር




d ማይነር ቁልፍ




g ማይነር ቁልፍ



e ማይነር ቁልፍ



f# ማይነር ቁልፍ



ተግባር 4

1. ከዚህ በታች የተሰጡትን የሙዚቃ ድምፆች መነሻ በማድረግ ማይነር እስኬልን መስርታችሁ አሳዩ፡፡

c ማይነር

c# ማይነር

f ማይነር

## 1.2.3.ፒች (የድምፅ መውጣትና መውረድ) እና የቁልፍ ምልክት

ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎናፀፉ የሚገባቸው የመማር ብቃት

ከዚህ ርዕስ ትምህርት ርዕስ በኋላ፡

- የድምጽ መውጣትና መውረድ፤ በሙዚቃ ውስጥ ያለውን ጥቅም ትናገራላችሁ፡፡
- የድምፅ ማውጣትና መውረድን ሊታችሁ ትሰማላችሁ፡፡


### ሀ. የድምፅ መውጣትና መውረድ

የግንዛቤ ጥያቄ 2

1. የድምፅ መውጣትና መውረድ ምንድነው? በሙዚቃ ውስጥ ያለው ሚና ምንድነው? የድምፅ መውጣትና መውረድ የሚባለው ድምጽ በኖታ ሲፈጠር ድምጻችን በማውጣት የሚናሳየው ነው፡፡ ይህን ስንል የድምፅ መውጣትና መውረድ የድምጽ እርግብግቢት አይነት መነሻ መሠረት በማድረግ ድምፅ መውጣት ወይም

መውረድ የሚገለይበት ነው:: ናቹራል የድምፅ መውጣትና መውረድ (ነጭ ቁልፍ) የፊደላት ስም ቅደም ተከተል A, B, C, D, E, F እና G የሚወክሉ ናቸው::

የድምፅ መውጣትና መውረድ የኖታዎች ስም ሻረፕ እና ፍላት (ጥቁር ቁልፍ) ደግሞ በአምስት ፊደላት የተሠየሙ ናቸው::እነርሱም በቅደም ተከተል ስናስቀምጣቸው C♯,D♯,F♯,G♯,A♯, እና $B^{b}$,$A^{b}$,$G^{b}$,$E^{b}$ እና $D^{b}$ ናቸው:: ይህንን ለመገንዘብ ከዚህ በታች የተሰጠውን ስዕል በተጨባጭ እንመልከት::




ስዕል 8 የፒያኖ (ኪቦርድ) ቁልፍ ስም::

### ለ. የቁልፍ ምልክት

**ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎናፅፉ የሚገባቸው የመማር ብቃት ከዚህ ትምህርት ርዕስ በኋላ፡**

- የቁልፍ ምልክት ትርጉምን ትገልጻላችሁ::
- የቁልፍ ምልክት ላይታችሁ ታሳያላችሁ::


የግንዛቤ ጥያቄ 3

1. ሙዚቃን በመስራት ውስጥ የቁልፍ ምልክት ምን ዓይነት ሚና አለው ?

የቁልፍ ምልክት አንድን ሙዚቃ የሚወስን ሆኖ እንዴት እንደሚቆጠር፣የትኛው ምት ትኩረት እንዲፈልግና ሙዚቃው የሚፈጥረው ስሜት እንዴት አይነት እንደሆነ የሚወሰን ነው፡፡ በተጨማሪ የቁልፍ ምልክት የትኛው የሙዚቃ ድምፅ በእስታፍ ላይ መስመር እና ባዶ ቦታ ላይ እንደሚገኝ የሚነግረን ሆኖ ያለው ኖታ ሻርፕ፣ ፍላት ወይም ናቹራል መሆኑን የሚንገልፅበት ነው፡፡


የሻርፕ ወይም የፊት ቁልፍ ምልክት ከክሌፍ ቀጥሎ መስመር ላይ ወይም ባዶ ቦታ ላይ ሲገኙ ሁሉም ኖታዎች መስመር ወይም ባዶ ቦታ ላይ የሚገኘው የሻርፕ ወይም የፍላት ኖታ ባዶ ይሆናል፡፡

ከዚህ በታች የተሰጠውን ምሳሌ ተመልከቱ፡፡



ከላይ ከተሰጠው የሙዚቃ እስታፍ መረዳት እንደሚቻለው ፍላት ሆነው የተቀመጡ የቁልፍ ምልክቶች ሁሉ በእስታፉ ላይ የተፃፉ ድምፆችን በሙሉ በግማሽ ድምፅ በማድረግ የኖታዎቹንም ስም ይቀይራሉ፡፡ ከዚህ ውስጥ F ሜጀርን ስንመለከት እንደሚከተለው ይሆናል፡፡






ከላይ በተሰጡት እስታፎች ላይ ሻርፕ ሆነው የተቀመጡ የቁልፍ ምልክቶች ሁሉ በእስታፉ ላይ የተፃፉ ድምፆችን በግማሽ ድምፅ በማሳደግ የኖታዎችንም ስም ይቀይራሉ፡፡ ለምሳሌ የሚከተለውን A ሜጀር ማየት ይቻላል፡፡




ከዚህ በላይ በተሰጠው ማብራሪያ ላይ መገንዘብ የሚቻለው የቁልፍ ምልክት ብቻ በማየት የእስኬሉን ምስረታ በቀላሉ ማወቅ ያስችለናል፡፡ ለምሳሌ ከዚህ በላይ 1ኛ ተራ ቁጥር ላይ ያለው G$^{M}$ ሆኖ F# መሆኑን ያሣየናል፡፡

## ተግባር 5

1. የቁልፍ ምልክት ማለት ምን ማለት እንደሆነ ለጓዳኞቻችሁ ንገሩ፡፡
2. ያሉትን የቁልፍ ምልክቶች ሁሉ ሠርታችሁ አሳዩ፡፡

## 1.3 ስነ-ትያትር እና ስነ-ፊልም

**ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎናጸፉ የሚገባቸው የመማር ብቃት**

በዚህ ምዕራፍ ትምህርት መጨረሻ፡

- የስነ-ትያትር እና ስነ-ፊልም ተመሳሳይነትና ልዩነት ትረዳላችሁ፡፡
- የትያትር ድርሰት እና የፊልም ድርሰትን ይፅፋሉ፡፡
- ትያትር ታዘጋጃላችሁ፡፡

ተግባር 5

2. ትያትር እና ድራማ ልዩነታቸው ምንድነው ብለህ ታስባለህ?

3. ጭውውት ማለት ምን ማለት ነው ?

### 1.4.1. ስነ-ትያትር

የትያትር አጥኚዎችና ሙሁራኖች በትያትር ትርጉም በተለያየ ሀሳብ ይገልፁታል፡፡ ገሚሶቹ ትያትር የጀመረው ከቅርብ አመታት ወዲህ ነው ይላሉ፡፡ ሌሎች ደግሞ ከሰው ልጅ መገኘት ጋር ያያይዙታል፡፡

የሰው ልጅ በዚህ ምድር ላይ ከተገኘ ጊዜ ጅምረዉ፤ የተለያዩ እንቅስቃሴዎች የሚያደርገው ትያትር እንደሚያሳይ የሚገመት ሲሆን፤ መሬት ደግሞ እንደ መድረክ ይወሰዳል፡፡ በዚህ ምድር ላይ የሚታየው የመድረክና የተዋንያን ውጤት ውስጥ የማይወጣ መሆኑን ያሳያል፡፡ ይህ ማለት ስነ- ትያትር የሰው ልጅ የሚያደርገው ትወና፣ተግባር፣ጥሩና መጥፎ ነገር፣ የኑሮ ውጣ ውረድ ፣ደስታና ሀዘን፣መምሸትና መንጋት፣የፈጠራ ችሎታና የኑሮ ዘይቤን ለማሻሻል የሚደረገው ጥረት፣የኑሮ ግጭት፣ድንገተኛ አደጋ፣በሞት መለየት፣ጋብቻ፣የሚዋደዱ ሰዎች በተለያዩ ምክንያት ሲለያዩ እና ሲገናኙ በአጠቃላይ ያለፈውን፣በውስጡ ያሉትን እና የወደፊቱን ትንበያ የሰው ልጅ የሚያደርገው ድርጊቶች ትያትር ነው፡፡

ይሁን እንጂ የትያትር መጀመሪያው የራሱን ሳይንስና እራሱን የቻለ ሆኖ፤ በመጀመሪያ ጊዜ የታወቀው በግሪክ ሀገር ውስጥ ነው፡፡ የትያትር ትርጉም መነሻ የግሪክ ቃል ሲሆን "Theatron" ከሚለው ቃል የመጣ ነው፡፡ 'Theatron' ማለት አንድን ነገር የሚናይበት ቦታ ወይም የምንመለከትበት ቦታ ነው፡፡ ትያትር በየእለት ኑሮአችን ውስጥ የሚናከናውነውን ተግባር የሚያሳይ ነው፡፡ በትያትር ውስጥ የሚታየው ተግባር ወይም እኛ የምናየው ተግባር ድራማ ይባላል፡፡

ድራማ በስራ ወይም በተግባር በማሳየት መስራት ማለት ነው፡፡ ድራማ የሚለው ከግሪክ ቃል 'dran' ከሚለው የመጣ ነው፡፡ ተርጉሞ መስራትና በተግባር ማሳየት ነው፡፡ ድራማ በተግባር ከማሳየት በፊት በድርሰት መልክ በጽሁፍ የሚዘጋጅ ሆኖ፤በመቀጠል የትያትር ባለሙያዎች በመድረክ ላይ ተመልካች ባለበት ቦታ እና አስፈላጊው ቁሳቁስ በተሞላበት ቦታ በቀጥታ ከመድረክ ላይ ለተመልካቾች ሲቀርብ ትያትር ሆነ ማለት ነው፡፡

ከዚህ ላይ የሚንገነዘበው የትያትር እና የድራማ ልዩነትን ነው፡፡ በመድረክ ላይ ትያትር ሲባል ድራማ ደግሞ በወረቀት ላይ ድራማ ይባላል፡፡ ስለዚህ ትያትር፣ድራማ፣ትወና፣የድራማ ሳይንስ በውስጡ ይዘዉ የሚዘጋጅ ወይም የስነ-ፅሁፍ እና ስነ-ጥበብ የትያትር ቴክኒክ አካላት በውስጡ የያዘ ነው፡፡



ስዕል .9 በመድረክ ላይ እየተላለፈ ያለውን ቲያትር የሚያሳይ ስዕል::

### 1.4.2.ተውኔት

ተውኔት ማለት የትያትር ጽሁፍ ሰዎች ገፀ-ባህርያት ተክተው የሚሰሩት ተግባር ነው፡፡ ተውኔት ከሰው ልጅ እድገት ታሪክ ጋር የጀመረ ነው፡፡ ተውኔት እንደ አሁኑ ዘመናዊ ከመሆኑ በፊት የሰው ልጅ ለመኖር በሚያደርገውን ጥረት ውስጥ የተለያዩ የሀይማኖት እንቅስቃሴ ሲያደርግ በዚህ ተግባር ውስጥ ያደገ ነው፡፡ የተውኔት መገኛ ሀገረ ግሪክ ናት፡፡ የሰው ልጅ ፈጣሪውን ለማመስገን፣የሀይማኖት ስርዐት ለመፈፀም ሲል በሚያደርገው እንቅስቃሴ ተውኔት ተወለዶ አደገ፡፡ ሆኖም በሮም ዘመነ መንግስት በጣም የሚናቅና የሚጠላ ቢሆንም፤እየኖረ እየተወደደና ተቀባይነት እያገኛ በመምጣቱ ለህዝብ እይታ መታየት ጀመረ፡፡

በዚህ ሁኔታ ተውኔት በህግና በደንብ መስራት በመጀመሩ አሁን ያለው ደረጃ መድረስ ችሎአል፡፡ በአሁኑ ዘመን ተውኔት እንደቀድሞ በሀይማኖትና በክብረ በዓላት ላይ የሚቀርብ ሳይሆን፤ በሙያና በብቃት ተደግፎ የሚሠራ ስራ ሆኗል፡፡ በስልጣኔ ዘመን ተውኔት የተዋናዩን ብቃትና ችሎታ የሚጠይቅ ሆኖ በተፈለገ ሠአት የሚታይ ነው፡፡ ይህም

በተለያዩ ጫወታዎች በመለማመድ የራስን ብቃት አክሎበት ማሳየት ነው፡፡ ከዚህ ሌላም የድራማ ስራ በጣም የሚያስደንቅ የስነ-ጥበብ ስራ ሆኖ ማየት በስራ ውስጥ የሚፈጠር ድንገታዊ ፈጠራ መስራትና ማሳየት ፣በድራማ እንቅስቃሴዎች፣ድምፅ፣ውዝዋዜ(ጭፈራ) በሙዚቃ ማሳየት ነው፡፡ አንድ ትያትር ተውኔት ዝግጅት በደንብ አምሮ ተውቦ ተመልካችን እንዲያዝና እንዲያስደስት ከሚያደርጉት አንዱ ዋነኛው የትያትር ዝግጅቱ ውስጥ ድርሻ የወሰዱ ተዋንያኖች ናቸው፡፡ አንድ ዝግጅት ውስጥ በወረቀት ላይ ያሉት ገጸ-ባህርያትን ነብስ ዘርቶበት ተመልካችን አልቅሰው የሚያስለቅሱ፣ተደስተው የሚያስደስቱ ዝግጅቱን በማቅረብ በተመልካች ፊት የሚታዩ ተዋንያኖች ስለሆኑ ድርሻ (ሚናቸው) የላቀ ነው፡፡ ስለዚህ ተዋንያኖች ከተውኔት ተለይተው መታየት የለባቸውም፡፡

## የስነ-ተውኔት ምንጭ

ተግባር 6

ተዋንያን የትዋኔን ስነ-ጥበብ ከየት ያገኛሉ ብለህ ታስባለህ ?

- የስነ-ተውኔት ችሎታ የሚገኘው በትውልድ (በተፈጥሮ) ሆኖ ተዋንያኖች ችሎታቸውን በትምህርት፣በስልጠና እና በልምድ ይበልጥ ማሻሻል እና ማሳደግ ይኖርባቿል፡፡
- ተዋንያኖች የስነ-ተውኔት ችሎታቸውን በማሳደግ ወደ ዝግጅት ስራ ሳይገቡ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የስነ ተውኔት ላይ ማተኮር አለባቸው፡
  - በትኩረት መመልከት
  - ትውስታ
  - ምናባዊ ችሎታ

- ድንገታዊ ፈጠራ
- ለይቶ ማየት (ማስተዋል)
- እንቅስቃሴ

ተዋንያንን ትልቅ ቦታ ለማድረስ እነዚህ የስነ-ተውኔት ችሎታዎች መሠረታዊ ስለሆኑ አንድ በአንድ እንመልከታቸው፡፡

በትኩረት መመልከት

ተዋንያኖች የተሰጣቸውን ገፀ-ባህሪያትን ምን እንደሚመስል ማወቅ፣በውስጣቸው ምንእንደሚያስቡ ስሜታቸውን፣ደስታ፣ሀዘን፣ቁጭት እና የመሳሰሉትን እንዴት መሆን እንዳለበት በትኩረት መመልከት አለባቸው፡፡ ለምሳሌ፡- ተዋንያኖች ተወክለው የሚጫወቱትን ገፀ-ባህሪ፡- ወጣት ነው ወይስ ሽማግሌ፣ጥሩ ስነ-ምግባር ያለው ወይስ አስቸጋሪ ሰው፣ ይህ ሰው ምን ይወዳል፣ምን ይጠላል፣ስነ-ልቦናው ምን ይፈልጋል? በማለት በትኩረት መከታተል (ማጥናት)፣እንዴት እንደሚያወራ፣እንዴት እንደሚራመድ፣የፊቱ ገፅታ (አገላለፁ) ሁሉ በትኩረትና በጥልቀት ማወቅ ወይም ማጥናት እንዲችሉ ያደርጋል፡፡ ስለዚህ ተዋንያኖች የተውኔት ችሎታቸውን በማዳበር በአካባቢያቸው ያለውን ሁኔታ በትኩረት ማስተዋል ይጠበቅባቸዋል፡፡

ተዋንያኖች ሁል ጊዜ የሰውን ቦታ ብቻ ሳይሆን፤ የእንሰሳትን ድርሻ ወክለው መጫወት ስላለ የሚያዩትን፣የሚሰሙትን ሁሉ ማስተዋል አለባቸው፡፡ ስለዚህ የምልከታ ትኩረት ተዋንያን ጋር ከፍተኛ ሚና አለው፡፡

## ትውስታ

ተዋንያኖች በስነ-ተውኔት ችሎታ ውስጥ ትልቁን ድርሻ ወይም ሚና ያለው ትውስታ ነው፡፡ የስነ-ተውኔት ችሎታ ውስጥ ተዋንያኖች ከቃለ-ተውኔት እና ተግባር ውጪ ተግባርን ማሳየት አስቸጋሪ ስለሆነ ይህን

ችግር ለመፍታት ለትውስታ ትልቅ ቦታ መስጠት አስፈላጊ ነው፡፡ ትውስታ ስንል፤ ተዋንያኖች የሚወክሉትን ገፀ-ባህሪ በአስፈላጊው ስሜት መጫወት ካልቻሉ የህይወት ልምዳቸውን በማስታወስ በተሠጣቸው ገፀ-ባህሪ ፀባይ ጋር በማነፃጸር ልዩ ስሜትን የመፍጠር አጋጣሚዎችን በመጠቀም መጫወት ነው፡፡

ገፀ-ባህሪያት በትያትር ፅሁፍ ውስጥ በአለም ላይ ያሉትን ሰዎች የሚወክሉ ስለሆነ ታሪካቸው ከተዋንያኖች ታሪክ ጋር መመሳሰል ይችላል፡፡ በመድረክ ላይ መሳቅና ማልቀስ ተዋንያኖችን ከሚያጋጥሙ ትልቅ ፈተናዎች አንዱ ነው፡፡ ስለዚህ ተዋንያኖች በተለያዩ የህይወት ልምድን በተግባር ውስጥ መጠቀም ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ፡- በትያትር ፅሁፍ ውስጥ የሚያለቅስ ገፀ-ባህሪ ድርሻ የወሰዱ ተዋንያኖች ማልቀስ ካልቻሉ በህይወታቸው ውስጥ እናታቸው ወይም የሚወዱት ሰው ሞቶ ከሆነ ያንን ክስተት በማስታወስ ማልቀስ አለባቸው፡፡ መሳቅም ካስፈለገ በህይወታቸው ያሳቃቸውን ክስተት በማስታወስ መሳቅ ይችላሉ፡፡

## ምናባዊ ችሎታ

የስነ ተውኔት ችሎታን ለማሳደግ ምናባዊ ችሎታ በጣም ጠቃሚ ነው፡፡ ምናባዊ ችሎታ ማለት በሰው አዕምሮ ውስጥ ሁኔታና ምስልን መፍጠር መቻል ነው፡፡ አንድ ተዋናይ አስመስሎና አ`መሳስሎ መድረክ ላይ የሚያቀርበውን ተግባር አሳምሮ ለመጫወት በሰውነቱ፣በእጁ፣በእግሩ፣በድምፁ፣በአይኑ፣በፊት ገጽታው ወይም በመላ አካሉ ስለሚጠቀምበት ሰውነቱ ተዘጋጅቶ፣ተነቃቅቶ፣ተቀላጥፎ መገኘት አለበት፡፡ ይህን ሁሉ ለማድረግ ምናባዊ ችሎታው በጣም ጠቃሚ ነው፡፡ ለሠውነት እንቅስቃሴው ስልጠና ከወሰደ በኋላ የሰውነት አካሉን አጠናክሮ የስነ-ተውኔት ችሎታውን ለማሳየት ሰውነት ትልቅ መሳሪያ ነው፡፡ ተዋኒያኖች መድረክ ላይ ጫወታቸውን ሳይጀምሪ በፊት

ተመልሰው በማስታወስ በአዕምሮአቸው ውስጥ ምናባዊ ችሎታን ማሳደግ አለባቸው፡፡ ተዋንያኖች ምናባዊ ችሎታቸውን ለማሳደግ፤

ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ነገሮች ማወቅ አለባቸው፡-

- አንድን ነገር በአዕምሮ ውስጥ መፍጠር፡፡
- ለእየአንዳንዱ ተግባር ትኩረት መስጠት፡፡
- የሚጠይቁት ጥያቄዎች በቅደም ተከተል ትኩረት መስጠት፡፡
- በአእምሮ ውስጥ ለሚፈጠር ነገር ሁሉ ምንነቱን እና ውስጡን በትኩረት ማጥናትና ማስተዋል፡፡
- ምናባዊ ችሎታን በተለያየ አቅጣጫ ማየት፡፡
- እራሱን የቻለ ገፀ-ባህሪ ከሌሎች ገፀ-ባህርያት በአዕምሮ ውስጥ መፍጠር፡፡
- ይህ ገፀ-ባህሪ ከሌሎች ገፀ-ባህሪያት ያለውን አንድነት እና ልዩነት ማወቅ፡፡

ታሪክን መፍጠር፣ተግባርን ማሳደግ፣በደንብ የሚጫወት ተዋንያን ለመሆን የተለያዩ ሀሳቦችን ማመንጨት አስፈላጊ መሆኑን ማወቅ አለባቸው፡፡ ምናባዊ ችሎታ የአዲስ ሀሳብ ምንጭና እድገት መሰረት ነው፡፡ እንዲሁ የተገኘውን ምናብ ማስታወስና በትኩረት የተገኘውን ሀሳብ ማሳደግ አለብን፡፡ አንድ ነገርን በምናብ ውስጥ ፈጥረን መስራት እንችላለን፡፡ ምናብን ማሳደግ በሚቻለው መጠን የፈጠራ ችሎታን ማሳደግ ይቻላል፡፡ ይህም የሚሆነው በአእምሮ ውስጥ በተፈጠረው ምስል መሰረት የተፈለገውን ነገር አስቀድሞ ማየት አስፈላጊ መሆኑን ተዋኒያኖች ማወቅ አለባቸው፡፡

ስለዚህ ተዋንያኖች ምናባቸውን በማሳደግ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መሠረታዊ ነገሮች ማወቅ አለባቸው፡

- አንድን ትእይንት በአእምሮ መግለፅ (መቅረፅ)፡፡
- በአንድ ትእይንት ውስጥ ያሉትን ገፀ-ባህሪያት በትኩረት

መመልከት፡፡

- አስፈላጊ የሆኑትን ጥያቄዎች በስፋት ማንሳት፡፡
- እያንዳንዱን ትዕይንት በትኩረት መመልከት፡፡
- የአንዱን ትእይንት ከሌላው ያለውን አንድነት እና ልዩነት ለይቶ ማወቅ፡፡

## ድንገታዊ ፈጠራ

ድንገታዊ ፈጠራ ማለት የተዋኒያኖች የመድረክ ላይ ተግባር ሆኖ ሳይዘጋጅበት በሆነ ክስተት መሰረት አድርጎ የሚሠራ የትወና ችሎታ ነው፡፡ ድንገታዊ ፈጠራ የተማሪ ተዋንያኖችም ሆነ በልምምድ የሚሰሩ ተዋንያኖች የስነ-ተውኔት ችሎታቸውን ለማሳደግ ይረዳል፡፡ ስለዚህ ተዋንያኖች ወደ ትወና ትምህርት ሲገቡ አስቀድሞ የድንገት ፈጠራዎችን ከልምምድ ውጪ በማሰራት ቀስ በቀስ ችሎታቸውን እንዲያሳድጉ ያደርጋል፡፡ ከዚህ ሌላ የተውኔት ተማሪ የተውኔት ትምህርት ሲጀምር የነበረውን ፍርሃት ለማስለቀቅ ይጠቅመዋል፡፡ አንድ አዘጋጅም የተዋንያኖችን ችሎታና ፍላጎት በቀላሉ ማወቅና የቃለ-ተውኔት አቀባበል የድምጽ አወጣጥና የመሳሰሉትን በደንብ ማወቅ ይጠበቅበታል፡፡

ተዋንያኖች የቃለ-ተውኔት አቀባበል ሁኔታን ስለድራማ በሚሰሩ ጊዜ ሊያውቁ ይችላሉ፡፡ ሆኖም በመጀመሪያ ድንገታዊ ፈጠራን በመጫወት ችሎታቸውን ማሳደግ ይኖርባቸዋል፡፡ በአንድ ድራማ ወስጥ የቃል ተውኔት አቀባበል ትልቅ ሚና አለው፡፡ የስነ ተውኔት ችሎታን ለማሳደግ የግድ ከድራማ መጀመር አስፈላጊ አይሆንም፡፡ እንዲሁም ከተወሳሰበ ገጸ-ባህሪ ከማስጀመር ይልቅ ቀስ በቀስ ከድንገታዊ ፈጠራ ጀምሮ ተማሪን ማሳደግ አስፈላጊ ነው፡፡

## ለይቶ ማየት (መስተዋል)

ማስተዋል ማለት አንድ የሚሰራ ነገር በቅደም ተከተል ገፀ-ባህሪያት ምን እንደሚሠሩ፣ የት እንደሚሰሩ፣ዝግጅቱን ለማን እነደሚያቀርቡ አስተውለው ማወቅ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ይህም በሀሳብም ሆነ በግልፅ በቀላሉ እንዲያውቁ ይረዳቸዋል፡፡ ተዋኒያኖች የተውኔት ጹሁፍ በማንበብ ብቻ ያውቃሉ ብሎ ማሰብ አይቻልም፡፡ ስለዚህ በጥልቀት አስተውለው ካወቁ በኋላ በተግባር ማሳየት አለባቸው፡፡ ተዋንያኖች ቀደም ብለዉ ስራቸውን ሳይጀምሩ የአካል እንቅስቃሴ በማድረግ የለይቶ ማየትን ችሎታ ስለሚያሳደግ የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ማድረግ አለባቸው፡፡ የአካል እንቅስቃሴ በቀላሉ የለይቶ ማየትን ችሎታ በአእምሮአቸው ውስጥ ማዳበር ይችላሉ፡፡

ተዋኒያኖች የተውኔት ፅሁፍ እንደሚል አብሮ ከሚሠራው ገጸ-ባህሪ ማን እንደሆነ፤ስራው እንዴት መድረክ ላይ እንደሚቀርብ እና የመሳሰሉትን በሀሳብ ከአስተዋሉ በኋላ በተውኔት ፅሁፍ ህግ መሰረት ለተመልካች አስደሳች ስራ ያቀርባሉ፡፡ ይህም የአእምሮ እና የአካል ስራ መሆንን ማስተዋል ይጠበቅባቸዋል፡፡ ተዋኒያኖች መድረክ ላይ የሚያቀርቡትን ስራ በፊት ገጻቸው ለማሳየት ማስተዋል ትልቅ መሣሪያ ነው፡፡ ብዙ ተዋንያኖች የተሰጣቸውን ገጸ-ባህሪ ምንነቱን በደንብ ሳያውቁ፣ሳያስተውሉ መድረክ ላይ ወጥተው ደረጃው የወደቀ ስራ ስለሚያቀርቡ ይህ ደግሞ ተመልካቾች ከተዋኒያኖች እምነት እንዲያጡና ስራውን እንዲንቁ ሊያደርጋቸው ይችላል፡፡ ስለዚህ ይህ ሁሉ እንዳይፈጠር ማስተዋል ትልቅ ሙያ ነው፡፡

## የአካል እንቅስቃሴ

የአካል እንቅስቃሴ ሲንል፤ የተዋኒያንን የአካል ብቃታቸውን የሚያጠናክር፣ሰውነታቸውን እንደተፈለገ ለማዘዝ የሚረዳቸው ማለት

ነው፡፡ የአካል እንቅስቃሴ አንድ ተዋንያን ገጸ-ባህሪን ወክሎ ሲጫወት በአካል፣በንግግር፣በስሜት ሁሉም ነገር አስመስሎ ለመጫወት አካሉ እንደሚፈልገው መታዘዝ አለበት፡፡ ይህ ካልሆነ ግን የተወከለውን ገጸ-ባህሪ ሆኖ መጫወት ይከብደዋል፡፡ ይህ ስለሆነ ተዋንያኖች የአካል እንቅስቃሴ የመስራት ግዳጅ አለባቸው፡፡ ስለዚህ ተዋንያኖች ስራቸውን ከመጀመራቸው በፊት መስራት ያለባቸው ነገር የአካል እንቅስቃሴ ነው፡፡ አንድ ተዋንያን የሚያምር አካል፤የሚያምር ድምፅ፣ጎበዝ ተዋንያን ለመሆን የድምፅ ልምምድ ማድረግ አለበት፡፡በመድረክ ላይ የተዋንያን አካል ሲጨማደድ ተዋንያኑ ይጨነቃል፡፡ ተወክሎ የሚሰራውን ገጸ-ባህሪ ሊረሳ ይችላል፡፡ ማለትም፡- ስለእግሩ፣እጅ፣ጀርባው እና ድምፅ እያሰበ ይጨናነቃል፡፡

የአካል እንቅስቃሴ ሲያደርጉ በሰውነታቸው ውስጥ ደግሞ በቀላሉ እንዲዘዋወር ያደርጋል፡፡

በአጠቃላይ የአካል እንቅስቃሴ ለተዋኒያኖች፡

- ድምጽን ለማጥራት፡፡
- ጡንቻዎችን ለማፍታት፡፡
- በደስታ እንዲጫወቱ ያደርጋል፡፡
- የደም ዝውውራቸውን ያቀላጥፋል፡፡
- ሠውነታቸው በተፈለገው መልኩ እንዲታዘዝ ያደርጋል፡፡
- ጭንቀትን ያስወግዳል፡፡
- ስሜታቸውን በሠውነታቸው እንዲገልጹ ያደርጋል፡፡
- በጨዋታ ውስጥ የሰውነታቸውን አቅም እንዲጠብቁ ያደርጋል፡፡
- አእምሮን፣ፊትን፣እጅን፣አይን፣እግር፣ሳንባ፣ድምፅ፣ጀርባ፣አንገት፣እራስ፣ምላስ እና ወዘተ በትክክል እንዲጠቀሙ ያደርጋል፡፡

## የድምፅ ልምምድ

በአንድ ተውኔት ውስጥ ስለ ድምፅ ስናወራ የተዋኒያኖች ድምጽ፣ሙዚቃ ድምፅና የተለያዩ የእቃዎች ድምፅ በተውኔት ውስጥ የሚሰሙ ናቸው፡፡ የተዋኒያኖችን ድምጽ፤ በሁለት መንገድ ማየት እንችላለን፡፡

የመጀመሪያው ተዋኒያኖች የተለያየ ድምጽ ለማውጣት እንዲችሉ የሚደረግ የድምጽ ልምምድ ነው፡፡

የድምጽ ልምምድ እንደ አካል እንቅስቃሴ ከትያትሩ ዝግጅት በፊት የሚደረግ ልምምድ ነው፡፡ የተዋኒያን ድምጽ ጥርት ብለዉ እንዲሰማ ቃላታቸው በጥራት እንዲሰሙ እና ድምጻቸው ጥራት እንዲኖረው ይረዳቸዋል፡፡ ሁለተኛው ደግሞ የአንዱ ተዋንያን ድምጽ በሌላው ላይ ያለው ተጽዕኖ ነው፡፡ ይህ ማለት ከአንድ ተዋንያን የሚወጣ ድምጽ፤ ሁኔታ እና መጠን በሌላው ተዋንያን ላይ ተፅእኖ ፈጥሮ መልስ እንዲሰጠው መንገድ ይከፍታል፡፡ ስለዚህ የድምጽ አጠቃቀማችን የተዋንያኖችን ስሜት ለመቀየር ትልቅ ሚና ስላለው ተዋንያኖች ከስነ-ተውኔት ችሎታ ማዳበር ይችላሉ፡፡ በቀላል መንገድ ደግሞ በተውኔት ውስጥ እራሱን የቻለ ድምጽ ትልቅ አገልግሎት አለው፡፡ በዚህ ውስጥ ድምጽ ህይወት ያለውና የሌለው ተብለዉ በሁለት ይከፈላል፡፡

ህይወት ያለው የሚባለው አንድ ትርኢት መድረክ ላይ ሲሠራ የሚሰሙ የእርምጃ ድምጾች፣የተለያየ የበር መንኳኳት ድምፅ፣የበር መከፈት እና መዝጋት ድምፅ፣የስልክ ጥሪ እና ወዘተ…ናቸው፡፡ ህይወት የሌለው የሚባሉት በመድረክ ላይ የማይታዩ ድምጻቸው ብቻ የሚሰማ ማለት ነው፡፡ ለምሳሌ የአይሮፕላን ድምጽ፣የመኪና ድምጽ፣የባቡር ድምፅ እና የመሳሰሉት ሁሉ በተግባር ውስጥ ትልቅ አገልግሎት ስለሚሰጥ እድገቱ፣ጥራቱ፣አቅጣጫ እና በሚወስድ ጊዜ ሁሉ ታውቆ መጠበቅ አለበት፡፡

በተግባር ውስጥ ድምጽ ትልቅ ቦታ ስላለው ተዋንየን ይህንን አውቆ አስፈላጊ የሆነውን ድምፅ ተለማምደው ሁል ጊዜ መስራት አለባቸው፡፡

የተውኔት አይነቶች

የተውኔት አይነቶች ሁለት ናቸዉ፡፡

እነርሱም፡

ሀ. ጥልቅ ተውኔት እና

ለ. ጥልቀት የሌለው ተውኔት ናቸው

## ሀ. ጥልቀት ያለው ተውኔት

ጥልቀት ያለው ተውኔት ስንል ስነ-ልቦናዊ አስተሳሰብ፣ስሜት፣የዕውቀት ባህር፣አእምሮ እና የመሳሰሉትን አውጥቶ የሚያወርድበት፣ የሚገመግምበት፣የውስጣዊ ገጸ-ባህሪ ስሜት ላይ ተመስርተው መጫወት ነው፡፡ የዚህ ተውኔት አይነት ከፍተኛ እና ጥልቅ የሆነ ስሜት ያስፈልገዋል፡፡ ይህ ማለት የገጸ-ባህሪውን ስሜት በደንብ ማወቅና ስሜታዊ ሆኖ ለተመልካች ማሳየት መቻል ነው፡፡ ይህ የትወና ዘዴ አንድ ተዋንያን የተሠጠውን የገጸ-ባህሪ ቦታ እራሱን አስቀምጦ እኔ ቢሆን፤ ምን እናገራለሁ፣ስሜቴ እምዴት መሆን አለበት ብለዉ ከአስተዋለ በኋላ በተግባር ማሳየት ነው፡፡ይህ የትወና ዘዴ ከውስጥ ወደ ውጭ ተብለዉ ይታወቃል፡፡

## ለ. ጥልቀት የሌለው ተውኔት

ጥልቀት የሌላው ተውኔት ሲንል፤ ደግሞ ስሜትን ለማሳየት ድምፅን እና አካልን መጠቀም ነው፡፡ ይህ የትወና ዘዴ ከውጪ ወደ ውስጥ ተብለዉ ይታወቃል፡፡ ይህ ማለት ተዋኒያኖች በቅዲሚያ ምን ማውራት እና መስራት እንዳለባቸው እንደሚያተኩሩ ይታመናል፡፡ ስሜት ደግሞ ከአነጋገር እና ከተግባር በኋላ የመጣል፡፡

### 1.4.3.የተውኔት ፅሁፍን መጻፍ

በዚህ ርዕስ ውስጥ የተውኔት ፅሁፍ ምንነት፣የተውኔት ጽሁፍ አጻጻፍ ዘዴ፣የተውኔት ጽሁፍ አላባዊያን፣ጀማሪ የተውኔት ፀሀፊን የሚያጋጥሙ ችግሮችን በመግለጽ መሠረታዊ ትምህርት ይሠጣል፡፡

ተግባር 7

1. የተውኔት ፅሁፍ ማለት ምን ማለት ነው?
2. የተውኔት ፅሁፍ አፃፃፍ ዘዴዎችን ዘርዝር ?

የተውኔት ፅሁፍ የስነ-ፅሁፍ ቅርንጫፍ ሆኖ በመድረክ የሚዘጋጅ ፅሁፍ ነው፡፡ የተውኔት ፅሁፍ በተግባር ለማሳየት የሚሆን ቃለ ተውኔት የያዘ ሲሆን፤ ተዋኒያኖች እየተነጋገሩ በአካል እንቅስቃሴ እያዋሃዱ ያቀርባሉ፡፡

የትያትር ተውኔት ፅሁፍ ደግሞ ታሪኩ ለመድረክ እንዲመች ተደርጎ የሚዘጋጅ ነው፡፡ ይህ ፅሁፍ የፀሀፊው የፈጠራ ውጤት ነው፡፡ ይህን ፅሁፍ የሚያዘጋጅ የድራማ ፀሃፊ ይባላል፡፡ የተውኔት ፅሁፍ ተዋንያኖች የሚነጋገሩትን ቃለ ተውኔት፣ግለ-ተውኔት፣የእንቅስቃሴ ገለጻ፣ገጸ-ባህሪያት ሁኔታ የመድረክ ላይ የሚታየውን ወዘተ… በውስጡ የያዘ ነው፡፡

የተውኔት ፅሁፍ መዋቅር

በተለያየ መልኩ የተውኔት ፅሁፍ ውስጥ ያለው ታሪክ በገብረ እና ትዕይንት ተብለዉ ይመደባል፡፡ አንድ ገብር ውስጥ ብዙ ትእይንቶች ይገኛሉ፡፡ አንድ የተውኔት ፅሁፍ ገብር አልቆ ወደ ሌላ ገብር ለማለፍ ይዘቱ ቦታውን እና ድርጊቱ ሙሉ በሙሉ መቀየር አለበት፡፡ ግን ትእይንትን ለመቀየር ከዚህ በላይ ከተዘረዘሩት ወስጥ አንድ ብቻ መቀየር በቂ ነው፡፡ አንድ የተውኔት ጽሁፍ ከአንድ ቦታ ተነስቶ የሚያርፍበት ቦታ ገብረ የሚገልጽ ሲሆን፤ ይህ ገብር ውስጥም የሃሳብ መቀያየር፣የጊዜ እና የቦታ መቀያየር እና ተመልካችን የሚያሳርፉበት

ቦታ ነው፡፡ በእረፍት ጊዜ መጋረጃ ተዘግቶ መድረክ ላይ መቀየር ያለበትን ነገር ቀይሮ በመድረክ የሚደረግ ነው፡፡ በረጅም የትያትር ፅሁፍ ውስጥ ገብር ቢያንስ ሁለት ቢበዛ ከሦስት ማለፍ የለበትም፡፡ ትእይንት ውስጥ በአጭር ጊዜ ትናንሽ መቀያየር ይታያል፡፡ ከዚህም ሌላ በገጸ- ባህሪያት ሲገቡና ሲወጡ የሚታይ መቀያየር ትዕይንት የባላል፡፡

የተውኔት ጽሁፍ አይነቶች

ሁለት አይነት የተውኔት ፅሁፎች አሉ እነርሱም፡-

የአንድ ገብር የተውኔት ጽሁፍ እና ረዥም የተውኔት ፅሁፍ ናቸው፡፡

የተውኔት ፅሁፍ አጻጻፍ ዘዴዎች ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት ዘዴዎች የተውኔት ጽሁፍ ለመጻፍ የሚረዱን ናቸው፡፡

## ዋና ሀሳብ

ዋና ሀሳብ ማለት ስለምንጽፈው ጉዳይ ማለት ነው፡፡ የሚንጽፍበት ዋና ጉዳይን ለማግኘት ማህበረሰቡ ውስጥ ገብቶ ጥናት ማድረግ ነው፡፡

- ማህበረሰቡ ውስጥ ገብቶ ሀሳብን ማስፋፋት፡፡
- ማህበረሰቡ ውስጥ ገብቶ መጫወት (ማህበረሰቡ ውስጥ ያለው ጨዋታ ውስጥ መሳተፍ)፡፡
- ማህበረሰቡ ውስጥ ገብቶ የአካባቢውን ሁኔታ ማየት፡፡
- ማህበረሰቡ ውስጥ ገብቶ ከሠዎች ጋር ቃለ ምልልስ ማድረግ፡፡

❖ ከስነ-ተውኔት ጸሀፊ ላይ ምን ይጠበቃል ?

አንድ በማህበረሰብ ውስጥ የሚኖር የተውኔት ጸሀፊ እንደ ህዝብም ሆነ እንደ ግለሰብ ታሪኩን በጥልቀት ማወቅ አለበት፡፡ ፀሀፊው በህይወቱ ውስጥ በሚያጋጥመው ገጠመኝ ተነስቶ ይጻፋል፡፡ በሰው ልጅ ህይወት ውስጥም፤- ድስታ፣ሀዘን፣ብልጽግናውን፣ጥላቻ፣ፍቅሩን፣ጉዳቱን፣ጭቆና የመሳሰሉት በሰው ልጅ ላይ ይታያሉ፡፡ ፀሀፊውም የሠው ልጅ አካል

ስለሆነ፣ በማህበረሰብ ላይ የሚደርሰውን አስተውሎ በግልጽ ማሳየት አለበት፡፡ ከዚህም ሌላ የሚኖርበትን ማህበረሰብ ፍልስፍናን በግልጽ በማውጣት ችሎታውን በመጠቀም ያለውን እውነት ለማህበረሰቡ ማቅረብ ይጠበቅበታል፡፡

ከዚህ ሌላ የሚኖርበትን የማህበረሰብ ፍልስፍና በግልጽ

አውጥቶ፣በችሎታው ተጠቅሞ ያለውን እውነት አሳምሮ በሚገርም ጥበብ ወደ ህብረተሰቡ ማቅረብ ይጠበቅበታል፡፡ የጸሀፊው ስራ ሁሌም መቼም ቢሆን ከሚኖርበት ማህበረሰብ ውጪ መውጣት የለበትም፡፡ አንድ ፀሀፊ ማዘጋጀት (መጻፍ) ከፈለገ በቅድሚያ ቤተ መጽሀፍት ውስጥ ያሉትን መፅሀፍ ማንበብ ይኖርበታል፡፡ የተለያዩ መጽሀፍቶችን ከአነበበ የተለያየ እውቀት (መረጃ) ያገኛል፡፡ ከዚህም ሌላ በሚፅፈው መጽሀፍ ላይ፣ የተለያዩ ጸሐፍያንን ማስገምገምና ሀሳብ ለመስጠት ጽሁፉን ማሻሻል ይኖርበታል፡፡

❖ አንድ ጸሀፊ ሙያውን ለማሻሻል የሚጠበቅበት፡

- ከባለ ሙያዎች ሀሳብ መውሰድ፡፡
- የተለያዩ የተውኔት ፅሁፎችን ማንበብ፡፡
- ተስፋ ሳያቋርጥ ደጋግሞ መጻፍ፡፡
- የሚኖርበትን ማህበረሰብ በጥልቀት ማወቅ፡፡
- የተለያዩ ትያትሮችን በመመልከት ገጸ ባህሪያትን ማናገር፡፡
- ከሌላው ስራ ጋር የራሱን ስራ ማነጻጸር እና መገምገም፡፡
- ምናባዊ ችሎታውን ማሳደግ፡፡
- የፈጠራቸውን ገፀ-ባህርያት ማንነታቸውን፣ቋንቋውን በጥልቀት ማወቅ ፡፡
- ባህሉን፣እምነቱን ፣የመሳሰሉትን፣ የሚወዱትን እና የሚጠሉትን ማወቅ አለበት፡፡ የገጸ ባህሪውን አመለካከት እና ስሜት ማንጸባረቅ እንጂ የራሱን ከማንጸባረቅ መቆጠብ አለበት፡፡

- በማስታወሻ ላይ የእለት ከእለት የህይወት ገጠመኙን የመፃፍ ችሎታውን ማዳበር አለበት፡፡

የተውኔት ጽሁፍ አይነቶች

በአሁኑ ሰአት የድራማ አይነቶች በዝተዋል፡፡ ይሁን እንጂ በአሁኑ ሠአት በመድረክ ላይ የሚታወቁ እና የሚታዩት አራት ስም አላቸው፡፡ እነሱም፡-

- ትሬጀዲ
- ኮመዲ
- ቀልድ
- ልብ አንጠልጣይ

እንዲሁም ሁለት ተጨምሮበታል፡-

- ትራጀዲ-ኮመዲ
- እውነተኛ ታሪክ

ትራጀዲ /አሳዛኝ ታረክ ያለው ትያትር

የትራቴጂ ትያትር በድሮ ጊዜ፣ ከክርስቶስ ልደት በፊት እንደተጀመረ ይታወቃል፡፡ ትራጀዲ የሚያሳዝን ታሪክ ላይ የሚያተኩር ሆኖ ከጨለማ ውጭ አንድም የብርሃን እና የሚያስደስት ሀሳብ አይኖርበትም፡፡ የሚያሳዝን ታሪክ ያለው ድራማ ትራጀዲ ይባላል፡፡ ትራጀዲ ውስጥ ዋና ገፀ-ባህሪ በራሱ በመጣው ስህተት ችግር ውስጥ ይገባና ተሰናክሎ ይወድቃል፡፡ ከዛ ተመልካችም ችግሩን በሀሳብ ተጋርቶ አብሮ ይጨነቃል፡፡

ኮሜዲ /አስቂኝ/

ኮሜዲ በረመልካች ዘንድ ጨለማን ሳይሆን ብርሃን፣ሳቅ፣ደስታ እና ሐሴትን ፈጥሮ በዛው ልክ ትምህርትን የሚያስተላልፍ ነው፡፡ ገጸ-ባህሪም እንደ ትራቴጂ በራሱ ባመጣው ችግር የሚወድቅ ሳይሆን፣ በሰላም መንገድ ላይ እየተራመደ ሲወድቅ ሳይሆን ሲነሳ

ይታያል፡፡ ስለሆነ ጼሁፍም ይህን አገናዝቦ መፃፍ አለበት፡፡

**ቀልድ**

ቀልድ ከስሙ እነደሚገለፅ ቀልድ የሚበዛበት የተውኔት ፅሁፍ ወይም ተግባር ነው፡፡ በዚህ ተውኔት ውስጥ ሴራ እና ክርክር ቢኖርም የተውኔት አጻጻፍ ሲጠብቅና ጠንከር ያለ ትምህርት ሲያስተላልፍ አይታይም፡፡ ጎልቶ የሚታይ ነገር ቢኖር ሳቅ እና ጫወታ እና ደስታን ፈጥሮ ተመልካችን ማዝናናት እና ማስደሰት ብቻ ነው፡፡ ገፀ-ባህሪው የሚገባበት እና ተመልካችም የሚጋራው ችግር ፈጽሞ አይኖርም፡፡ ልብ አንጠልጣይ /Melo drama/ ሜሎ ድራማ ይህ ድራማ እንደ ትራቴጂ ሆኖ ቅድሚያ በጨለማ የተሞላ ገጸ-ባህሪ ችግር እና ውጥረት ውስጥ ሲገባ ይታያል፡፡ በኋላ ላይ ግን በማያሳምን መልኩ በድንቅ ሁኔታ ከገባበት ችግር ሲወጣ ይታያል፡፡ ይህ እንዴት ሆነ ለምን ሆነ ለሚለው ጥያቄ መልስ ለመስጠት አይቸገርም፡፡ በትራቴጂ እና ኮሜዲ ውስጥ ግን መልስ ይሰጣል፡፡ በልብ አንጠልጣይ ውስጥ ለሴራ እና ክርክር እንዲሁም ለሚሰጠው ታሪክ መጨነቅ የለም፡፡

## የተውኔት ጽሁፍ መጻፍ

የተውኔት ጽሁፍ አጻጻፍ እራሱን የቻለ ህግና ደንብ እንዳለው ሁሉ በመጻፍ ሂደት ውስጥ የሚጠቅሙ የስርዓተ ነጥቦችም ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ ምክንያቱም አንድ የተውኔት ፅሁፍን የሚፅፍ ጸሀፊ የገፀ-ባህሪያትን ሀሳብ ሲገልጽ ስርዓተ ነጥቦችን ተጠቅመው ስሜታቸውን እና ታሪኩን ሙሉ አድርጎ ያቀርባል፡፡ ስለዚህ ስርዓተ ነጥብ የተውኔት ድርሰት አጻጻፍ ውስጥ ተገቢውን ጥንቃቄ የሚያሹ ህጎች እና ጸሀፊውን ሊስብበት የሚገባው ጉዳይ ነው፡፡

ከዚህ በታች ያለውን ምሳሌ እዩት፡፡

ቦታው የኔ ጋሻ ቃንቄሬ ቤት ነው፡፡ ጊዜው ጠዋት ሆኖ በበጋ ወቅት ተማሪዎች አምረውና ተውበው ወደ ትምህርት ቤት የሚሄዱበት ጊዜ ነው፡፡

**ተሊሌ**፡ (በ አይኗ ፊት ለፊቷን እያየች) ወይኔ ይሄ ልብስ እንዴት ያምራል?

**ቶላ** ፡ (ይስቃል) የሚገርም ነው! አሁን ጊዜው ልብስን አይቶ የሚያደንቁበት ጊዜ ነው?

ከዚህ በላይ የተሰጠው ምሳሌ የተውኔት ጽሁፍ አጻጻፍ ውስጥ ስርዓተ ነጥባት እንዴት እንደሚጠቀም ያስተምራል፡፡

ከዚህ በታች ያለውን ምሳሌም ተገንዘብ፡፡

**ሌንሳ**፡ እንዴት ነህ? ሰላም ነህ? (በመንገድ ዳር የሚቆሙ አንድ ሰውዬን እያየች)

**ጋዲሳ**፡ እኔን ነው? እኔን እያናገርሽኝ ነው? (አይኗ ውስጥ አትኩሮ እያየ)

**ሌንሳ** ፡ አዎ!

**ጋዲሳ** ፡ (ይስቃል) እኔ ምንም አይደለሁም፡፡ ምንም፡፡

**ሌንሳ** ፡ ለምን እንደዛ አልክ?

**ገዲሳ** ፡ ምክንያቱም እውነት ነው፡፡

**ሌንሳ** ፡ (ከትንሽ ጊዜ ዝምታ በኋላ) የምርህን ነው? ልታምነው አትችልም ?

**ጋዲሳ** ፡ እናቴን እና አባቴን ጠይቂው፡፡

**ሌንሳ** ፡ ምን እያልክ ነው ?

**ጋዲሳ** ፡ እነሱ ይጠሉኛል፡፡ ሊያዩኝ ራሱ አይፈልጉም፡፡

**ሌንሳ**፡ (ለትንሽ ጊዜ ዝም ብላ) እድሜህ ስንት ነው?

**ጋዲሳ** ፡ አስራ አምስት ብዬ አስባለሁ እሱ ችግር አይኖረውም፡፡

**ሌንሳ** ፡ አንተ እንደምታስበው አስራ አምስት ነው?

**ጋዲሳ**፡ አዎ!

**ሌንሳ** ፡ ሊገባኝ አልቻለም፡፡

**ጋዲሳ** ፡ ያ ጠንካራ ቤተሰቤ እድሜዬን አልነገረኝም፡፡

**ሌንሳ**፡ ትምህርት ቤት አልሄድክም?

**ጋዲሳ**፡ ለአንድ ጊዜ ሄጃለሁ::

**ሌንሳ**፡ የት ነው የሚትኖረው?

**ጋዲሳ**፡ እኔ ከማንም ሰው ጋር አልኖርም::

**ሌንሳ**፡ ምን ማለት ነው?

**ጋዲሳ**፡ ቤት የለኝም:: በመንገድ ላይ ነው የምኖረው::

የምግብ፣የሽንት እና የመጸዳጃ ቦታዬም እዚሁ መንገድ ላይ ነው፡፡

**ሌንሳ**፡ ስምህ ማነው?

**ጋዲሳ** ፡ ጋዲሳ ነው፡፡

**ሌንሳ** ፡ ሕይወትህን ለመቀየር ምን እያደረግህ ነው?

**ጋዲሳ** ፡ (ይስቃል) ትቀልጅብኛለሽ? እንዴ?

**ሌንሳ**፡ እየቀለድኩ አይደለም፡፡ እኔ ሌንሳ እባላለሁ፡፡ መንገድ ላይ የምኖሩ ሕጻናት መርጃ ድርጅት ውስጥ ሊቀ-መንበር ነኝ፡፡ ልረዳህና ልመክርህ ፈልጌ ነው፡፡

ከዚህ ምሳሌ ማወቅ የሚቻለው ቃለ-ተውኔት ከተውኔት ጽሑፍ አጻጻፍ ዘዴ አንዱ መሆኑ ነው፡፡ በተለይም በሚንኖርበት ማህበረሰብ ውስጥ ቃለ-ምልልስ ማድረግ አሪፍ የተውኔት ጽሁፍ ለመጻፍ የሚረዳን አሪፍ ዘዴ ነው፡፡

ስለዚህ የቃለ ተውኔት ጥቅም በተውኔት አጻጻፍ ውስጥ ፡

- ተዋንያንን ይለያል፡፡
- ሴራን ያጠነዝዛል

- ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡

የተውኔት ፅሁፍ አጻጻፍ ዘዴዎችን ለማወቅም ወሳኝ ነው፡፡ አንድ ተውኔት ሲጻፍ የተውኔት አላባዊያንም ጨምሮ የአጻጻፍ ዘዴም እራሱን የቻለ አለው፡፡ ተፅፎ የቃለ ተውኔት ከሽፋኑ ጀምሮ እስከ መጨረሻው ገፅ ላይ የጸሀፊው ስምና አድራሻ ነው የሚጻፈው፡፡

በሁለተኛ ገፅ ላይ የተወኔቱ ርዕስ ይጻፋል፡፡ በሌላኛው ገጽ ላይ ደግሞ የተዋንያኖች ገጸ-ባህርያት ግንኙነት የሴራ አይነት (በቅደም ተከተል) መቼት፣የተውኔቱ አይነት፣ የተውኔቱ ቅርፅ እና ወዘተ. በተውኔት ፅሁፍ ህግ መሰረት ከሽፋን ገፁ ጀምሮ ይጻፋል፡፡

በሶስተኛው ገጽ ላይ ደግሞ የተውኔት ገብር እና ትዕይንት ተፅፎ ተውኔት ጽሁፍ መጻፍ ይቀጥላል፡፡

### 1.4.4. የትያትር ዝግጅት

የትያትር ዝግጅት ሲንል፤ አንድ የትያትር ስራ ተዘጋጅቶ በሚጠበቀው ብቃት ተቀናብሮ በመድረክ ላይ ለተመልካቾች የሚቀርብበት ሂደት ማለት ነው፡፡ ይህም ሥራ የሚዘጋጀው በትያትሩ አዘጋጅ አማካኝነት ነው፡፡

በአንድ ትያትር ዝግጅት ውስጥ አዘጋጁ የትያትርን እውቀት ያለው የመድረክ ባለሙያ እና የተውኔት ድርሰት ባለሙያን አማክሮ ተዋንያኖችን የሚያሰራቸው ነው፡፡ አንድ ጸሀፊ የፈጠራ ችሎታውን ተጠቅሞ የጻፈውን ነገር አዘጋጅ ደሞ ሀሳቡን መሠረት አድርጎ የራሱን ፈጠራ ጨምሮበት አሳምሮ ተመልካችን እንዲያዝናና አድርጎ ያቀርባል፡፡

አዘጋጅነት ከትያትር ሙያ ስራዎች አንዱ ሆኖ በዋነኛው የአዘጋጅ ድረሻ የሆነ ስራ ነው፡፡ አዘጋጅ የትያትር ሙያ ሊኖረው የሚገባ

እና ተውኔት ጽሁፍን በማንበብ የመድረክ ላይ ዝግጅት ሁኔታን አስቀድሞ ማወቅ ያለበት ሰው ነው፡፡ አዘጋጅነት ውስጥም የአዘጋጅ ድርሻ የተውኔትን ጽሁፍ ማንበብ እና ለመገምገም ተዋናዮችን የሚያዘጋጅ ነው፡፡ የትያትር አዘጋጅ ሀላፊነት ተዋንያኖችን ማሰልጠን፣ የሚያስፈልጉትን ቁሰሶችን መለየት፣ የመድረክ አጠቃቀም ማስታወሻን መስራት፣በተውኔት ጽሁፍ ውስጥ ያለውን ተግባር ማሳመር ነው፡፡

መሻሻል እየመጣ በሄደ ቁጥር የትያትር ዝግጅትም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሸሻለ መጥቶ ከሃይማኖታዊ ይዘት ወደ ጥበብ ተሻግሮአል፡፡

ድሮ በአንድ ሰው ተፅፎ ተዘጋጅቶ እየቀረበ የነበረ በአሁኑ ጊዜ ይህ ሁኔታ ተቀይሮ በዘመናዊነት በትያትር ባለሙያዎች ተቀናብሮ ተዘጋጅቶ እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ ስለዚህ አንድ ፃሐፍ እውቀትና ልምዱን ተጠቅሞ በአእምሮ ውስጥ አሰላስሎ ጨምቆ የጻፈውን አዘጋጁ ደግሞ የጸሃፊውን ሀሳብ መነሻ በማድረግ የራሱን ፈጠራ ጨምሮበት የድምጽ ባለሙያ፣የመብራት ባለሙያ፣የሜካፕ ባለሙያ፣የመድረክ ባለሙያ፣የአለባበስ ባለሙያ እና የመሳሰሉትን ተዋኒያን በመቀናጀት የባለሞያዎችን ሀሳብ ከራሱ ሀሳብ ጋር በማቀናጀት ለተመልካቾች ይቀርባል፡፡

የትያትር አዘጋጅ ሥራ በዘመናዊ ትያትር ውስጥ ከፍተኛ ቦታ አለው፡፡ ይሁን እንጂ የዘመናዊ ትያትር አዘጋጅ መድረክን አሳምሮ እንደ አንድ ሙያ ዘመናዊነቱን ተላብሰዉ የታወቀው በ20ኛው ክፍለ ዘመን ውስጥ ነው፡፡

አዘጋጁ የራሱን ችሎታ ተጠቅመዉ የሚያየውን ነገር ምናባዊነት እና የራሱን ልምድ ጨምሮበት የራሱን የስልጣኔ ችሎታ ተጠቅሞ ጸሀፊው የተጠቀመውን የተለያዩ ዘዴዎችን በመገምገም የራሱንም የፈጠራ ሀሳብ በመጨመር ለተመልካቾች በመድረክ ላይ

እንዲቀርብ ያደርጋል፡፡ ይህንንም ለስራ ፍላጎት እና ግዴታ አለው፡፡ በመጀመሪያ ተውኔት ጽሁፍ በእጁ ከገባ ቀን ጀምሮ የጥበብ ስራን አስደናቂ የሚያደርግ ነገችን በመጨመር ማዘጋጀት አለበት፡፡

አዘጋጅ ከጸሃፊ ቀጥሎ ስሙ በቀጥታ የሚጠራ ነው፡፡ በትያትር ዝግጅት ውስጥ አዘጋጅ ምን ያዘጋጃል ለሚለው ጥያቄ አዘጋጅ የሚሰራው ስራ አንድ ብቻ ሳይሆን፤ የተለያዩ ስልቶችን እንደ ቃለ-ተውኔት፣እንቅስቃሴ፣ተግባር፣ድምጽ፣መብራት፣መድረክ፣ገጸ-ባህሪ እና የመሳሰሉትን ሁሉ የትያትር ስነ ምግባር በሚይዘው ሁኔታ ይሰራል፡፡ ይህንን ለማድረግ ከአዘጋጅ የሚጠበቀው ነገር፡

- የትያትር ጽሁፍ፡፡
- የመረጥከውን ትያትር ጽሁፍ ገምግሞ መረዳት፡፡
- ተውኔት መምረጥ፡፡
- የትያትር ፅሁፍን ማንበብ፡፡
- ትያትር ፅሁፍ ላይ ከተዋኒያን ጋር መመካከር፡፡
- ልምምድ መጀመር፡፡

ገጽ ባህርያትን ማዘጋጀት ሲሆን፤ ይህ ማለት ደግሞ በገጸ-ባህሪ ተግባር ውስጥ የሚገባውን ቃለ ተውኔት የሙዚቃ መድረክ፣የድምጽ ውጤት፣የመብራት አለባበስ፣ቅብ፣የመድረክ ቅንብር የሚሆኑ ነገሮችን እና የመሳሰሉትን ሁሉ ከተዋንያን እና ባለሙያዎች አቀናጅቶ ማዘጋጀት ነው፡፡

## 1.4 ስነ - ፊልም


ተግባር 8

1. የስነ- ፊልም እና የስነ - ተያትር ልዩነት ምንድን ነው?
2. ስነ-ፊልምን ለመስራት የሚያገለግሉን መሳሪያዎች ምን ምን ናቸው

ፊልምም ልክ እንደ ትያትር በምልከታ የምናየውና በእስክሪን ላይ ከሚታየው ጋር ትስስርነት አለው፡፡ እስክሪን በካሜራ ተቀድቶ የሚታይ ነው፡፡ ካሜራ ምስልን የሚያነሳ፣የሚያሳይ እና አንድን ዝግጅት በቀጥታ ስርጭት ለማስተላለፍ የሚረዳ ነው፡፡ ይህም ምስል ምስልን በድምጽ ወይም በቪዲዮ እና በፎቶ ነው፡፡ ስሙም የተወሰደው ከላቲን ቋንቋ 'dark chamber' ከሚለዉ ቃል ሲሆን፤ ትርጉሙም የፎቶ ማንሻ ማሳያ ማለት ነው፡፡ በአሁኑ ሠአት የካሜራ ቴክኖሎጂ አለምን ፊት ለፊት እንድትታይ ከአደረጉት አንዱ ነው፡፡ አንድን ተጨባጭ ድረጊት በርቀት ሳይገድብ ለማየት፣ልምድ ለመለዋወጥ እና መልእክት ለማስተላለፍ እንዲሁም፤ እንደ አንድ የትምህርት ደረጃ እያገለገለ ነው፡፡


ፊልም ከመጀመሪያው ጀምሮ እስከ አሁን በቴክኖሎጂ እድገት እየተሻሻለ በመምጣቱ ዛሬ ላይ ታዋቂ እና ለተለያዩ ጉዳዮች የምንጠቀምበት ሆኗል፡፡ ይህም ውጤት ከትንሽ ፈጠራ ሂደት ጀምሮ የመጣ ነው፡፡

በ 1834 ዓ.ም. ዊሊያም ሆርነር የሚባል ሰውዬ መዞር የሚችል እንደ ከበሮ አይነት ሆኖ 'zoetrope' የሚባለውን ማሽን ፈጠረ፡፡ ይህ ማሽን ሲዞር የሚታየው ምስል የፈረስ ግልቢያ ምስል ሲሆን፤ ከበሮ ሲዞር እንቅስቃሴ ያሳያል፡፡ ይህም እንቅስቃሴ የፈረስ ፎቶ ከበሮ ውስጥ በመለጠፍ በእሽክርክሪት በማሽከርከር የሚፈጠር ነው፡፡



ሥዕል 10 የፈረስ መስል በተለጠፈበት የከበሮ ምስል የሚያሳይ ስእል ፡፡

ኢ.ድዋርድ ሞይብሪ የሚባል በትውልድ ብሪትሽ የሆነ በዜግነት ደግሞ አሜሪካዊ የሆነ በ1872-1877 ዓ.ም. አስራ ሁለት የፈረስ ስዕል በአንድ ካሜራ አንስተዉ፤ አራቱን የፈረስ እግር አንድ ላይ መሬት እንዲነኩ በማሳየት ፊልምን የፈለሰፈ ነው፡፡ በፊልም አጀማመር ታሪክ ውስጥ ስሙ በአንጋፋነት የሚነሳ ነው፡፡



ስእል 11፡የኢድ ዋርድ ሙብሪጅ ፈረሶች ስእልና ምስል የሚያሳይ ስእል፡፡

በአጠቀላይ ፊልም ሊፈጠር የቻለው መነሻው ካሜራ መሆኑ ነው፡፡ ስነ-ፊልም ትያትር ትኩረቱ መድረክ ላይ እንደሆነ ስም ደግሞ ትኩረቱ ካሜራ ላይ ነው፡፡

አንድ ፊልም ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ትልቅ ጉልበት ይፈልጋል፡፡ የሚሰራበትን መሳሪያ ሳይቀር የሰው ጉልበት ይፈልጋል፡፡ ይህ ማለት በፊልም ውስጥ ያሉ የተሳታፊዎች እንደ ተዋኒያን፣ባለሙያዎች ፊልሙ ተሰርቶ ያልቃል፡፡ በተለይም ፊልም የሚሰራባቸው እቃዎች ወሳኝ ናቸው፡፡ እነኚህ መሳሪያዎች እንደ ካሜራ፣የቪዲዮ መብራቶች፣ድምጽ መቅጃ፣ኮምፒውተር እና የካሜራ መሸከሚያ፣የድምጽ መቅጃ መሸከሚያ እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡





ስዕል 12 የፊልም ስራን ለመስራት የሚያገለግሉ መሳሪያዎች መህል ጥቂቶችን የሚያሳይ ስዕል

## የምዕራፍ ማጠቃለያ

- ንድፍ ማለት በአካባቢያችን በተፈጥሮ ወይም በሰው ሰራሽ የምናገኘውን ነገር ትርጉም ባለው መልኩ በወረቀት እና በሌሎች ነገሮች ላይ በስዕል መስራት ማለት ነው፡፡
- ንድፍ በመስመር እና በቅርፅ ላይ በማተኮር የሚሰራ ነው፡፡
- ንድፍ የሚለው ቃል ከጣሊያን የመጣ ነው፡፡
- ንድፍ የሁሉም ስነ-ስዕል ስራ መነሻ ነው፡፡
- አንድ ሰው ንድፍ በደንብ መንደፍ የማይችል ከሆነ የቀለም ቅብ፣ቅርጻ ቅርጽ እና ትክክለኛ የሆነ የህትመት ስራ መስራት አይችልም፡፡
- የነድፍ አይነቶች በሁለት ይከፈላሉ፡፡
- የሙዚቃ ሜጀር እና ማይነር ቁልፍ ለይተው ማወቅ መሰረታዊ የሙዚቃ ችሎታ ነው፡፡
- አንድ ሙዚቀኛ ትክክለኛ የሆነ ሙዚቃን ለመስራት በሁለት ቁልፍ መሀል ያለውን ልዩነት ለመለየት አስፈላጊ ነው፡፡
- ፒች ደጋግሞ የሚፈጠረውን የድምጽ ሞገድ ላይ በመመርኮዝ ከፍና ዝቅ ብለው ለማዜም የሚያገለግል ነው፡፡
- አንድ እስኬል ቀጥሎ ባለው ኦክታቭ ሳይመለስ የተለያዩ ሰባት ፒቾች አለው፡፡
- በሁለት ጥቁር ቁልፎች መካከል ያለው እርምጃ ሙሉ ነው፡፡
- የማይነር እስኬል ሙሉ በሙሉ የሚጀር እስኬል ላይ ተለጥፎ ይገኛል፡፡
- የሻርፓ እና የፍላት ኖታዎች ፒች ስሚሰየመው በአምስት ፊደሎች ነው፡፡

$C^{\#}$, $D^{\#}$, $E^{\#}$, $G^{\#}$, $A^{\#}$ fi $B^{b}$ $A^{h}$ $G^{h}$ $E^{b}$ $D^{b}$ ናቸው፡፡




- ትያትር የምንኖርበትንና በየእለቱ የምንሰራቸውን ድርጊቶች የምንገልጽበት ነው፡፡
- የትያትር ስያሜ ከግሪክ ቃል 'Theatron' ከሚለው የተወሰደ ነው፡፡
- ተውኔት የድራማ ታሪክ ጽሁፍ በቃለ ተውኔት መልክ በጽሁፍ ተዘጋጅተው ተዋኒያን ለተመልካቾች የሚያቀርቡት ነዉ፡፡
- ትያትር በመድረክ ላይ በተግባር የሚታይ ሲሆን፤ፊልም ደግሞ ተሰርቶ ከአለቀ በኋላ በእስክሪን የሚታይ ነው፡፡
- የአንድ አዘጋጅ ሃላፊነት ተዋንያንን ማለማመድ ነው፡፡

የተውኔት ጽሁፍ ከመጽሀፍ በፊት የሚጻፍለትን ሀሳብ እና ተውኔት አይነቶችን ማወቅ አስፈላጊ ነው፡፡

## የምዕራፍ አንድ መልመጃ

I . ከዚህ በታች ያሉት አረፍተ ነገሮች ትክክል ከሆኑ 'እውነት' ስህተት ከሆኑ ደግሞ 'ሀሰት' በማለት መልሱ፡፡

1. ንድፍ የስነ-ስዕል ስራ የሚሰራበት ዘዴ ነው፡፡
2. ንድፍ በብዛት መስመር እና ቀለም ላይ በማተኮር የሚሰራ ነው፡፡
3. ንድፍ ማለት ቀለም አዘል ባህሪ ሆኖ በመስመር የሚሰራ ነው፡፡
4. ንድፍ ማለት በሰው አእምሮ ውስጥ የተፈጠረ ሀሳብ ወደ ተግባር የሚቀርብበት መንገድ ነው፡፡
5. ንድፍ በሁለት መንገድ ይሰራል፡፡
6. ለስነ-ስዕል ስራ አይነቶች ንድፍ መነሻ አይደለም፡፡
7. ድራማ፣ስነ-ፊልምና ስነ-ትያትር ልዩነት የላቸውም፡፡

8. ፊልም በቀጥታ በመድረክ ላይ ለተመልካች ይቀርባል፡፡
9. በትያትር ውስጥ የቃል ተውኔት ጥቅም ተዋንያንን መለየት ብቻ ነው፡፡
10. በስነ ትያትር ውስጥ ከአዘጋጅ ድርሻዎች ውስጥ አንዱ የአዘጋጅ ማስታወሻ መስራት ነው፡፡
11. ድራማ የሚለው ከግሪክ ቃል 'dran' ከሚለው የተወሰደ ነው፡፡

II. ከዚህ በታች ያሉትን ጥያቄዎች በማንበብ ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ፊደል በመምረጥ በፅሁፍ መልሱ፡፡

1. ከዚህ በታች ከተሰጡት ምርጫዎች ውስጥ ንድፍን የማይገልጽ የቱ ነው

   ሀ. ስሜት ለ. ሀዘን ሐ. ባህሪ መ. መልሱ አልተሰጠም

2. ንድፍ የሚሰጠው ጥቅም ያልሆነ የቱ ነው

   ሀ. ታሪክን ይነግረናል ሐ. መረጃ ያስተላልፍልናል

   ለ. አያዝናናንም መ. ያስተምራል

3. የሰው ልጅ ለመጀመሪያ ጊዜ ንድፍን የነደፈው በምን ላይ ነው

   ሀ. ዋሻ ለ. ወረቀት ሐ. የስዕል ሰሌዳ

   መ. ሁሉም መልስ ናቸው

4. ንድፍን በደንብ መንደፍ የማይችል ሰው ከዚህ በታች ካሉት ነገሮች ውስጥ መስራት የማይችለው የቱ ነው

   ሀ. ቅርጻ ቅርጽ ለ. ቀለም ቅብ

   ሐ. ህትመት መ. ሁሉም መልስ ናቸው

5. ንድፍ ለመንደፍ የማይጠቅመው የቱ ነው

   ሀ. እርሳስ ለ. ጠመኔ ሐ. ከሰል

   መ. መልሱ አልተሰጠም

6. 'G' ሜጀር እስኬል ስንት ሻርፕ (#) አለው?


   ሀ. 4 ለ. 3 ሐ. 2 መ. 1

7. አንድን ድምጽ በአጋጣሚ የሚቀይረው ምንድን ነው

ሀ. ኦክስደንታል ለ. ሻርፕ ሐ.ፍላት

መ. ናቹራል


8. ከዚህ በታች ያለው እስታፍ ላይ የተጻፈው ቁልፍ-----------ነው፡፡



ሀ. $B^b$ማይነር ለ. D' ማይነር ሐ. $E^b$ ማይነር

መ. E ማይነር

9. ከዚህ በታች የተሰራው ቁልፍ የትኛው እስኬል ነው ?



ሀ. 'B' ማይነር ለ. 'A' ሜጀር ሐ. 'D' ሜጀር

መ. $A^b$ማይነር

10.'$B^b$' ሜጀር ቁልፍን አስመልክቶ ትክክል የሆነ የቱ ነው?

ሀ. $B^b$ እና $E^b$ ለ. D እና A ሐ. $B^b$ እና $A^b$

መ. $B^b$ $E^b$ እና $A^b$

11.በፊልም አጀማመር ውስጥ በመጀመሪያ ስሙ የሚነሳ ሰው ማን ነው

ሀ. ኢድዋርድ ሙይብሪጅ ሐ. ዊልበርት ጎልድ

ለ. ቶማስ ኢድሰን መ. ቡልምዬ ብራዘር

12.ፊልም ለመስራት የሚያስፈልጉ መሳሪያዎች የሆነዉ የቱ ነው ?

ሀ. ካሜራ ለ. ድምጽ መቅጃ ሐ. መብራት

መ. ሁሉም መልስ ናቸው

13.አንድ ትያትር በመጀመሪያ ከምን መጀመር አለበት

ሀ. የሚጻፈውን ሀሳብ ማግኘት ሐ. አዘጋጅ

ለ. የትያትር መሳሪያዎችን ማዘጋጀት

መ. ሁሉም መልስ ናቸው፡፡

14.ከዚህ በታች ካሉት ውስጥ የስነ-ተውኔት ምንጭ የሆነ የቱ ነው ?

ሀ. ማስተዋል ለ. ምናባዊ ችሎታ ሐ. ድንገታዊ ፈጠራ

መ. ሁሉም መልስ ናቸው፡፡


## III. ከዚህ በታች ያሉትን ጥያቄዎች በተጠየቀው መሰረት መልሱ፡፡

1. የሙዚቃ ድምጾች ስብስብ በቅደም ተከተል ከወፍራም ድምጽ ወደ ቀጭን ድምጽ ወይም ከቀጭን ድምጽ ወደ ወፍራም ድምጽ እየጨመረ ወይም እየቀነሰ ሲሄድ ምን ይባላል ?
2. የሜጀር ቁልፍ ስንሰራ በ---------እና --------ድምፅ እንዲሁም፤ በ----------እና-------ድምጽ መሀል የሰው እረምጃ ሁሉም ጊዜ ግማሽ መሆን አለበት፡፡


3. ከዚህ በታች ያለው የሙዚቃ እስታፍ ላይ ያለው ኖታ የትኛውን ቁልፍ ያሳያል፡፡




4. ከዚህ በታች ያለው የሙዚቃ እስታፍ ላይ ‘F’ ሜጀር እስኬል ሰርታችሁ አሳዩ



5. ከዚህ በታች ያለው የሙዚቃ እስታፍ ላይ ‘G’ ማይነር ቁልፍ ሰርታችሁ አሳዩ፡፡



6. ከዚህ በታች የተጠየቁትን ቁልፎች እስታፍ ላይ በመጻፍ እነሱን የሚተካውን የሜጀር ቁልፍ ሰይሙ፡፡



3 ፍላት    4 ሻርፕ    5 ፍላት    5 ሻርፕ    7 ሻርፕ

# ምዕራፍ 2

# የፈጠራ ችሎታ

ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎናጸፉ የሚገባቸው የመማር ብቃት፡-

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- የትሬብል ክሌፍ እና ቤዚክሌፍ ልዩነትን ለይተህ ትናገራለህ/ሽ ፡፡
- ቀለል ያሉ የዜማ ምቶችን ትገነዘባለህ/ሽ፡፡
- ከፍና ዝቅ ያለ ድምጾችን በመለየት ትረዳለህ/ሽ፡፡
- በንድፍ እና በተለያዩ ስነ-ስዕል መካከል ያላቸውን ትስስር ያደንቃሉ፡፡
- ንድፍ በቀለም ህትመትና ቅርጻ ቅርጽ ውስጥ ያለው ጥቅም ትገልጻለህ/ሽ፡፡
- የቀለም ቅብ ንድፍ በምን መልኩ እንደሚነደፍ ትለያለህ/ሽ፡፡
- ቀለል ያሉ ንድፎችን ለቀለም ቅብ ስራ ይነድፋሉ፡፡
- ሀሳባቸውን በስነ-ቲያትር እና በስነ-ፊልም ተጠቅመው ይገልጻል/ትገልጻለች፡፡

## መግቢያ

በምዕራፍ አንድ ውስጥ የሜጀር ቁልፍ ፍቺ እና የማይነር ቁልፍ ፍቺ እንዲሁም፣ ፒች (piich) የቁልፍ ምልክት ጥቅሙን ተምረሃል፡፡ በዚህ ምዕራፍ ደግሞ ስለ ከፍታና ዝቅታ ድምጾች እንዲሁም፣ ትሬብል

ክሌፍና ኖዚ ክሌፍ ላይ ቀለል ያሉ ዜማዎችን እንዴት በሙዚቃ ስታፍ ላይ አንብበህ ማዜምን በመቻል ትማረለህ፡፡ እንዲሁም ንድፍ የሁሉም ስነ-ስዕል መነሻ ነው፡፡ አንድ የስነ ስዕል ስራን ከመስራት በፊት ለመስራት

የፈለግነውን ጠቅላላ ሀሳብ በንድፍ ማሳየት፡፡ በንድፍና የስነ-ጥበብ ዓይነቶች መካከል ትልቅ ግንኙነት አለው፡፡

የውስጣችንን ሀሳብ ከምንገልጽበት መንገድ አንዱ ሥነ-ትያትር ነው፡፡ ሀሳባችንን በትያትር መግለጽ ሲንል፣ አንድ ሰው በአይምሮው ውስጥ ያለውን የሀሳብ ክምችት ወደ ፈጠራ በመቀየር በስነ-ትያትር መልክ መግለጽ ይችላል፡፡ ተማሪዎችም ሀሳባቸውን መግለጽ የፈለጉትን በስነ-ትያትር መልክ በመጠቀም የሚያቀርቡ ይሆናል፡፡

## 2.1 ቀለል ያሉ ዜማን ምት ክሌፎች ላይ መጻፍ

### የግንዛቤ ጥያቄ

ቀጭን ወፍራም እና መካከለኛ ድምፅን መነሻ ለይተን ለማዳመጥ ወይም ለመዘመር የምንጠቀመው ምልክት ምንድን ነው ?

ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎናጸፉት የሚገባቸው የመማር ብቃት

በዚህ ምዕራፍ መጨረሻ፡

- የቤዝ ክሌፍና ትሬካል ክለፍ ልዩነትን ይገልጻል/ትገልጻለች፡፡
- ቀለል ያሉ የዜማ ምትቾን ይጫወታሉ፡፡

### ተግባር አንድ

በሙዚቃ ስታፍ ላይ ክሌፎችን መጠቀም ለምን አስፈለገ ?

ቀለል ያሉ ዜማን ትሬብልና ቤዝ ክሌፍን በመጠቀም መጻፍ፣ መለማመድ፣መሠረታዊ ይዘትን ለይተን ማወቅ ካለብን ውስጥ

የክለፎችን አይነት፣የጊዜ ማሳየ ምልክት፣(ፐች) ዜማና የምት ክፍልፋዮች ወሳኝ የሆኑ ናቸው፡፡

ጊዜ ማሳያ ዘዴ ከዚህ በፊት እንደተማራችሁት በቁጥር የሚገለፅ ሲሆን፤ በመጀመሪያ የሙዚቃ አስታፍ ላይ ከክለቭ ቀጥሎ የሚጻፍ ነው፡፡ የትኛውም ሙዚቃ የተወሳነ ምት ጠንካራና ለስላሳ ቢት ይጀምራል፡፡

## የጊዜ ማሳያ ምልክት

የጊዜ ማሳያ ምልክት ደግሞ በባር መስመርን መክፈል፤ አንድና ከሌላ የሚቀጥለው መሀል ቋሚ ሆኖ እንዲቀጥል ወይም አንድ አይነት ስፍራ እንዲኖረው ያደርጋል፡፡

ላይኛው ቁጥር በአንድ ባር ውስጥ ያሉትን ምት የሚያሳይ ሲሆን፤ የስረኛው ቁጥር ደግሞ ለየትኛውም ኖታ የተሠጠ ምት መኖሩን ያሳያል፡፡

ከጊዜ ማሳይ ምልክቶች ውስጥ በስራ ላይ እያዋልን ያለነው $^{4}4$ $^{4}2$ $^{4}3$ 6 $^{2}2$ እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

### የሙዚቃ ክሌፎች

ክሌፍ የሙዚቃ ኖታ በፊደል ተሰይመው ወፍራም ድምፅ፣ቀጭን ድምፅ እና መካከለኛ ድምፅ የምንለይበት ሲሆን፤ ሁልጊዜ በእስታፍ መጀመሪያ ላይ ይጻፋል፡፡ በተጨማሪም በእስታፍ መስመር እና ባዶ ቦታ ላይ ኖታ የት

እንደሚጻፍ የሚወሰኑ ናቸው፡፡ ክሌፍ ሙዚቃን በማቀናጀት ውስጥ ከፍተኛ ቦታ አለው፡፡

## ፒች

ፒች የቁልፍ ድምፅ ሆኖ ከየአንዳነዱ ከሙዚቃ መሳሪያዎች የሚሰማ ድምፅ ነው፡፡

## ምት

ከሙዚቃ ሂደት ጋር የሚደረገው ተግባር ወይም እንቅስቃሴ ነው፡፡

## ዜማ


እንደ ኖታ በምንልበት ጊዜ የፒች ድምፅ የተገደበና የተገደበ ቆይታ ያለው ሆኖ ኖታዎች ቀጣይነት ባለው በቅድመ ተከተል በመጣበቅ ተያይዘው በቅንጅት የሚፈጥሩት ዜማ ይባላል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ዜማ የድምጽ ፍሰት ተቀናጅተው ለጆሮ ማራኪ በሆነ መልክ የሚፈጠር ነው፡፡

በአጠቃላይ ዜማ ለመለማመድ ሆነ በሙዚቃ ሰሌዳ ላይ ትርጉም ባለው መልኩ ለመግለጽ፤ ከዚህ በላይ የተገለጹ የሙዚቃ ኢለመንትስ ሁሉም ያላቸው ድረሻ ከፍተኛ ነው፡፡ ከዚህ ነጥብ በመነሳት ዜማ ወይም የድምፅ ፍሰት ማራኪ ቀለል ያለ ምት ያላቸው ክሌፎች በመጠቀም በሙዚቃ ሰሌዳ (የእስታፍ መስመሮች) ላይ መጻፍና መጫወት ይቻላል፡፡ (የእስታፍ መስመሮች) ላይ ሲጻፍ ከዚህ በታች እንመልከት፡-

.

ምሳሌ 1






ምሳሌ 2



ምሳሌ 3




ቤዝ ክሎፎች በመጠቀም በቀላል ምት በሙዚቃ ሰሌዳ (እስታፍ) ላይ ዜማ ሲጻፍ ከዚህ በታች እንደ ምሳሌ የተጻፈውን ተመልከቱ



ኖታዎች በይበልጥ (በብዛት) በሙዚቃ እስታፍ ላይ በሚውሉበት ጊዜ መሪ መስመር ላይ ሲውሉ ሙዚቃ ለማንበብም ሆነ ለመጻፍ የሚቀለው ክሌፎችን በመጠቀም ነው፡፡ ከዚህ በታች ባለው የሙዚቃ ሰሌዳ ለመረዳት እንደሚቻለው ኖታዎች ትሪብል ክሌፍና ቤዝ ክሌፎች ላይ ያሉት ተመሳሳይ ናቸው፡፡ ያለው ልዩነት የቤዛ ክሌፎች ላይ ያሉት ረዳት መስመር ላይ ወይም የሙዚቃ ሰሌዳ ስር ደግሞ ለመጻፍ የሚያግዙት ብዙዎች መጠቀሳቸው ነው፡፡

### ረዳት መስመሮች


ረዳት መስመሮች ትንንሽ መስመሮች ከእስታፍ ውጭ ሙዚቃን ለመጻፍና የሙዚቃ ድምፅን ከእስታፍ በላይ ወፍራም ወይም ቀጭን የሆኑትን ጨምረን የሚንፅፍበት ነው፡፡ ይሁን እንጂ የረዳት መስመር ብዛት በማሳነስ በቀላሉ ትሬብል ክሌፍ ላይ እንዳለ መጻፍ ይመረጣል፡፡

**ምሳሌ**



ስዕል 1 ተመሳሳይ የሙዚቃ ድምጽ የሆኑትን በትሬብል ክሌፍና በቤዝ ክሌፎች ጊዜ ሲጻፍ የሚያሳይ ስዕሎች ፡፡

በኖታ ፊደል "G" ትሬብል ክሌፍ ላይ ያለው የኖታ ፊደል 'C' መሀል ላይ ( C ክሌፍ) በላይ የሚገኙ ሲሆን፤ የኖታ ፊደል 'F' ቤዝ ክሌፍ ላይ ያለው ደግሞ የኖታ 'C' ፊደል መሀከል በታች ይገኛል፡፡ ይህ ማለት ትሬብል ክሌፍ ቤዝ ክሌፍ በአንድ ቦታ ሲቀመጡ የኖታዎች ረጂ ድምጽ በሰውና በሙዚቃ መሳሪያ በስራው ያሳያል ማለት ነው፡፡




ሥዕል 2 ትሬብል ክሌፍ እና ቤዝ ክሌፍ መሀል C መካከለኛ መኖሩን ያሳያል፡፡

## ሀ. ከፍና ዝቅ የሚሉ ድምጾች

**ተማሪዎች ቢያንስ መጎናፀፍ ያለባቸው የመማር ብቃት**

ከዚህ ትምህርት ምዕራፍ በኋላ ተማሪዎች፡-

- ዝቅ የሚሉትን ድምጾች ለይተው ይናገራሉ፡፡
- ከፍና ዝቅ የሚል የድምጽ መጠን በሙዚቃ ውስጥ ያላቸውን ድረሻ ለይተው ያብራራሉ፡፡

ድምፅ ከፍና ዝቅ በሚልበት ጊዜ ደጋግመን ስንለማመድ ለፒች ያለን ስሜት እየጨመረ በመሄድ የሚናወጣው ድምጽ (የምንሰማው) በትክክል መዜሙን ወይም ጉድለት መኖሩን መለየት ይቻላል፡፡ በሌላ በኩል ሲንዘምር (ሲንዘፍን) ፒች መጠበቃችን ከእስከል ሳንወጣ እንድንናገር ያደርገናል፡፡

**ተግባር 2**

ልምምድ ከዚህ በታች በፒያኖ ቁልፍ (ክሌፎች) እና በሙዚቃ ሰሌዳ (እስታፍ) ጎን ለጎን በማያያዝ ደጋግማችሁ ተለማመዱ፡፡

ሰማያዊ የተቀቡ ቁልፎች ድምጾችን እንድንለማመድ የታዘዝንባቸው ቦታ መሆኑን ለማሳየት ብቻ ነው፡፡






## 1. ከፍ ያለ የሙዚቃ ድምፅ

ከፍ ያለ የሙዚቃ ድምፅ ወይም ቀጭን ('G' ተሬብል) ክሌፎች ላይ የምንጫወተው ይሆናል፡፡ ከፍ ያለ የሙዚቃ ድምጽ ቀጭን ድምጽ የሚያወጡ መሣሪያ ተብለዉ የሚታወቅ እና ቀጭን ድምጽ ማውጣት ለሚችሉ ሰዎች የሚንጫወት ይሆናል፡፡ ከፍ ያለ የሙዚቃ ድምጽ ቀጥታ ድምጽ የሚያወጡ መሣሪያ ተብለው የሚታወቁ እና ቀጭን ድምጽ ማውጣት ለሚችሉ ሰዎች የሚንጫወት ይሆናል፡፡

ተግባር 3

ከዚህ በታች የተጻፈውን ሙዚቃ ከፍ ባለ ድምጽ /በቀጭን/ በሙዚቃ መሳሪያ ተለማመዱ፡፡



## 2. ዝቅተኛ የሙዚቃ ድምጽ

ዝቅተኛ ወይም ወፍራም የሙዚቃ ድምጽ F'(ቤዝ) ክሌፍ ላይ ይጫወታል፡፡

ወፍራም ወይም ዝቅተኛ የሙዚቃ ድመጽ ወፍራም ድምጽ የሚያወጡ የሙዚቃ መሳሪያዎች ተብለው የሚታወቁ ወፍራም ድምጽ ማውጣት በሚችሉ ሰዎች ይጫወታል፡፡

### ተግባር 4

1. ከዚህ በታች ያለውን ሙዚቃ በወፍራም ድምጽ ተለማመድ፡፡



2. ከዚህ በታች ያለውን ዜማ ከመምህር ጋር በመሆን ተለማመድ፡፡





## 2.2 የቀለም ቅብ እና የህትመት ንድፍ

**ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎናጸፉ የሚገባቸው የመማር ብቃት፤**

**ከዚህ ትምህርት ርዕስ በኋላ ተማሪዎች፡-**

- ለቀለም ቅብ እና ለህትመት የሚሰራ ንድፍ ትለያላችሁ፡፡
- ለቀለም ቅብ ስራ ቀላል የሆኑ ነገሮችን ንድፍ ትነድፋላችሁ፡፡
- የነደፋችሁትን ንድፍ የተለያዩ ቀለሞችን በመጠቀም ቅቡን ተቀባለችሁ፡፡

ተግባር 5

ንድፍ ምንድን ነው ?

ንድፍ የሁሉም ስነ-ስዕል መነሻ እንደሆነ እና አንድ ሰው ትክክለኛውን ንድፍ የማይነድፍ ከሆነ፤ ቀለም ቅብ፣ቅርጻ ቅርጽ ትክክለኛውን የህትመት ስራ መስራት እንደማይችል ባለፈው ምእራፍ ውስጥ ተምራችኋል፡፡ ስለዚህ ንድፍ በደንብ መንደፍ አስፈላጊ እና ወሳኝ ነው፡፡ መስመሮች በመገናኘት፣በመራራቅ፣በመቁረጥ የተለያዩ ብርሃንና ጥላን መፍጠር ይችላሉ፡፡ አንድ መስመር ከሌላው መስመር ጋር እየተጠጋጋ በሚሄድበት ጊዜ የተለያዩ ጥላ እና ውፍረት ሲፈጥር እየተራራቀ በሚሄድበት ጊዜ ደግሞ በመሳሳት ንጣትን ያሳያል፡፡

በንድፍ ውስጥ የተሰመረ መስመር ወፍራም ወይም ጥቁር ከሆነ፣

ያኛው ነድፍ የሚገኘው ጥላ ወይም የብርሃን ተቃራኒ ቦታ ነው፡፡

እንዲሁም ጥንካሬና ክብደት አለው ማለት ነው፡፡

በንድፍ ውስጥ የተሰራ መስመር ቀጭን ወይም ነጣ ያለ ከሆነ ደግሞ፤

ያኛው የነደፍነው ንድፍ የሚበራበት ብርሃን በመብራት አቅጣጫ ያለው እና ክብደት የሌለው መሆኑን ያሳያል፡፡

ስለዚህ አንድን ንድፍ ስንነድፍ በቅርጻ ቅርጽ፣የቀለም ቅብ እና የህትመት መሆኑን ለይተን ማወቅ አለብን፡፡ የምንነድፈው ንድፍ በሚሰራ የስነ-ስዕል ስራ የረሱ ባህሪ እና ልዩነት አለው ማለት ነው፡፡

### 2.2.1. የቀለም ቅብ ንድፍ

የቀለም ቅብ ፎርም በሚሰራው የቀለም ቅብ ንድፍ ላይ በማተኮር የሚሰራ ነው፡፡ የቀለም ቅብ ንድፍ የሚሰራው በሚንጠቀመው የቀለም አይነት ላይ ተሞርክዘው ልዩነት አለው፡፡ የውሃ ቀለም በሚንጠቀምበት ጊዜ የምንጽፈው የንድፍ አይነት ሳሳ ያለ እና ቀጭን መሆን አለበት፡፡ ምክንያቱም ወፍራም መስመር የሚንጠቀም ከሆነ፤ የውሃ ቀለም የሚንጠቀምበት ከሆነ መስመሩ በቀለሙ ስር ጎልቶ በመጣየት የማንፈልገውን መስመር ስለሚያሳይ የሚንጠቀመው መስመር መቅጠን ወይም መሳሳት አለበት፡፡



ስዕል 2 ለውሃ ቀለም ንድፍ እንዴት እንደምንነደፍ የሚያሳይ ስዕል፡፡

ልምምድ 1

ከዚህ በላይ ያለዉን የዉሃ ቀለም ቅብ ንድፍ ሥዕል በእርሳስ ንዳፍ የዘይት ቀለም በመቅጠን ቀለም ቅብ የሚንሰል ሲሆን በተቃራንዉ ከዚህ በላይ ደማቅ እና ፈዛዛን መስመር መተቀም አለብን፡፡ ምክንያቱም ስስ በሆነ መስመር የዘይት ቀለም ቅን ንድፍ ነድፌን፤ በዛዉ ንድፍ ላይ ቀለም ስንቀባ በቀላሉ ሊደበቅብን ይችላል፡፡ ስለዚህ የዘይት ቀለም ቅብ ስንሰራ ደማቅ ወይም ወፍራም መስመር መጠቀም አለብን፡፡


ልምምድ 2

1. ቀላል የሆኑትን የፎርም ንድፍ በወረቀት ላይ ስሩ፡፡
2. የሰራችሁትን ንድፍ በማየት ማስተካከል ያለባችሁን ነገሮች ከመምህራችሁ ሀሳብ በመውሰድ ከአካባቢያችሁ የምታገኙትን ቀለም በመጠቀም ቀብታችሁ አሳዩ፡፡

## 2.2.2.የቅርጻ ቅርጽ ንድፍ

አንድ የቅርጻ ቅርፅ ባለሙያ የቅርጻ ቅርጽ ስራ ከመጀመር በፊት ንድፉን በወረቀት ላይ መንደፍ አለበት፡፡ ምክንያቱም :-

- ቅርጻ ቅርጽ ለሚሰሩ ባለሙያዎች ንድፍ መስራት የሚያስፈልገው አይተው ለመስራት የሰሩትን ነገሮች እንዳይረሱ ወዲያው በወረቀት ላይ መንደፍ አለባቸው፡፡



ስዕል 2.2.1. የስነ-ቅርጻ ቅርጽ ንድፍ ስራ የሚያሳይ ስዕል ፡፡

ልምምድ 3

ከዚህ በላይ የተሠራውን የቅርጻ ቅርጽ ንድፍ ስራ በእርሳስ ንደፉ፡፡

ልምምድ 4

ከመምህራችሁ የተሰጣችሁን መመሪያ በመከተል የተሰጣችሁን ተግባር ስሩ፡፡

1. እርሳስ በመጠቀም በአካባቢያችሁ የሚገኙትን ቁሳቁሶች (እንደ ጀበና፣ስኒ፣ኩባያ፣ፅዋ፣እንስራ፣ማሰሮ፣ድስት እና የመሳሰሉት) መርጣችሁ በወረቀት ላይ ስሩ፡፡

2. የሠራችሁን ንድፍ ለመምህራችሁ ከአሳያችሁ በኋላ መምህራችሁ የሰጣችሁን ሀሳብ በመውሰድ የሰራችሁትን ንድፍ አሻሽሉ፡፡
3. የሸክላ አፈር ወይም ሌሎች በአካባቢያችሁ የምታገኙትን ነገሮች ቅርጻ ቅርጽ ለመስራት የሚሆኑትን በመጠቀም የሠራኸውን ንድፍ ለማየት ቅርጻ ቅርጽ ስሩ፡፡



ስዕል 2.2.2. የህትመት ስራን የሚያሳይ የንድፍ ፎቶ፡፡

ልምምድ 5

ከዚህ በላይ የተሠጠውን የህትመት ስራ ንድፍ ለማየት እርሳስን በመጠቀም ንደፉ፡፡

ከመስራታቸው በፊት ሀሳባቸውን እንዲሰበስቡ ይረዳቸዋል፡፡

የሚሰሩትን ስራ በትኩረት እንዲመለከቱ እና እነዲገነዘቡ ይረዳቸዋል፡፡ የቅርጻ ቅርጽ ባለሞያዎች የሚሰሩትን ስራ በተለያየ አቅጣጫ እንዲያዩ

ይረዳቸዋል፡፡

የቅርጻ ቀርጽ ንድፍ ከቀለም ስራ ንድፍ ልዩነት አለው፡፡ በቅርጻ ቅርጽ ንድፍ ስራ የሚሰሩ መስመሮች ከቀለም ቅብ ንድፍ መስመሮች ይደምቃሉ፡፡ እንዲሁም፤ የቅርጻ ቅርጽ ንድፍ በፎርም ጥናት ላይ የተመረኮዘ ነው፡፡

2.2.3 የህትመት ንድፍ

ንድፍ እና የህትመት ስራ የቅርብ ግንኙነት አላቸው፡፡ በሚሰራ የህትመት ስራ ውስጥ ንድፍ መሠረታዊ ነው፡፡ ለምሳሌ፡- የእስቴንስል ህትመት፣ከላጅ፣ሞዛይን፣ፖስተር፣ሎጎ እና የመሳሰሉትን ለመስራት፤ መጀመሪያ የሚሰራውን የዲዛይን ንድፍ መንደፍ አስፈላጊ ነው፡፡ የህትመት ስራ ልዩነት እንደላው ሁሉ የሚሰራበት ዘዴም ልዩነት አለው፡፡ ቀላል የህትመት ስራ በወረቀት ገጽ ላይ እንደሚሰራ ሁሉ በከፍተኛ ደረጃ የተለያዩ ማሽኖችን በመተቀም የሚሰሩ ሕትመቶችም ብዙ ናቸው፡፡

ቀላልና የቆየ ህትመት ከሆኑት አንዱ የእንጨት ቀርጻ ቅርጽ ህትመት ሲሆን በጣም ጥቁር ወፍራም እና የሚደምቅ መስመር ለመንደፍ የጠቆረው መስመር የሌለበት ቦታ ቆርጦ በማውጣት የሚሰራ ነው፡፡ የእንጨት ቀለም ሲቀባ ተቆርጦ የወጣው ቦታ ቀለም አያገኘውም፡፡ ስለዚህ በወረቀት ላይ የህትመት ስራ ስንሰራ ህትመቱም በጥቁር መስመር ላይ ዲዛይኑ ላይ ወይም ተቆርጦ ባልወጣው ላይ የሆናል፡፡ በአጠቀላይ ዲዛይን ስራ በስነ-ስዕል ውስጥ ከፍተኛ ስራ አለው፡፡

የትያትር እና የቪዲዮ የሀሳብ ገለጻ

**ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎናጸፉ የሚገባ የመማር ብቃት፤-**

ከዚህ ትምህርት ርዕስ በኋላ ተማሪዎች፡

- የስነ-ትያትር እና ስነ-ፊልምን ሀሳብ ታብራራለህ

ከዚህ ያለውን ምሳሌ ሀሳብን በቲያትር መግለጽ የሚለውን ተመልከቱ፡፡

ጊዜው ሰው ሁሉ የራሱን ሀሳብ እንደተመቸው የሚገልጽበት ጊዜ ነው፡:

ቦታው በኦሮሚያ ክልል በነቀምት ከተማ በአቶ ኩምሳ ቤት ውስጥ ነው፡፡ አቶ ኩምሳ ስልጣኔ ብለው የሚያስቡትን ዘመናዊነት መከተል ነው፡፡ አንድ ወጣት የሆነ ልጅ አለው፡፡ አብረው ሲወያዩ ይታያሉ፡፡ መጋረጃው ሲገለጥ፤

**አቶ ኩምሳ፡** ልጄ መዝናናት አስፈልጎኛል፤ እስቲ የሰራኸውን ዘመናዊ ሙዚቃ አሰማኝ/ክፈትልኝ፡፡

**የሮን፡** እሺ 'ማይ ዳድ' አንተ ከእኔ ጋር ዘመናዊ ሙዚቃ ለማዳመጥ ብቻ ፍቃደኛ መሆንህ ለእኔ የተለየ ደስታ የሠጠኛል (የሰራውን ሙዚቃ ከፍቶ አሰማው)፡፡

**አቶ ኩምሳ፡** ከሙዚቃው ጋር እንደ ወጣት ዘመናዊ ዳንስ ጀመሩ፡፡

**ወ/ሮ ሶሬ፡** ምንድነው መሬቱን የሚደበድበው ብላ ቀስ ብላ ተደብቃ ወደ ጓሮ መጥታ ስታይ፤ አባወራዋ ከዘመናዊ ሙዚቃ ጋር ሲደንስ አይታ አፍራ ወደ ኋላ ተመለሰች፡፡

**የሮን፡** በቃ 'ዳድ' አንድ ጊዜ ተቀመጥ እንወያይ፡፡

**አቶ ኩምሳ፡** እሺ ምን አልክ ልጄ ፡፡

**የሮን፡** አሁን ዘማናዊነትን አብረን መከተል አለብን የዱሮ ከአንተ ጋር አይሄድም፡፤

**አቶ ኩምሳ፡** ላለፈው እራሱ እያናደደኝ ነው አንተ በርታና ስራ እኔ

ከአንተ ጎን አለው፡፤

**የሮን፡** አሁን ያለንበት ዘመን ግሎባላይዜሽን ነው(ዘመናዊ ነው)፡፡ እነርሱን መከተል አለብን፡፡

**አቶ ኩምሳ፡** የሰውዮውን ስም ማን አልከኝ፡፡

**የሮን፡** ሳቀ ግሎባላየዜሽን ግዜ ነው እንጂ ሰው አይደለም (በመሀል የየሮን እናት ብቅ አለች)፡፡

**ወ/ሮ ሳሬ፡** እኔን ነው ምንም አታውቅም ያላችሁት የውላችሁ ከልጆች ጋር

እድሜውን የማይመጥን ነገር በመለማመድ ተዋረደ፡፡

**አቶ ኩምሳ፡** ተናደደ ስለዘመናዊነት ምን ታውቂያለሽ ዝም ብለሽ ቤት ውስጥ

ተቀመጪ (ለመማታት ቤት ውስጥ አሯሯጣት)፡፡

**የሮን፡** (መሀል ገብቶ በመገላገል አስታረቃቸው) ዳድ ከዛሬ ጀምረዉ ስሜን ወደ

ዘመናዊ ስም ቀይርልኝ (ብሎ ጠየቀው)፡፡

**አቶ ኩምሳ፡** ከዛሬ ጀምሮ የሮን የሚባለው ስምህ ወደ ተቀይሯል፡፡ ከዚህ በላይ

በተሰጠው ምሳሌ ላይ መረዳት እንደሚቻለው፤ የሰው ልጅ በአዕምሮው ውስጥ ያለውን ሀሳብ በትያትር መግለጽ እንደሚችል እና የፈጠራ ችሎታችን ለማዳበር ይረዳል፡፡

ፊልም ማለት የሀሳብ ፈጠራን በካሜራ ወይም በእስኮርን ተጠቅመን የምንፈልገውን መልእክት ለህትረተሰብ በሚዲያ ማስተላለፍ ነው፡፡ ከዚህ በታች ያለውን የፊልም ፈጠራን ምሳሌ ሀሳብ እንዴት እንደሚተላለፍ ተገንዘብ፡፡

ትዕይንት አንድ

የየሮ ሳፋ ትምህርት ቤት ግቢ ውጪ

ቶለሼ እና ጫላ 6ኛ ክፍል የሚማሩ ተማሪዎች ናቸው፡፡ በዕረፍት ጊዜያቸው ባለአራት ፎቅ ህንጻ ላይ ቆመው ሸገር ከተማን ያያሉ፡፡ የሰዎች እና የተለያዩ ነገሮችን እያዩ ያደንቃሉ፡፡

ቶለሼ

አለም የሁለት ጭንቅላት ሰዎች ተሸክማ ትኖራለች፡፡

ጫላ

ምን ማለት ነው? አልገባኝም ፡፡

ቶለሼ

ማለቴ፤ጥላማ እና ብርሃናማ የሆነ ጭንቅላት ነው፡፡

ጫላ

ጭለማው መብራት የለውም ማለትሽ ነው

ቶለሼ

አንተ እየቀለድክ ነው እኔ የታዘብኩት ነገር አለ፡፡

ጫላ

ፎቅ ላይ በነበርንበት ጊዜ ብዙ ሃሳብ ወደ ጭንቅላትሽ መጣ ማለት ነው፡፡

ቶለሼ

አንዳንድ ሰው ጭንቅላቱ ጨለማ ነው ማለቴ፤ሰው ሲመጣበት እንደ አውሬ ማየት ይፈልጋል፤ጭንቅላቱ ብርሃናማ የሆነ ደግሞ ውሻ ራሱ ብትመጣበት እንደ ሰው ያከብራል ማለቴ ነው፡፡

ጫላ

ቶለሼ አሄ ከባድ ሀሳብ ነው ፡፡

ቶለሼ

አዎ ለሁሉም የሚከብድ ሀሳብ ነው ነገር ግን ሁሉም ሰው ቀና አስተሳሰብ

ቢኖረውና እርስ በእርስ ተከባብረን በጥንቱ ባህላችን ብንኖር፤ ማለቴ ነው::

ጫላ

ተይ አንቺ ገና ልጅ ነሽ አዬ በሀይል አትጨነቂ፡፡

ቶለሼ

ልጅነት በጎ ማሰብን አያዳግትም ቢሆንም፤ ከአባቶቻችን ባህል ጥሩ ማሰብ ተምረናል (ደወል ሲደወል ወደ ክፍል ተመልሰው ትምህርታቸውን ቀጠሉ) ፡፡

በአጭሩ ከዚህ በላይ በተሰጠ ምሳሌ ላይ መረዳት የሚቻለው የፊልም ፈጠራ ስራ ተጠቅመን ሀሳባችን መግለጽ እንችላለን፡፡

ተግባር 6

በአእምሮ ውስጥ የመጣውን ሀሳብ ወደ ቲያትር እና ፊልም ቀይራችሁ ጻፉ፡፡

## የምዕራፍ ሁለት ማጠቃለያ፡

- አንድን ሙዚቃ በቀላል መንገድ መጻፍና ማንበብ የሚንችለው ክሌፍን ስንጠቀም ነው፡፡
- ትልቁ እታፍ (ግራንድ) የሠው ድምጽ እና የሙዚቃ መሳሪያ ድምጽ ለመጫወት ያስችለናል፡፡
- አጋዥ መስመር ከሙዚቃ እስታፍ ውጪ የሚፃፉ ፅሁፎችን ለመፃፍ ያስችለናል፡፡
- ተራርቀው የተሰመሩ ደምዛዛ መስመሮች ብርሃን ለማሳየት ይረዳል (ያገለግላል)፡፡
- መስመር መጥቆር ወይም መድመቅ የሚችለው እርሳሳችንን አጥብቀን በመጫን ስናሰምር ነው፡፡
- የሚነደፈው ንድፍ በሚሰራው የስነ-ስዕል ሁኔታ የራሱ ባህሪና ልዩነት ይኖረዋል፡፡
- በቀለም ቅብ ውስጥ በምንነድፈው ንድፍ እና በምንጠቀመው የቀለም ዓይነት ልዩነት ይኖረዋል፡፡
- የቅርጻ ቅርጽ ንድፍ ከቀለም ቅብ ንድፍ ይለያል፡፡
- በሚሰራ በህትመት ስራ ሁሉ ውስጥ ንድፍ መሠረታዊ ነው፡፡
- ፈጠራ አዲስ ነገር የማሳየት ችሎታ ነው፡፡
- ስነ-ትያትር እና ፊልም የሠዎችን የሀሳብ ፈጠራ የሚገለጽበት ነው፡፡

## የምዕራፍ ሁለት መልመጃ

I ከዚህ በታች ያሉትን ዓረፍተ ነገሮች ትክክል ከሆኑ እውነት ስህተት ከሆኑ ደግሞ ሐሰት በማለት በጽሁፍ መልስ፡፡

1. መስመሮችን በማራራቅ ሲናሰምር ብርሃንን ለማሳየት ነው፡፡
2. የሚናሰምረው መስመር መድመቅ የሚችለው እርሳሳችንን በማላላት ስናሰምር ነው፡፡
3. የምንሰራው ስራ በብርሃን በኩል ካለ የሚሰመረው መስመር ከፍ ያለው ድምቀት አለው፡፡
4. የሚሰራው ንድፍ በሚሰራው ነገር ላይ በመመስረት ይለያያል፡፡
5. የቀለም ቅብ በሚሰራው ቀለም ፎርምና ቀለም ላይ በማተኮር የሚሰራ ነው፡፡
6. በቀለም ቅብ ውስጥ የሚነደፈው ንድፍ በሚንጠቀመው የቀለም ዓይነት ላይ በመመስረት ልዩነት አለው፡፡
7. በውሃ ቀለም ቅብ ውስጥ ቀጭን መስመር ካሰመርን ቀለም ስንቀባ መስመሩ ከውስጥ ጎልቶ ይታያል፡፡
8. ለቅርጻ ቅርጽ ካለሙያ ንድፍ ወሳኝ አይደለም፡፡
9. የቅርጻ ቅርጽ ንድፍ ከቀለም ስራ ንድፍ ይለያል፡፡
10. ንድፍና የህትመት ስራ ጥብቅ ግንኙነት አለ፡፡
11. ፐች ከጊዜ ጋር ተቀናጅቶ የሚሰራ ተግባር ወይም እንቅስቃሴ ነው፡፡
12. የሙዚቃ ክሌፎች አንድን ድምጽ እንዴት እንደሚንጫወት ያሳዩናል፡፡
13. ኢጋዥ መስመሮች ከእስታፍ በላይ ወይም ከእስታፍ በታች ያለውን ሙዚቃ የሚጻፍበት ነው፡፡

II. ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ፊደል በመምረጥ በፅሁፍ መልሱ፡፡

1. አንድ መስመር በሌላ መስመር ላይ ተጠግቶ ከተሠመረ ምን ያሳያል ?

   ሀ/ ጨለማ ለ/ ድምቀት ሐ/ ጥላ

   መ/ ሁሉም መልስ ነው

2. በውሃ ቀለም ቅብ ስራ የሚነደፈው ንድፍ በምን ዓይነት መስመር ይነደፋል ?

   ሀ/ ቀጭን ለ/ ወፍራም ሐ/ ጠንከር ያለ መ/ መልስ የለም

3. የቅርጻ ቅርጽ ንድፍ በይበልጥ ምን ዓይነት ዘዴ ላይ ያተኩረል ?

   ሀ/ ቀለም ለ/ ቅርጽ ሐ/ ገጽታ መ/ መስመር

4. ቀላል የህትመት ስራ ንድፍ በምን ዓይነት ዘዴ ላይ ያተኩራል ?

   ሀ/ ቀጭን ለ/ ስስ ሐ/ በብርሃን መ/ መልስ አልተሠጠም

5. በአንድ ነጠላ ነገር ውስጥ ያሉትን የኖታ ብዛቶች የሚነግረን በምንድነዉ?

   ሀ/ ክሌፍ ለ/ የቁልፍ ምልክት ሐ/ የግዜ መለኪያ

   መ/ ፒች

6. አራተኛው የቤዝ ክሌፍ መስመር ስሙ ማነው ?

   ሀ/ Mi ለ/ Re ሐ/ La መ/ Fa

7. በግዜ መለኪያ ውስጥ የታችኛው ቁጥር ምን ያመለክታል?

   ሀ/ በዛ ነጠላ ባር ውስጥ ያለውን የኖታ አይነት፡፡

   ለ/ በዛ ነጠላ ባር ውስጥ ባሉ ኖታ ብዛት፡፡

   ሐ/ የ $\frac{1}{8}$ ኖታ ምት መ/ ያ ሙዚቃ የሚጫወትበት ድምጽ፡፡

### III. ከዚህ በታች ያሉትን ጥያቄዎች በስራ አሳዩ ፡፡

1. ከዚህ በታች በእስታፍ ላይ ለተዘረዘሩት ኖታዎች ትክክለኛውን መልስ ጻፉ፡፡





2. ከዚህ በታች ከእስታፍ በላይ እና ከእስታፍ በታች የተጻፉትን ቦታዎች በየትኛው ክሌፍ እንደምትለማመዱ ከመረጣችሁ በኋላ ክሌፍን እስታፍ ላይ በመጻፍ ለእየአንዳንዱ ኖታዎች ትክክለኛውን ስም ጻፉ፡፡



3. በአእምሮ ውስጥ የተፈጠረውን ሐሳብ በቲያትር እና በፊልም ተውኔት ተጠቅመህ ግለፁ፡፡
4. የጻፋችሁትን ተውኔት በቡድን በመለማመድ አሳዩ፡፡

# ምዕራፍ 3

# የባህል እና የታሪክ ተጨባጭ ሁኔታ

### የዚህ ምዕራፍ ትምህርት ውጤት፡

**ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎናጸፉት የሚገባቸው የመማር ብቃት**

**ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች ፡-**

- ትርክትን ወደ ትያትር ትቀይራላችሁ፡፡
- የስነ-ትያትር ታረክ ትጽፋላችሁ፡፡
- የባህል የሙዚቃ መሳሪያዎች አይነት እና የባህል ውዝዋዜ ትገነዘባላችሁ፡፡
- የሙዚቃ መሳሪያዎች እና ውዝዋዜ ያላቸውን ልዩነት ታውቃላችሁ፡፡
- በአካባቢ ከሚገኙ ነገሮች ላይ የባህል ሙዚቃ መሳሪያዎች ትሰራላችሁ፡፡
- በአሪ ታሪክና በስነ ስዕል መካከል ያለውን ግንኙነት ታደንቃላችሁ ፡፡
- ስነ-ስዕል ተረት ተረት በመግለፅ ውስጥ ያለውን ጠቀሜታ ትረዳላችሁ ፡፡
- ስነ-ስዕልን በመጠቀም ተረት ተረትን መግለፅ እንደሚቻል ትለያላችሁ፡፡

**መግቢያ**

ስነ-ትያትርም ሆነ ስነ-ፊልም ተዘጋጅቶ ለማቅረብ በመጀመሪያ ታሪክ መኖር አለበት፡፡ ለስነ-ትያትር እና ለስነ-ፊልም የሚሆነው ታሪክ ከተለያየ ምንጭ እናገኛለን፡፡ ታሪክ ከሚገኝባቸው ምንጮች አንዱ የማህበረሰብ ሥነ-ቃል ነው፡፡ በዚህ ርዕስ ስርም ከማህበረሰቡ ስነ-ቃል ስጥ በአካባቢያችሁ የሚገኘውን ተረት-ተረት አጥንታችሁ በስነ-ትያትር መልክ ታቀረባለችሁ፡፡ በመቀጠልም የባህል የሙዚቃ መሳሪያዎች እንዴት እንደሚሰሩ እና አጨዋወታቸው ትርጉማቸው እና ጥቅማቸውን እና የባህል ውዝዋዜ ትማራላችሁ፡፡ በተጨማሪም ማንኛውም ባህል የራሱን አፈ-ታሪክ መኖሩን እና የአንድን ሕብረተሰብ ባህል፣ታሪክ፣እሴት፣ጀግንነት እና የመሳሰሉትን ለማሳየት በጣም ይጠቅመናል፡፡ አፈ ታሪክ በብዛት ነስነ-ጥበባት የምናሳየው ነው፡፡

## 3.1 የባህል ትርክትን ወደ ትያትር በመቀየር ማሳየት

**ተማሪዎች ቢያነስ መጎናፀፍ የሚገባቸው የመማር ብቃት**

ከዚህ ርዕስ ትምህርት በኋላ፣

የባህል ትርክትን ወደ ትያትር በመቀየር ታሳያላችሁ፡፡

በዚህ ምዕራፍ ባለፉት ትምህርት ክፍሎች ስለ ታሪክና ባህል ተጨባጭ ሁኔታዎች ስትማሩ ቆይተችኋል፡፡ ስነ-ቃልን ወደ ትያትር፣ ተውኔትና ትወና ለመቀየር ስትማሩና ስትለማመዱ ቆይተችኋል፡፡ አሁን ደግሞ የባህል ትርክትን በትያትር በሚለው ርዕስ ስር በኦሮሞ ባህል ትርክት ፍልስፍና ውስጥ የሚታወቁ የሆኑ የኦሮሞ የዘር ሀረግ ትርክት፣ የኦሮሞ ገዳ ስርዓት ትርክት፣ የኦሮሞ ሸነን ኦዳ ትርክት፣ የተፈጥሮ መብት ትርክት ለምሳሌ የዕፅዋት፣ የሰው ልጅ በተለይ የሴቶችና የመሳሳሉትን በማስመልከት ያሉትን ትርክቶች ወደ ትያትር በመቀየር ማሳየት

ይቻላል፡፡ በዚሁ መሠረት የኦሮሞ ህዝብ የሴቶችን መብት በመጠበቅ ላይ ያለውን ትርክታዊ ፍልስፍና በመውሰድ እንደሚከተለው በምሳሌነት ማጤን ይቻላል፡፡

## ሄረ ፌኖ ሰገሊ

ሁለት ተማሪዎች (ወንድና ሴት) በመማሪ ክፍላቸው ውስጥ ሆነው በስነ-ዜጋ ክፍለ ጊዜ የተማሩትን ስለ ሴቶች መብት እየተከራከሩ ይታያሉ፡፡

ተማሪው፡ ከዚህ በኋላ በቃ ሴቶች አንችላችሁም፡፡

ተማሪዋ፡ ለምን

ተማሪው፡ እንዴ በቃ መብታችሁን ከሚገባ በላይ ከመምህራችን ተምራችሁ ነቃችሁብን እኮ፡፡

ተማሪዋ፡ እኛ ገና ዛሬ ስለ መብታችን ከትምህርት ስርዓት ወይም ከመምህር የሰማን ይመስልሃል እንዴ

ተማሪው፡ ታዲያ ከየት ሰማሽ

ተማሪዋ፡ በኦሮሞ የጥንት ህግ-ደንብ ከሄረ ፌኒ ሰገሊ፣ ከንፈኒሳን ሰገልተም ሰገሊ ነው መብታችን ያስጠበቀልን፡፡

ተማሪው፡ እንዴት፣ እንዲህ አይነቱን ፍልስፍና ደግሞ ከየት አመጠሽ

ተማሪዋ፡ ስማ! የኦሮሞ ፍልስፍናም ሆነ ህገ-ደንቡ ሁሉ ሴቶችን እንደሚጠብቅና በሴቶች እንደሚጠበቅ እወቅ

ተማሪው፡ የኦሮሞ ህገ-ደንብ አባ ገዳ እጅ እንጂ እነንተ ሴቶች ጋር ምን ይሠራል

ተማሪዋ፡ የኦሮሞ ሽማግሌዎች እኮ የገዳ ስርዓት ከሚጻፍልን በሴቶች አእምሮ፣ በህፃናትና በበረት ውስጥ እናስጠብቃለን ብለው መስክረውልናል፡፡

ተማሪው፡ አንቺ የምታወሪው ድንቅ ነው! ሌላስ የተሰጣችሁ አደራ አለ

አንዷ ተማሪ፡ ከአደራ የበለጠ ትልቅ ቦታ ነው የተሰጠን፡፡

2ኛዋ ተማሪ፡ በትክክል በዚህ ዓለም ላይ ንጉስ ከሚባሉት አምስት ነገሮች አንዷ ሴት ናት

1. የመሬት ንጉስ- መንገድ ነው
2. የዕፅዋት ንጉስ- ጥጥ ነው
3. የብረት ንጉስ- መርፌ ነው
4. የፀጉር ንጉስ- ቅንድብ ነው
5. የሰው ልጅ ንጉስ- ሴት ናት

ተማሪው፡ ክክክክ (ረጅም ሳቅ ይስቃል) አሁንስ አበዛችሁት የገዳ ስርዓት ህገ ደንብንም የምናወጣው እኛ ነን ሊትሉ ይሆናል እኮ!

ተማሪዋ፡ እሱም እውነት ነው! ሴቶች ከወንዶች እኩል ህገ-ደንብ ታወጣ ነበር፡፡ አንድ ጊዜ ሴት ልጅ አይነስውራንን፣ መስማትና የተሳናቸውን እና አከለ ጎዶሎ የሆኑትን ወንዶች አታገባም ብላ ህግ በማውጣቷ ምክንያት አባ ሴራዎች ይንን ሲሰሙ በመቃወም የሴት አካለ ጎዶሎ ትወለዳለች ስለዚህ ተገባለች ታገባለች፤ ከዚህ በኋላ ሴቶች ህግ አታወጡም ታግዳችኋል ብለው ደነገጉ፡፡

## ስነ-ትያትርን በመጠቀም አፈ-ታሪክን ማሳየት

ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎናጸፉ የሚገባቸው የመማር ብቃት

በዚህ ርዕስ መጨረሻ ላይ፡-

- አፈ-ታሪክን ወደ ትያትር በመቀየር ታሳያለችሁ፡፡
- ታሪክ እንዴት እንደሚጻፍ ታብራራላችሁ፡፡

**ተግባር 1**

1. የሚታውቁትን አፈ-ታሪክ በክፍላችሁ ውስጥ ተነጋገሩ
2. ከተነጋገራችሁበት አፈ-ታሪክ ውስት የታሪኩን ተሳታፊዎች ተክታችሁ ከጓደኞቻችሁ ጋር ተጫወቱ ::

አምስተኛ ክፍል እንደተማርከው ስነ ቃል ታሪክ ማለት፡- በቃል

ዜማ ተሰጥቶት ወይም ሳይሰጠው ፈጠራ እና ስለማህበረሰቡ የሚገልጽ የተለያየ ሙያ ላይ ያተኮረ ነው፡፡ ስነ-ቃል አይነቶች ተረት፣ሽለላ፣እንቆቅልሽ፣ተረት-ተረት ዜማ እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡ ይህንን ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ፤ የምታውቁትን ተረት-ተረት እና የማታውቁትን ጠይቃችሁ ወደ ትያትር ቀይራችሁ ታሳያላችሁ፡፡ ስለ ተረት ተረት አስመልክቶ ባለፈው ክፍል ውስጥ ተረትን በገጸ-ባህሪያት ወይም ስለሚገለጸው ነገር አራዊትን በመተካት አብረው የሚነጋገሩትን አብረው የሚሰሩትን የሚጣሉትን እና የሰው ልጅን ሊያጋጥሙት የሚችለውን ችግር ያስተምረናል፡፡ ከዚህ በታች ስለ አህያ እና ውሻ የተሠጠውን ተረት በስነ-ትያትር መልክ የተዘጋጀውን አስተውሉ፡፡

## አህያ እና ውሻ

(በድሮ ጊዜ አህያ እና ውሻ የጌታቸው ቤት አብረው ይኖሩ ነበር፡፡ አህያም የጌታዋ ሸክም ስለሰለቻት ተነስተን እንጥፋ ብለው ተመካክረው ጠፉ፡፡)

**አህያ** ፡- ተነስተን እንጥፋ ?

**ውሻ**፡- ታገስ! ታግሰን ቢንቀመጥ ይሻላል ከሄድን ልንቸገር እንችላለን ፡፡

**አህያ**፡- እስከመች ነው? ሸክሙን ተሸክሜ የምኖረው

ከዚህ የሚበልጥ ችግር የለም እንጥፋ፡፡

**ውሻ**፡- ተው! ታግሰን እንቀመጥ አንሂድም ፡፡

**አህያ**፡- እኔ ከዚህ በላይ ታግሼ መቀመጥ አልችልም! እሄዳለሁ ፡፡

(አህያዋ ውሻዋን ጥላ ሄደች) አህያዋ ከሄደች በኋላ፤ ወሻውም ተከተላት እየሄዱ እያለ ስለመሸባቸው ለምለም ሳር አግኝተው

በውስጡ አረፉ፡፡

**አህያ**፡- እጮህለሁ! (ሊነጋጋ ሲል አህያዋ ጮኸች)፡፡

**ውሻ**፡- ተይ ተይ ጅብ ድምጽሽን ሰምቶ መጥቶ ይበላናል፡፡ (ውሻም በጣም ፈራች)፡፡

**አህያ**፡- (እምቢ ብላ ጮኸች) አሁንም እጮህለሁ፤ (በሦስተኛው ጅብ የአህያዋን አንጀት ዘርግፎ ገደላት) ውሻዋ ተደበቀች፡፡

**ጅብ**፡- ምን ትሰሪያለሽ ከዚህ (ውሻዋ በተደበቀችበት ቦታ አይቷት)፡፡

**ውሻ**፡-ጌታዬ ለአደን ወጥተን ነው (እየተንቀጠቀጠች)፡፡

**ጅብ**፡-ነይ አሁን ቶሎ ይህን ሁሉ ስጋ በብልት ብልት አውጪ እና ልብ ብቻ አስቀሪ አላት፡፡

**ውሻ**፡- እሺ! (ይህን እየአደረገች እያለች ልቡን ወስዳ በላች፡፡

**ጅብ**፡- ትንሽ ቆይቶ የአወጣሽውን የአህያ ልብ ስጭኝ አላት ፡፡

**ውሻ**፡- ምነው ጌታዬ አህያዋ ልብ ቢኖራት ለምን ጮሀ ተበላች!(በዚህ ያልቃል)፡፡

## 3.2. የባህል ሙዚቃ መስረያዎች

**በዚህ ርዕስ መጨረሻ ላይ፡-**

- የተለያዩ የባህል ሙዚቃ መሣሪያዎችን ክፍፍል ትገልፃላችሁ፡፡
- የባህል ሙዚቃ መሳሪያ አይነቶች ትዘረዝራላችሁ፡፡
- በአካባቢያችሁ ከሚገኙ ነገሮች ላይ የባህል ሙዚቃ ከሳሪያዎች ትሰራላችሁ፡፡

**ተግባር** 2

በቡድን በመሆን፤ በቀላሉ በአካባቢያችሁ ከሚታገኙት ነገሮች ላይ

ከባህል ሙዚቃ መሳሪያዎች ውስጥ አንዱን መርጣችሁ ስሩ፡፡

በሀገራችን ውስጥ የባህል ሙዚቃ መሣሪያዎች በስራ ላይ መዋል ከጀመሩ ይህ በሚባል ዘመን ባይታወቅም ረዥም አመታት አስቆጥሯል፡፡ እንደዛውም በሀገራችን ስራ ላይ እየዋሉ ያሉት መሳሪያዎች በመሻሻል ዘመናዊ የሙዚቃ መሳሪያዎችም ተፈጥሯል፡፡ ዘመናዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች የሚባሉት ውስብስብ በሆነ መንገድ በፋብሪካ ውስጥ እየተሰሩ በአይነት፣በመልክ እን በቅርጽ የተለያዩ እና በተለያዩ መንገድ የሚጫወቱባቸው ናቸው፡፡ በሀገራችን የሚገኙ የባህል የሙዚቃ መሳሪያዎች በሦሥት ትልልቅ ቦታ ይከፈላሉ፡፡ እነርሱም፡-

- የምት
- የትንፋሽ እና
- የክር ናቸው ፡፡

## ሀ. የምት የባህል ሙዚቃ መሳሪያዎች

**ተግባር 3**

❖ የምት የባህል ሙዚቃ መሳሪያዎችን ዘርዝር፡፡

የምት የባህል ሙዚቃ መሳሪያዎች የሚባሉት ከጥንት ጀምረዉ ሰዎች በኑሮአቸው ውስጥ እጅን በማጨብጨብ እና እንጨት አንድ ላይ ከመምታት ጀምሮ እስካ ዛሬ እየተጠቀሙበት ያሉ መሳሪያዎች ናቸው፡፡ እነርሱም መልክና የተለያዩ ቅርፆች ያለው እና ለተለያዩ ነገሮች ለተለያየ ጊዜ የሚጠቅሙ ናቸው፡፡ ይህ ማለት በአመት በዓል ጊዜ፣በሰርግ ጊዜ፣በአምልኮ ጊዜ እና የመሳሰሉት ይጠቅማል ማለት ነው፡፡ ከእነዚህም የምት የባህል መሳሪያዎች ውስጥ የተወሰኑት፡-

1. ከበሮ
2. ከበላ
3. ቡሾ(ቀንድ)
3. መረካሻ እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

### ለ. የትንፋሽ የባህል ሙዚቃ መሳሪያ

የሚባሉት በመንፋት የሚንጫወትባቸው ናቸው፡፡ እነርሱም፡-

- ዋሽንት
- በገና
- ጡሩንባ
- መለከት እና የመሳሰሉት

**ተግባር 4**

1. የትንፋሽ የባህል ሙዚቃ መሳሪያዎችን በመጻፍ ለክፍል ተማሪዎች ግለጹ፡፡
2. የትንፋሽ የባህል ሙዚቃ መሳሪያዎች ከምን ከምን እንደሚሰሩ እና የአጨዋወታቸውን ስልት ግለጹ፡፡
3. የትንፋሽ የባህል ሙዚቃ መሳረያዎች ውስጥ ዋሽንት ወይም ጡርንባ በአካባቢያቸው ከምታገኙት ቁሳቁስ ላይ ሠርታችሁ አሳዩ፡፡

### ሐ. የክር የባህል ሙዚቃ መሳሪያዎች

**ተግባረ 5**

1. የክር የባህል የሙዚቃ የመሳሪያዎች ፅፈህ ለክፍል ጓደኞችህ ግለፅ/ጭ፡፡
2. የክር የባህል ሙዚቃ መሳሪያዎች ከምን ከምን እንደሚሰሩ ዘርዝሩ፡፡
3. የክር የባህል የሙዚቃ መሳሪያዎች ውስጥ አንዱን መርጣችሁ በቡድን ሠርታችሁ አሳዩ፡፡

የሙዚቃ መሳሪያዎች ከጥንት ጀምሮ እንደሚያወቀው ቀስት መወርወር፣ጥጥ መፍተል እና ከመሳሰሉት ጀምሮ እስከ አሁን እየተሻሻለ ስራ ላይ እየዋለ ነው፡፡ የክር የሙዚቃ መሳሪያዎች

ሁለቱን ክር አቀናጅቶ በመገዝገዝ እና በግርፍ ይጫወታሉ፡፡

ከእነዚህ መሳሪያዎች ውስጥ ጥቂቶቹ፡-

1. መሲንቆ
2. ክራር
3. በገና እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

### 3.2.2. የባህል ውዝዋዜ

ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎናፀፉ የሚገባቸው የመማር ብቃት ፡

ከዚህ ትምህርት ርዕስ በኋላ ተማሪዎች፡-

- የአካባቢውን የባህል ውዝዋዜ ለይታችሁ ትገልጻላችሁ፡፡
- የኦሮሚያ ክልል የዞኖች የባህል ውዝዋዜ ትዘረዝራላችሁ፡፡
- ከአካባቢያችሁ የባህል ውዝዋዜ ውስጥ አንዱን ትሠራላችሁ ፡፡

**ተግባር 6**

የአካባቢያችሁ የባህል ውዝዋዜ እንዴት እንደሚጫወት በቡድንአችሁ አንድ መርጣችሁ ተለማምዳችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡

## ውዝዋዜ

ውዝዋዜ ሀሳቦች፣ስሜት፣ልምዳችንን እና እንቅስቃሴ ተጠቅመን የሚንገልጸው ጥበብ ሲሆን፤ ማህበረሰባችን እንደማንኛውም የአለም ማህበረሰብ ኑሮውን ከጥበብ ጋር የሚገልጽ ነው፡፡ ከስነ-ጥበባት ውስጥ ሙዚቃ አንዱ ሲሆን፤ የሰው ልጅ ስሜቱን፣ባህሉ እና ፈጠራውን እየገለጸበት ቆይቷል፡፡ ይህ ማለት ድምጽ እና እንቅስቃሴን ከሰውነት ጋር አዋህዶ በውዝዋዜ መልክ ይገልጻል፡፡ የባህል ውዝዋዜ የህብረተሰቡን ሙዚቃ በእንቅስቃሴ እና በዜማ በሙዚቃ መሳሪያ አቀናብረው ያቀርባሉ፡፡ የባህል ውዝዋዜ እንደ ጌሎ፣ኩምኩሜ፣ረገዳ፣ጺቺሳ፣ሽቦቴ፣ሽጎዬ፣ገድቱሜ፣ትሪ እና የመሳሰሉት በስፋት የታወቃል፡፡

## 3. 3 ስነ-ስዕል በመጠቀም ተረትን አስመስሎ ማሳየት

**ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎናፀፉ የሚገባቸው የመማር ብቃት ፡**

**ከዚህ ትምህርት ርዕስ በኋላ ተማሪዎች፡-የተረትን ምንነት ትገነዘባለህ**

- **ተረት አንዱን መልዕክት በማሳለፍ ውስጥ ያለውን ጥቅም ትገልጻላችሁ፡፡**
- **ተረት ተረትን ትናገራላችሁ፡፡**

### 3.3.1 ተረት ተረት

**ተግባር 7**

**ተማሪዎች፣ሽማግሌዎች ተረት ተረቱን ሲያወሩ ሰምታችሁ ታውቃላችሁ?**

**በአካባቢያችሁ የምታውቋትን ተረት ተረት ተራ በተራ ከመምህራችሁ የሚሰጣችሁን መመሪያ በመከተል ለክፍል አቅርቡ፡፡**

**ተረት-ተረት የማህበረሰብና የባህል ስራን ያሳያል፡፡ ማንኛውም ባህል የራሱ የሆነ ተረት-ተረት እንደ አዝናኝ፣ትምህርታዊ እና የባህል እንክብካቤ የሚያሳይ ባህሪ አለው፡፡ ተረት-ተረት ታሪክን ባህልን፣ እሴትን፣ጀግንነትን፣የህብረተሰብ እምነት እና የመሳሰሉትን ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚያስተላልፍ ነው፡፡**

**ተረት ተረት በቃል ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፍ ሲሆን ስነ-ስዕል ደግሞ በወረቀት እና በመሳሰሉት ነገሮች ላይ ሊሰራ የሚችል ነው፡፡ ምክንያቱም ስነ-ጥበባት በአጭር ጊዜ ውስጥ ብዙ ነገር ማስተላለፍ ስለሚችሉ ነው፡፡ ተረት-ተረትን በመግለፅ የሚጠቅሙ ፎቶ፣ስነ-ስዕል፣የድምፅ እና ምስል ቅኝት ፣ሙዚቃ እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡**

## 3.3.2 ስነ-ሥዕል በተረት ውስጥ ያለው ጥቅም

**ውይይት 1**

ስነ-ስዕል በተረት-ተረት ውስጥ ያለው ጥቅም ምንድን ነው በቡድን በመወያየት ለክፍል አቅርቡ፡፡

በጥንት ጊዜ ተረት-ተረትን የሚገልጹ ስዕሎች ማህበረሰቡ የተረት ተረት ታሪክ በቀል መረዳት እንደምንችለው ስለሚረዳቸው አርቲስቶች በስዕል ይጠቀሙ ነበር፡፡ የተረት-ተረት ስዕል ማህበረሰቡ ልብ-ወለ፣ጭውውት እና ግጥሙን እንዲገነዘቡ ያደርጋል፡፡

## ስዕላዊ መግለጫ

**ልምምድ 2**

ስዕላዊ መግለጫ ጥበብ ማለት ምን ማለት ነው? ጥቅሙስ ምንድን ነው? በቡድን በመወያየት ለክፍላችሁ አቅርቡ፡፡

የአንድ አካባቢ ተፈጥሮአዊ ነገሮች ወይም ሰው ሰራሽ ነገሮችን በስዕል በመንደፍ በቀላል እና ግልፅ በሆነ መንገድ የተፈለገ፣ መልእክት የሚተላለፍበት ስዕላዊ መግለጫ ይባላል፡፡ አንድ ጽሁፍ በስዕል በመደገፍ በቂ የሆነ መልዕክት ይሰጣል፡፡ ለምሳሌ በምናነበው ንባብ ውስጥ የንባቡ መልዕክት ካልገባን ከስእል ላይ እንረዳለን ማለት ነው፡፡

የሰው ልጅ በጥንት ጊዜ የተለያዩ መልዕክት እና ንግግር ሲያስተላልፍበት የቆየ ድምጽን ከፍ አድርጎ በመጮህ እና በመሳቅ እንደሆነ ታሪክ ይገልጻል፡፡ ከጊዜ በኋላ የሰው እግር የሄደበት መንገድ ላይ ድንጋይ በመከመር፣ቅጠል ቆርጦ በማስቀመጥ እና በመሳሰሉት ማስተላለፍ የፈለጉትን መልዕክት በስዕል በተደገፈ ምልዕክት ያስተላልፉ ነበር፡፡ የስዕል መግለጫ ንባብን ስናይ የሰው ልጅን ኑሮ ወለል ከአደረጉት ነገሮች ውስጥ አንዱ ነው፡፡

ስዕላዊ መግለጫ ንባብ መስራት የጀመረው በጥንት ጊዜ የሰው ልጅ

በዋሻ ውስጥ ሲኖር በነበረ ጊዜ ነው፡፡ ከግዜ በኋላ የምስራቅ ኤዥያ ሀገሮች ስዕላዊ መግልጫ ህትመት በለስላሳ እንንጨት ላይ መስራት ጀመሩ፡፡ በዚሁ መሰረት የተለያዩ መፅሀፍት፣መፅሔቶች እና መፅሀፎች መታተም ጀመሩ፡፡

ስዕላዊ መግለጫዎች ያለቸው ጥቅም ብዙ ነው፡፡ እነርሱም፡-

- አንድ ጽሁፍ ያለውን ቦታ በተጨባጭነት (በማስረጃ) ያረጋግጣል፡፡
- በተለያዩ መጽሄቶች ላይ የጹሁፍ መልዕክት ለማስተላለፍ ይረዳል፡፡
- ለልጆች የሚውሉ መጽሀፎች ላይ በተለያዩ ስዕሎች ተደግፎ እንዲታተም እና ጽሁፉ የያዘውን መልዕክት በስዕል እንድንረዳ ያደርጋል፡፡

በአጠቃላይ የስእል መግለጫ በፅሁፍ፣በፎቶ፣በቀለም ቅብ እና የመሳሰሉትን በመጠቀም በደንብ ተዋህዶ ያሰበውን ሀሳብ በደንብ እንዲማርክ እና ማንኛውም ሰው ለይቶ መረዳት እንደሚችል በማድረግ በተረት ተረትም ሆነ ትምህርታዊ መልዕክትን ለማስተላለፍ ከፍተኛ ሚና አለው፡፡

# ጅብ እና አህያ



በዱሮ ጊዜ አህያ እና ጅብ አይተዋወቁም ነበር፤ አንድ ቀን አህያዋ የጅብን ድምጽ ሰማች;; እግዚዘብሄር እንደዚህ የሚያምር ድምጽ ያለውን አሳየኝ ብላ እግዚአብሄርን ተማጸነች፡፡

እግዚአብሄር አህያ እና ጅብ እንደማይስማሙ ስለሚያውቅ አህያዋ ከጅብ ጋር መገናኘት እንደሌለባት ነገራት፡፡ አህያም አንቢ ብላ ለማየት ጓጓች፡፡ እግዚአብሄርም ጅቡን ከሰማይ ላይ አወረደ፡፡ አህያ እና ጅብ እንዲገናኙ ደግሞ እግዚአብሄር ምክንያት አድርጎ የጅብን ልጅ ገደላት፡፡ አህያም ከልጆቿ ጋር የጅብ ለቅሶ ቤት ሄዱ፡፡ ስትጮሁ ቅርብ ነው ድምጻችሁ ለሊት ስትሄዱ እሾኽ አይወጋችሁም፡፡ ጥቁር ብትበሉም ነጭ ነው ሰገራችሁ ትናንት ሰላም ነበራችሁ ዛሬ ልጃችሁን ምን አገኘባችሁ፣ እያሉ አለቀሱ፡፡ አህያዋ አልቅሳ ስትጨረስ፤ ልትሰናበት ወደ ውስጥ ስትገባ ጅቡ በሩን ዘጋባት የአህያዋ ውርንጭላዎች ፈርተው ሲሸሹ፣ጅብ ምነው ሳትሰናበቱኝ ትሄዳለችሁ እንዴ፤ብሎ ሲከተላቸው እነርሱም በደንብ ስለሮጡ ሊደርስባቸው

አልቻለም፡፡ በዚያዉ ሄዱ፡፡ የእናንተም መጨረሻ የኔው ነውና አላቸው፤ ጅቡ ተመልሶ ይበላል፡፡

## የምዕራፍ ሦስት መጠቃለያ

- ስነ-ቃልን ወደ ትያትር ተውኔት መቀየር ይችላል፡፡
- በስነ-ቃል ታሪክ ውስጥ የሚገኙ ተሳታፊዎች እንደ ተውኔት ገጸ-ባህሪ መውስዶ ይቻላል፡፡
- የስነ-ቃል ትረካ የትያትር ተውኔት ሀሳብ በመሆን ያገለግላል፡፡
- ተረት ተረት በአፍ ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፍ ሲሆን ስነ-ሥዕል ደግሞ ወረቀትና ሌሎች ነገሮችን በመጠቀም የሚሰራ ነው፡፡
- ተረት ተረት ለመግለጽ የሚጠቅሙት ስነ-ጥበባት፡- ፎቶ፣የስዕል መግለጨ፣ የድምጽ እና የምስል መቅጃ፣ሙዚቃ እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡
- የስዕል መግለጫ ማለት አንድ ጽሁፍ በስዕል ተደግፎ በቂ መልዕክት እንዲያስተላልፍ ማድረግ ማለት ነው፡፡
- የሥዕል መግለጫ ጥበብ የሰውን ልጅ ኑሮ አመቺ ከምያደርጉት ውስጥ አንዱ ነው፡፡
- የባህል የሙዚቃ መሳሪያዎች የተለያዩ አይነት፣መልእክት እና ቅርጻ ቅርጽ ያላቸው እና በተለያየ ሁኔታ የሚጫወቱ ናቸው፡፡
- ውዝዋዜ ሃሳባችን ስሜታችን እና ልምዳችን በጥበብ በእንቅስቃሴ የምንገልጸው ነው፡፡

## የምዕራፍ ሦስት መልመጃ

ከዚህ በታች ያሉትን ዓረፍተ ነገሮችን ትክክል ከሆኑ እውነት ትክክል ካልሆኑ ደግሞ ሀሰት በማለት በጹሁፍ መልሱ፡፡

1. ስነ-ቃልን ወደ ትያትር ተውኔት መቀየር ይቻላል፡፡
2. በስነ-ቃል ታሪክ ውስጥ የሚገኙ ተሳታፊዎች እንደ የተውኔት ጹሁፍ ተዋንያን ይወሰዳሉ፡፡
3. የስነ-ቃል ትረካ የትያትር እነ የፊልም ተውኔት ጹሁፍ ሀሳብ ሊሆን ይችላል፡፡
4. ተረት ተረት ታሪክን፣ባህልን፣እሴትን፣ጀግንነትን እና እምነትን ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚያስተላልፍ ነው፡፡
5. ተረት ተረት በስነ ስእል በወረቀት ላይ መስራት ይቻላል፡፡
6. ሥነ-ጥበባት በአጭሪ ጊዜ ውስጥ ብዙ መልዕክት ማስተላለፍ ይችላሉ፡፡
7. ፎቶ ተረት ተረትን ለመናገር ይረዳል፡፡
8. በስዕል የተደገፈ ገለጻ ፎቶ ይባላል፡፡
9. የስዕል በግለጫ ጥበብ የሰው ልጅን ኑሮ አመቺ ከሚያደርጉት ነገሮች ውስጥ አንዱ ነው፡፡

# ምዕራፍ 4

# የስነ-ጥበባት መስህብ

**የዚህ ምዕራፍ ትምህርት ውጤት፡**

**ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎናጸፉት የሚገባቸው የመማር ብቃት**

**ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች ፡-**

- የማህበረሰቡ ብርቅዬ እውቀትና እሴቶችን ወደ ትያትር ሙያ ቀይረህ/ሽ ታደንቃለህ/ሽ ::
- የስነ ምልከታ ብርቅዬ እውቀትን በማህበረሰቡ ውስጥ በመለየት ታደንቃለህ/ሽ ::
- በስነ-ምልከታ ጥቅም በብርቅዬ እውቀት ውስጥ ምን ያህል እነደሆነ ትገመግማለህ/ትገመግሚያለሽ ::
- የማህበረሰቡ ብርቅዬ እውቀትን በሙዚቃ በማድነቅ ታቀርባለህ/ሽ ::

## መግቢያ

ብርቅዬ እውቀት ማለት አንድ ማህበረሰብ አንድን ነገር ልማድ ወይም ባህሉን አድርጎ ከትውልድ ወደ ትውልድ እያስተላለፈ የነበረው እና ያለው የማህበረሰብ ብቻ የሆነ ሌላ ቦታ የማይገኝ እሴት ማለት ነው፡፡ ይህ ብርቅዬ እውቀት የስራ ባህል የሰርግ አሰራረግ ባህል የአብሮ መኖር እና የአኗኗር ደምብ እና ስርዓትን ያካተተ ነው፡፡

## 4.1 የማህበረሰብን ብርቅዬ እውቀትን በትያትር ሙያ ማድነቅ

**ቢያንስ ተማሪዎች ሊጎናጸፉት የሚጠበቅባቸው የትምህርት ክህሎቶች፡-**

**በዚህ ርዕስ መጨረሻ ላይ፡-**

- የማህበረሰቡ ብርቅዬ እውቀት በትያትር ሙያ ታደንቃለህ/ሽ

የማህበረሰብ ብርቅዬ እውቀት የሚባሉት ብዙ ናቸው፡፡ እነርሱም መጠለያ የማዘጋጅት፣ምግብ ማብሰ፣አውሬን ማደን፣ውሃ መዋኘት፣የምግብ ዝግጅት ቁሶችን መስራት፣ሰላምን እና የማህበረሰቡን ፍቅር የሚጠብቁበት መኖር እና የመሳሰሉነትን እንደ ምሳሌ ማንሳት ይቻላል፡፡ ምዕራፍ አንድ ላይ ትያትር ስለ ሰው ልጅ ኑሮ እና የአኗኗር ዘይቤ እንደሆነ እንደተማርክ አሁን ደግሞ የማህበረሰብን ብርቅዬ እውቀትን ማድነቅ እና በሱ እየተማረክ ማስተማር እንደምትችል ትማራለህ፡፡ በኦሮሞ ህዝብ ብርቅዬ እውቀት ላይ ስትሰራ ትያትር አንድ ስለ "ጉማ አራርሱ" የሚባል ብርቅዬ እውቀት እንስተን እንደ ምሳሌ እንየው፡፡ ሁለት ሽማግሌዎች እርስ በእርሳችን ሲመካከሩ ይታያሉ፡፡ ከነሱ ራቅ ብሎ ብዙ ሰዎች መርሃ ግብሩን ለመሳታፍ ስር ላይ ተቀምጠ ይታያል፡፡ ሌሎች የመሃላ ማስፈጸሚያ ቁሶችም ከነሱ ፊት ለፊት ተቀምጠው ይታያሉ፡፡

ሰዎች፡- አራራ ያ ላሚኮ

ሎሲ ማላ ኑ ሂሚሜ (2)

ሎሌን ሉጋመሜ

አራራ ያለሚኮ ሎስ

ማላ ኑ ሂሚሜ

ካላቻፍ ጫጩን ባዬ

አራራ ያ ላሚኮ

ሎሲ ማላ ኑ ሂሚሜ

ቤራ ካላሌፍ ዱርባ ጉዱሩን ባዬ

አራራ ያ ለሚኮ

ሎሲ ማላ ኑ ሂሚሜ

ጃርሳ ጉላ ፊ ቤራ ጭፍሬን ባዬ

አራራ ያ ለሚኮ

ሎሲ ማላ ኑ ሂሚሜ

ዱጋ ፍ ጉማ ኬኑ ዱፍኔ

አራራ ያለሚኮ

ሎሲ መለኑ ሂሚሜ

ናጋ ቡሱፍ ወራናቱ ጪሴ

አራራ የለሚኮ

ሎሲ ማላ ኑ ሂሚሜ

(ዜማው ይቀየራላ)

ጫጩቱ ዳባታ ካላቻቱ ዳባታ

አደራ ዋቅ !

ፋርዳቱ ለጋማን ዳባታ

አዳራ ዋቅ !

አዳራ ዋቅ !

አዳራ ሳልጋን ቦራና

አዳራ ኦዳ ናቤ

አዳራ ማዳ ወላቡ

ጉያ ሳገል ሳጋድኔ......

**አቶ ጀቤሳ ፡** (በስግደት ላይ የነበሩትን እጅ በማውጣት ያስቆማሉ፡፡) አቶ ጃለታ የሰው ነብስ በእጃችን ጠፍቷል፡፡ እነዚህ ሰዎችም ጉማ እናወጣለን ብለው፣ መስገድ ከጀመሩ ዘጠኝ ቀን አልፏል፡፡ ሰውን

የገደለው ልጅም “በ ቡሊ በደም እጄ ተጨማልቋል፣ በደሌን እጠቡልኝ እና አፅዱልኝ፣ ነብሴንም አድኑ” ብሎ እጁን ለኛ ከሰጠ ቆይቷል፡፡ ከዛ ጀምረዉ በሰንሰለት ታስረዉ፣ ፀጉሩ ተንጨባሮ፣ ልብሱም ቆሽሾበታል፡፡ ስለዚህ በግራና በቀኝ፣በኋላ እና በፊት አይተን፣ መምህሬን ውሸትን አርቀን፣ሚዛናችን አስተካክለን በህጋችን መሠረት ውሳኔ መስጠት አለብን፡፡

**አቶ ጃለታ፡** አስቀድመን ጠደቻ ተቀምጠናል፡፡ ያጠፋውን እና የተበደለውን ለይተናል፡፡ አጥንተን፣አስጠንተን እውነትን አግኝተናል፡፡ ዋቅ ደንጉሌን እንዳልገደለ አውቀናል፡፡ቢሆንም ግን አሁን ያለውን እውነት እናጣራለን፡፡

**አቶ ጀቤሳ፡** አቶ ጃለታ ኑርልን፣ትክክል ነገር ነው ያወራኸው፡፡ ወደ ህዝቡ ስብስብ ወጥቼ ስብሰባ /ጠደቻ/ ተቀምጠን ውሳኔ ከመስጠት በፊት እውነትን ማረጋገጥ እና ምስክርን መጥራት ስራችን ነው፡፡ ስለዚህ ዋቆም ይሆን የህዝብ ተወካይም እጁ ላይ የሰው ደም እንደሌለ በህዝቡ ፊት መማል አለባቹ፡፡ ይህ የህዝባችን ጥንታዊ ባህል ነው(ጦር፣ ቢላ፣ድንጋይ፣አመድ፣ጠመንጃ፣ጥይት፣እሳት፣ውሃ እና ሌሎች በህዝቡ ፊት ለፊት ቀርቧል)፡፡

**አቶ ጃለታ፡-** ጥሩ ነው እንዲቀርቡ አድርጉ (ዳባ እና ዋቆ ትንሽ ከሽማግሌዎቹ ርቀው ይቆማሉ) ፡፡

**አቶ ጀቤሳ፡-** ዳባ፣ ንግግርህ ቋሚነት ያለው ይሁን፡፡ እንግዲህ ምህረትን እና ሰላምን ለማውረድ ባህላችን መከበር አለበት፡፡ የአገር ሽማግሌ ያላቸውን መውሰድ አለባችሁ፡፡ የለሚ እናት የት እንደሄደች ምን እንደሆነች ዋቆ ባረሱ ይንገረን፡፡ የማያውቅም ከሆነ አላውቅም ብለዉ ይማልልን፡፡

**ዋቆ፡** (ከተቀመጠበት ቦታ ብድግ ብለዉ እየተነሳ) ጅራፍ በራሱ ገርፎ በራሱ ይጮሃል አሉ፡፡ የእናቴ ልጅ ከአንድ ማህጸን አብረን

የወጣነውን ገደልኩት ብዬ ልማልላችሁ፤ እኔ የወንድሜን የደም ዋጋ ላስከፍል እፋለማለሁ እንጂ… ( ያዙኝ ልቀቁኝ ብሎ ይንገዳገዳል) ፡፡

**አቶ ጀቤሳ፡** ህዝቡም የወንድምህን የደም ዋጋ (ጉማ) ለማግኘት ነው እየሰገደ ያለው ነገርን አታጠማዝ፣አትከራከረን ተከራክረህ የትም አትደርስም፡፡ የኦሮሞ ህዝብ ህግ ጥሰህ የትም አትደረስም፡፡ የአረጁ ሽማግሌዎችን ንቀህ አታመልጥም፡፡ ሽማግሌ ሲረግም ያጠፋል፡፡ ሲመርቅ ያኖራል፡፡ ሽማግሌዎች ጫጩ እና ከለቻን ይዘው ከህዝቡ ጋር ሆነው እንታረቅ ብለው እየጠየቁህ ነው፡፡ አንተ ምን መሆንህ ነው፡፡ ከኛ ህግ መሸሽ እራስህን መሸሽ ነው፡፡ የምንልህን እንቢ ካልክ በእርግማን ትያዛለህ፡፡ በአባቶችህ ደንብና ወግ ትያዛለህ፡፡ ተራምደህ አትርቅም፡፡ ዘለህ ወንዝ አትሻገረም፡፡ ፍግም ትላለህ፡፡

**ዋቆ**፡ (ከአይኑ እንባ እያፈሰሰ) ከእናንተ ሸሸቼ የት አባቴ እደርሳለሁ፡፡

**አቶ ጀቤሳ** ፡ አሁን መንገዱን ይዘዋል፡፡ ወደዚህ ጠጋ በል (የማህላው ቁሶች ወደ አለበት ቦታ ይጠጋል) ፡፡

**አቶ ጀቤሳ፡** እንካ ይህንን ጦር ነክሰህ "የዳንጉሌን ነብስ አጥፍቼ ደብቄ እንደሆነ በዚህ ጦር ነብሴ ጠፍቶ ይደበቅ" በል፡፡

**ዋቆ**፡ ከገደልኳት፣ ገድዬ ከደበቅኳት ነብሴ ትደበቅ፡፡

**አቶ ጀቤሳ፡** ገድዬ ከደበቅኳት ይሄ ጦር እና ጥይት አይጣኝ በል፡፡

ዋቆ፡ አይጣኝ ፡፡

**አቶ ጀቤሳ፡** ገድዬ ከደበቅኳት ይሄ ድንጋይ ነው፣የህሄንን ድንጋይ የሚያክል እጢ ጭንቅላቴ ውስጥ ያስቀምጥ በል፡፡

**ዋቆ**፡ ጭንቅላቴ ውስጥ ያስቀምጥ፡፡

**አቶ ጀቤሳ፡** ይበቃሃል ቁጭ በል ዋቆ፣ህዝባችን ሆይ ሀገራች ሆይ ዋቆ

ደንጉሌን እንደልገደለ፤ በእናንተ ፊት አስምለን አረገግጠናል፡፡ እንግዲህ አሁን ጉማን ለማውጣት ዘጠኝ ቀን ለምናችኋል፡፡ የደም ዋጋውም ተወስኗል፡፡ እርቅ ለማውረድ ከሁለቱም ወገኖች ያመለከታችሁ ወደ ፊት ይምጡ(የማሃላ ቁሶች ወደ አለበት ቦታ አቶ ገልገሎ ይመጣል) የጦሩን ጫፍ ወደ መሬት ዝቅ አርጋችሁ አቁሙ፡፡ ጦሩን ከእናንተ ወደ መሬት አዙሩ፡፡ እውነታችሁ እና የደማችሁ ዋጋ ይገኛል፡፡ የተበደላችሁት በደልም ይገኛል፡፡ አትጎዳዱ፡፡ በእውነት ብቻ ፍረዱ፡፡ እናንተም ማሉልን፡፡ (የጉማ ማውጣት ስረአቱን የሚያስፈፅሙትን ሰዎች በማስማል ይጀመራል፡፡ ቀለ መሃላውን ሲፈጽሙ በሽማግሌዎች ፊት ይንበረከካሉ፡፡)

**አቶ ጀቤሳ** ፡ ጉማን ታወጣለህ፡፡

**አቶ ገልገሎ፡** አዎ አወጣለሁ፡፡

**አቶ ጀቤሳ፡** የቦረናን ጉማ ስርአት አታጎድልም ፡፡

**አቶ ገልገሎ፡** አላጎድልም፡፡

**አቶ ጀቤሳ፡** በትላንቱ ምሽት አባ ቦኩ ጋር መጥተህ ቃል የገባኸውን ትፈጽማለህ? ጉማ እንደ አግባቡ ትከፍላለህ?

**አቶ ገልገሎ፡** አዎ እከፍላለሁ፡፡

**አቶ ጀቤሳ፡** እውነትን ካጎደልኩም፣ከቀየርኩም የጉማ እዳ ቤቴ ይግባብኝ በል፡፡

**አቶ ገልገሎ፡** ቤቴ ይግባብኝ፡፡

**አቶ ጀቤሳ፡** እውነትን እውነት ታወጣለህ?

**አቶ ገልገሎ፡** አወጣለሁ፡፡

**አቶ ጀቤሳ፡** ጉማን ከአጎደልኩ እውነት ከቀየርኩ የጉማ እዳ ይግባብኝ በል፡፡

**አቶ ገልገሎ፡** ይግባብኝ፡፡

**አቶ ጀቤሳ፡** የማይታረም ጠማማ ልጅ፣ የጉማ እዳ ታጥቦ የማይነጻው፣

የሰላሌ ሸለቆ የባሌ ገደል ገብተህ የማትወጣውን፣የዘጠኝ ቦኩዎች ርግማን፡- የቦኩ ጡሌ፣የቦኩ ጭቱ፣የቦኩ ወሊሶ፣የኦዳ ነቤ፣የአምስቱ ቦኩዎች እርግማን ተሰብስቦ ወደ ቤቱ ይግባ በል፡፡

**አቶ ገልገሎ፡** ወደ ቤቴ ይግባ፡፡

**አቶ ጀቤሳ፡** ወንድ ልጅ አይወለድልኝ

**አቶ ገልገሎ፡** አይወለድልኝ፡፡

**አቶ ጀቤሳ፡** ሴት ልጅ አትወለድልኝ

**አቶ ገልገሎ፡** አትወለድልኝ፡፡

**አቶ ጀቤሳ፡** ከእኔ የተፈጠረ በቤቴ አይወለድ፡፡

**አቶ ገልገሎ፡** በቤቴ አይወለድ፡፡

**አቶ ጀቤሳ፡** ቤቴን ቀየዬን ለም እና ንብረቴን ይውረሰኝ፡፡

**አቶ ገልገሎ፡** ይውረሰኝ፡፡

**አቶ ጀቤሳ፡** ጉማው ይግባብኝ፡፡

**አቶ ገልገሎ ፡** ይግባብኝ፡፡

**አቶ ጀቤሳ፡** ቅም አያትን፣ቅም ቅም አያትን፣ቅድመ አያትን ቆጥሮ በአዳ በቤቴ ይግባብኝ፡፡

**አቶ ገልገሎ፡** በቤቴ ይግባብኝ፡፡

**አቶ ጀቤሳ፡** ስለዚህ ጉማን እና እውነትን አላጎልም፡፡

**አቶ ገልገሎ፡** አዎ ስለዚህ አላጎልም፡፡

**አቶ ጀቤሳ፡** እውነትን አወጣለሁ እንጂ እጄን እታጠባለሁ እንጂ ታጥቤ ወደ ጎሳዬ እቀላቀላለሁ እንጂ ወደ ኋላ አልቀርም፡፡

**አቶ ገልገሎ፡** ዞር ብዬ ወደ ኋላ አልቀርም፡፡

**አቶ ጀቤሳ፡** ጉማውን የሚታወጡ እነዴ ቆይሉኝ፡፡ መሀላቸው ይደርሳል፡፡ ጉማ የሚትቀበሉ ደግሞ ወደ እዚህ ኑ ፡፡ እውነትን ትቀበለዋለህ እንጂ ጉማህን ትቀበለዋለህ እንጂ በደለህን ለህዝቡ

ትነግረዋለህ እንጂ ሌላ በደል አታስብም፡፡

**ዋቆ**፡ አዎ ሌላ በደል አላስብም፡፡

**አቶ ጀቤሳ**፡ የድሮ የቦረና ጉማ አሰጣጥ ጦር ተጎንቦሶ እርቅ የሚያወርዱበትን ባህል ትቀበለዋለህ፡፡ በውሳኔአችን ትገባለህ፡፡

**ዋቆ**፡ አዎ እገባለሁ፡፡

**አቶ ጀቤሳ**፡ ከዚህ ሁሉ የምትወጣ ከሆነ የጉማ ሰእርዓት ውርጅብኛ አይጣህ፡፡

**ዋቆ**፡ አይጣኝ፡፡

**አቶ ጀቤሳ**፡ ስትዘራ ዘር አይብቀልልህ

**ዋቆ**፡ አይብቀልልኝ፡፡

**አቶ ጀቤሳ**፡ ሲወለድ ልጅ አይደግልህ፡፤

**ዋቆ** ፡ አይደግልኝ፡፡

**አቶ ጀቤሳ**፡ አባትን እገላለሁ ልጅን እገላለው የምትል ከሆነ ይህ ጦር ነው፤ይህ ጦር አይጣህ፡፡

**ዋቆ**፡ አዎ አይጣኝ፡፡

**አቶ ጀቤሳ**፡ ገድሎ የነፍስን ዋጋ የማይሰጥ ያለ ቁምጥና የሚቆራርጥ ያለ እከክ የሚያሳክክ ይህ ሁሉ እርግማን ጦር አውጥቶ ይምጣብህ፡፡

**ዋቆ**፡ አዎ ይምጣብኝ፡፡

**አቶ ጀቤሳ**፡ በጓሮ ገብቶ ጓዳህ ይቀመጥ፡፡

**ዋቆ**፡ አዎ ጓዳዬ ይቀመጥ፡፡

**አቶ ጀቤሳ**፡ የአያቶች ቁስል ሆኖ ጓዳህ ይቀመጥ፡፡

**ዋቆ**፡ ይቀመጥ፡፡

**አቶ ጀቤሳ**፡ ከአልጋህ አይንቀሳቀስ

**ዋቆ**፡ አዎ ከአልጋዬ አይንቀሳቀስ፡፡

**አቶ ጀቤሳ**፡ እንግዲህ በሁለቱም ወገኖች በኩል አስምለናል፡፡ ይህ እርግማን ሙሉ ነው፡፡

ሞልቶ አይጎደልም፤

ወደ ኋላ አይመለስም፤

ረኸሮሙ አያጥረም ፤

አጠር ያለም አይቀጥንም፤

ይህ የጉማ ስርአትና እርግማኑ ፤

የዱሮ አባቶቻችን ጦር ነው፡፡

የጥንቱ ኦሮሞዎች ያስቀመጡት ነው፡፡

ከቅድመ አያቶች እና ከአያቶች እያወረስን ያመጠነው የባህላችን እሴት ነው፡፡ የማይፈርስ ነው አይረስምም፡፡ ከዚህ በኋላ

ጉማ የምትከፍሉም ጉማ የሚትቀበሉም፡-

አንድ ገበያ አብራችሁ ትነግዳለችሁ፤

እርስ በእርሳችሁ ትጋባላችሁ ፤

እርስ በእርሳችሁ ሚዜ ትሆናላችሁ፤

አብራችሁ ትበላላችሁ፣ትጠጣላችሁ ኑ! በታረደው እንስሳ ሆድ ውስጥ ተጨባበጡ እና ከደም ነጻ ይሁኑ፡፡ (የታረደውን እንስሳ ላምም፤ በግም ሊሆን ይችላል፡፡ ፋፋ ከፍ ብለዉ ሰንሰለቱ ይፈታለታል፡፡ ዋቆ እና ዳባ በአንድ በኩል ፋፋ እና ገልገሎ ደግሞ በሌላኛው በኩል ይቆማሉ፡፡ በታረደው በግ ሆድ ውስጥ እጃቸውን አስገብተው ይጨባበጣሉ፡፡ ማር ይጎራረሳሉ፡፡)

አቶ ጀቤሳ፡ ወተት ጠጡ፤ ለእርስ በእርሳችሁም ወተት ስጡ፡፡ እንግዲህ እርስ በእርሳችሁም ማር ሁኑ፡፡

(አቶ ጀቤሳ እርቅ ካወረዱ በኋላ ደመሺ ልጁ ዳንጉሌን ይዛ እጁን ዘርጋታ ከመጋረጃ ጀርባ ትወጣለች፡፡)

ደመሺ፡ ይሄው ዳንጉሌ ልጄ ብትገኝም እኔም እጄ ረክሷል፡፡ በቦንቱ ደም አእምሮዬ ታሞ ውስጡ በስብሷል፡፡ ህዝቤ ሆይ በሰው ልጅ ደም የቆሸሸውን እጄን አጽዱልኝ፡፡ ጉማ አውጡልኝ እና ከበደል ነጻ

አድርጉኝ፡፡

ከዚህ በላይ በተቀመጠው ምሳሌ የምንማረው ወይም ተማሪ መማር የሚችለው ከኦሮሞ ህዝብ ሀገር በቀል እውቀቶች አንዱ የጉማ አወጣጥ እና እርቅ ማስፈጸም ባህል ራሱን የቻለ ሂደት ያለውና የሰውን ነብስ ያጠፋ ሰው በሀገር ሽማግሌዎች አማካኝነት የበደለውን እና የተበደለውን ወገን እንደ ኦሮሞ ህዝብ እሴት የሚታረቁበት ሂደት መሆኑ ነው፡፡

በዚህ ጉማ አወጣጥ ህግ ውስጥ የኦሮሞ ህዝብ የበደለውን እና የተበደለውን አስታርቆ ሰላምና ማህበራዊ ፍቅርን እንዴት ሲጠብቁ እንደነበረ እንማራለን፡፡ ሀገር በቀል እውቀትን በቲያትር ማድነቅ ውስጥ የምንማረው ትልቁ ነገር አገር በቀል እውቀት ህብረተሰብ ውስጥ ያለው ፋይዳ ነው፡፡ በተጨማሪም የህዝባችን ሀገር በቀል እውቀትን ወደ ትያትር ጥበብ በመቀየር ማህበረሰባችን እንድናስተምር ይረዳናል፡፡

**ተግባር**

ከማህበረሰቡ ሀገር በቀል ውስጥ አንዱን መርጣችሁ ወደ ትያትር ቀይራችሁ አሳዩ፡፡

## 4.2. የማህበረሰቡን ሀገር በቀል እውቀት በስነ-ጥበብ ማድነቅ

ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎናጸፉ የሚገባቸው የመማር ብቃት፡-

ከዚህ ትምህርት ርዕስ በኋላ ተማሪዎች፡-

- በማህበረሰቡ ውስጥ ሲሰራ የቆየ ሀገር በቀል እውቀት ትገልጻላሁ፡፡
- ሀገር በቀል እውቀት ምን ምን እንደሚያካትት ትናገራለችሁ፡፡
- ንድፍ ለማህበረሰቡ ሀገር በቀል እውቀት ያለውን ጥቅም ትገልጻላችሁ፡፡

**ውይይት 1**

1. እናንተ የሚትኖሩበት ማህበረሰብ በብዛት የሚጠቀምበት እና የሚታወቅበት እውቀት እና ሙያ (ጥበብ) ለይታችሁ ታውቃላችሁ ወይ?
2. የምትኖሩበት አካባቢ የማህበረሰቡ እውቀት እና ሙያ አይነቶች በመለየት በቡድን ተወያዩና ለክፍላችሁ አቅርቡ፡፡

ሀገር በቀል እውቀት፣የተወሰነ ማህበረሰብ የፈጠራ እውቀት ማለት ነው፡፡ እሱም በማህበረሰቡ ውስጥ ለረጅም አመታት የቆየ እንደ የባህል መዳሃኒት፣ እርሻ፣ምግብ ማብሰል፣የአካባቢ እንክብካቤ እና ጥበቃ እንዲሁም ሌሎች ነገሮች አኗኗራቸውን ያከናውኑበት የነበረውን ሁሉ ያካትታል፡፡

ሀገር በቀል እውቀት በአሁኑ ጊዜ እድገት መያሚያመጡ እውቀት ወስጥ ትኩረት እያስገኘ ነው፡፡ ይህ እውቀት ሰላም ለማስፈን፣ ለኢኮኖሚ እድገት እና ለትምህርት እድገት ከፍተኛ ሚና አለው፡፡ ሀገር በቀል እውቀት ልዩ የተወሰነ ማህበረሰብ የባህል እውቀት ማለት ነው፡፡

ሀገር በቀል እውቀት ከዘመናዊ ሳይንሳዊ እውቀት ይለያል፡፡ የሀገር በቀል እውቀት ባህሪ በተወሰነ አካባቢ መወሰኑ እና በአንድ በህብረተሰብ ወይም ሀገር መወሰኑ ነው፡፡ ሀገር በቀል እውቀት የተለያዩ እውቀትን በውስጡ ይይዛል፡፡ እነሱም፡-የእርሻ እና የእርሻ መሳሪያ እውቀት፣የማዋለድ እውቀት፣የባህል መድሃኒት፣የእጅ ስራ፣የተፈጥሮ ሀብት እንክብካቤ እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡ አንድ አንድ ማህበረሰብን ከህይማኖት ጋር ያያይዛሉ፡፡ የማህበረሰቡን ፍላጎትም ይገልጻሉ፡፡ አንድ አንድ ማህበረሰብ በሀገር በቀል እውቀት የሆኑት ነገርች ላይ ኑሮአቸውን መስረተው ይኖራሉ፡፡ ለምሳሌ፡- ተረት እና ምሳሌ፣የተለያዩ ልምዶች፣የተፈጥሮ እንክብካቤ ጋር ተያይዞ ለዛ ማህበረሰብ መልዕክት እና እውቀት

ለማስተላለፍ ሚና አለው፡፡ በማህበረሰባችን ውስጥ ከሚታወቀው ሀገር በቀል እውቀቶች ውስጥ አንዱ የእጅ ስራ ነው፡፡

**ውይይት 2**

ሀ. የእጅ ስራ ማለት ምን ማለት ነው?

ለ. እጅ ስራ የሆኑት ነገሮች ለማህበረሰቡ ምን ጥቅም አላቸው ብላችሁ ታስባላችሁ ? በቡድን ተወያዩ እና ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ?

የእጅ ስራ ሙያ ሀገር በቀል እውቀት ሆኖ፤ በማህበረሰብ ውስጥ የሚገኝ እና ባህላዊ ዘዴ ብቻ በመጠቀም የተለያዩ ነገሮች የሚሰሩበት ነው፡፡ ብዙዎቹ የእጅ ስራ የሚሰሩ ሰዎች በተፈጥሮ ከሚገኙ ነገሮች ውስጥ በብዛት ሀገር በቀል እውቀት ተጠቅመው የሚሰሩ ናቸው፡፡ የእጅ ስራ የሀገር በቀል እውቀት እነደ ባህል፣እሴት፣ማንነት እና ምንነት የመሳሰሉትን የሚገልጽበት ነው፡፡ ይህ እጅ ስራ በሚሰራበት ዘዴ እና ከሚሰራባቸው ቁሳቁሶች በተለያየ መንገዶች ይከፈላል፡፡ ከእነዚህም ጥቂቶቹ፡-

- የሸክላ ስራ ሙያ
- የሽመና ስራ ሙያ
- የቆዳ ውጤቶች ስራ ሙያ
- የብረታ ብረት ስራ ሙያ
- የእንጨት ስራ ሙያ
- ስፌት መስፋት ስራ ሙያ
- የወርቅ እና የብር ስራ ሙያ
- የዘንቢል ስራ ሙያ (የቅርጫት)

## 4.2.1 የሸክላ ስራ ሙያ

**ውይይት 3**

እንደ ምጣድ፣ማሰሮ፣ጀበና፣ጋን እና የመሳሰሉት ቁሳቁሶች እናቶቻችን እንደ ገዙ ሳይጠቀሙበት ለምን በእሳት እንደሚያሚሹ በቡድን ተወያይታችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡

የሸክላ ስራ ሙያ ከጥንት ጀምሮ በተለያየ ቦታ ሲሰራ የቆየ እና አሁንም እየተሰራ ያለ ነው፡፡ የሸክላ ስራ ሙያ ከሸክላ አፈር የሚሰራ ነው፡፡ የሸክላ አፈር እንደ ሌሎች ማእድናት በመሬት ውስጥ ከሚገኙ ውስጥ አንዱ ነው፡፡ በሸክላ አፈር ውስጥ የሚገኘው ማእደን በእሳት ሲቃጠል የመጨረማመት ባህሪ አለው፡፡ ስለዚህ እናቶቻችን ከመጠቀማቸው በፊት በእሳት የሚያቃጥሉት፡፡ ምክንያቱም በእሳት ሳይቀጠል (ሳይሚሽ) ከተጠቀሙ በቀላሉ ሊሰበር ስለሚችል ነው፡፡



ስዕል 1. የሸክላ ሰሪ ሰው የሚያሳይ ስዕል፡፡



ስዕል 2. የሸክላ ስራ ውጤት የሆኑትን ቁሳቁሶች በእሳት ሲያቃጥሉ የሚያሳይ ስዕል፡፡

፤ሳይሚሸ ከተጠቀሙበት እንደሚሰበር ስለሚያውቁ ከድሮ ጀምሮ ማንም ሳይነግራቸው ሲጠቀሙበት የቆየ ነው፡፡

**ልምምድ 1**

ከሸክላ አፈር የጀበና፣የምጣድ፣ጽዋ፣የማሰሮ፣እንስራ ከመሳሰሉት ቅርጻ ቅርጽ ውስጥ አንዱን መርጣችሁ ስሩ፡፡

**4.2.2የሽመና ስራ ሙያ**

**ውይይት 4**

በአካባቢያችሁ የሽመና ስራ የሚሰሩ ሰዎች አሉ ወይ? ያ ከሆነ የሚሰሩት ልብስ ምንድን ነው? ምን ዓይነት ልብስ እንደሚሰሩ እና እንዴት እንደሚሰሩ በቡድን ተከፋፍላችሁ ተወያዩ የተወያያችሁበትን ለክፍል አቅርቡ፡፡

የሰው ልጅ ልብስን ሰርቶ ከመልበሱ በፊት በድሮ ግዜ በጣም ሰፊ የሆነ ቅጠል በመቁረጥ በላዩ ላይ ያገለድም ነበር፡፡ ከግዜ በኋላ እውቀታቸው እየጨመረ ሲሄድ ደግሞ አራዊቶችን በማደን ቆዳቸውን እየገፈፉ ይጠቀሙበት ጀመሩ፡፡ ይሁን እንጂ ሀሳባቸው እና የፈጠራ ችሎታቸው

በዚህ አላዎመም ነበር፡፡ እንደሚመቻቸው ልብስ እየሰሩ መልበስ ጀመሩ፡፡

ልብስም ከተለያየ ነገር ላይ መስራት ጀመሩ፡፡ ለምሳሌ፡- ጥጥ፣ክር እና ከመሳሰሉት ላይ ይሰራሉ፡፡ ከጥጥ የሚሰራው እንደ ቡሉኮ፣ጋቢ፣ነጠላ እና የተለያዩ የባህል አልባሳትን የሚለብሱ እና የሚታሰሩ ናቸው፡፡ ክከር የሚሰቱ ደግሞ እንደ አልጋ ልብስ የሚሠራበት ሁኔታ እና ለውበት የሚጠቅሙ ነገሮች ታሪክ፣እሴትን፣ባህልን፣ምንነትን፣ማንነትን የአንድን ብሄር የሚገልጽ ነው፡፡ ለምሳሌ የኦሮሞ ባህል ልብስ ከሌላ ብሄር ልብስ ልዩነት አለው፡፡



ስዕል 3 የሽመና ስራ የሚሠራ ሰው የሚያሳይ ስዕል ፡፡

## ውይይት 5

1. በካባቢያችሁ በወንዶች እና በሴቶች የሚለበሱ እና የሚታሰሩ የባህል ልብሶች ምን እንደሆነ በቡድን ተወያዩ እና ለክፍል ጓደኞቻችሁ ግለጹ፡፡
2. እነዚህ ልበሶች በምን ግዜ እንደሚለበሱ፣እንደሚታሰሩ እና እንደሚያዙ እንዲሁም ለምን ምክንያት እንደሚጠቀሙ እና ለይታችሁ በቡድን ከተወያያችሁ በኋላ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡

## 4.2.3 የቆዳ ውጤት ስራ ሙያ

ከቆዳ የተለያዩ ነገሮች የሚሰሩ ሰዎች በአካባቢያችሁ አሉ? በአካባቢያችሁ ካሉ ከቆዳ ላይ ምን ምን እነደሚሰሩ በቡድን ተወያዩ?

የሰው ልጅ ከድሮ ዘመን ጀምሮ በቆዳ ከተለያዩ ነገሮችን እየሰራ ይጠቀምበት እና አሁንም እየተጠቀመበት እንደላ ይታወቃል፡፡ በቆዳ ላይ የተለያዩ ዲዛይን ሲሰሩ የተለያዩ እቃዎችን ሲያሳምሩበት ቆይተዋል፡፡ ለምሳሌ፡- ለፈረስ ኮርቻ፣ትራስ፣አንሶላ አገልግል፣ስልቻ፣ድብዳብ፣ልብስ፣ቀበቶ፣ቦርሳ እና የመሳሰሉትን መጥቀስ ይቻላል፡፡ በድሮ ጊዜ ወረቀት ባልነበረበት ወቅት በወረቀት ፋንታ በተለያየ ቦታ እንደ የእምነት ቦታ፣በቤተ መንግስት እና በመሳሰሉት ውስጥ እነደ ወረቀት ሲጠቀሙበት ቆይተዋል፡፡ የክብር ዶ/ር ሎሬት አርቲስት ለማ ጉየም በቆዳ ላይ በቀለም ቅብ ሙያ ይታወቃሉ፡፡ ስለዚህ ቆዳ ለጽሁፍ ብቻ ሳይሆን ለቀለም ቅብም እያገለገለ የቆየ እና አሁንም በተለያየ ቦታ እያገለገለ ያለ ነው፡፡ በአጭሩም ቆዳ እየሰጠ ያለው ጥቅም ብዙ ነው፡፡ የቆዳ ሙያ በክር በሰው እጅ የሚሰራ ሆኖ ብዙ ዲዛይን በውስጡ ያለው ነው፡፡ የቆዳ ሙያ በሁለት መንገድ ይሰራል፡፡ እነርሱም፡-

1. ጸጉሩ ከላዩ ላይ ከተነሳ በኋላ፤ ዲዛይንን ተሰርቶበት ዲዛይኑ በቀለም ማስመር ፡፡
2. ጸጉር ባለው ቆዳ ላይ በተፈለገው ዲዛይን መስራት ፡፡



ስዕል 4 የክብር ዶ/ር ሎሬት አርቲስት ለማ ስዕል የሚያሳይ ፡፡

ሀ. የስነ ጥበብ እና እደ-ጥበብ መካከል ያለ ልዩነት

| | | |
|---|---|---|
| 1 | ስነ-ጥበብ | የእጅ ሙያ ጥበብ |
| 2 | ልዩ ስራ ሆኖ በብዛት በአንድ ሰው ብቻ የተገደበ ስለሆነ ለሌላ ሰው ደግሞ በድጋሚ አይሰራም | በሠዎች እጅ የሚሰሩ ቅርጻ ቅረጾች |
| 3 | የተፈጥሮ ተሰጥኦ ላይ በመመስረት | አንድ ሰው የሰራውን ስራ እንዴት እንደተሰራ የተሰራበትን ዘዴ ተከትሎ በድጋሚ መስራት ይችላል፡፡ |
| 4 | ሀሳብ ወይም ስሜት መግለጽ ላይ ያተኮረ ነው፡፡ | የፈጠራ ስራው በእጅ የተሰራ ነገር ላይ ያጠነጠነ ነው፡፡ |
| 5 | ስዕል ነው፡፡ | ዕቃ/ቁሳቁስ ነው |

## 4.3 ሀገር በቀል የማህበረሰብን እውቀትን በሙዚቃ ማድነቅ

**ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎናጸፉት የሚገባቸው የመማር ብቃት**

**ከዚህ ትምህርት ርዕስ በኋላ ተማሪዎች ፡-**

ማህበረሰቡ በሙዚቃ ላይ ያለውን ሀገር በቀል እውቀት ትገልጻላችሁ፡፡

በማህበረሰብ ልማድና እሴት ውስጥ ሀገር በቀል እውቀት ያለውን ሚና ትናገራላችሁ፡፡

ማህበረሰባችን በሙዚቃ ላይ ያለውን ሀገር በቀል እውቀት በሰፊው ትምህርት የሚያስተላልፍ ነው፡፡ ይህ ማለት በአኗኗራቸው ውስጥ አንድነትን ለመጠበቅ፣በስራ ላይ ለማበረታታት፣መቆረቆሩን በመግለጽ፣የህይማኖት ስርዓቱን ለማካሄድ እና የመሳሰሉትን ጉዳያቸውን የወጡበት ነበር፡፡ አሁንም እየተጠቀሙበት ይገኛሉ፡፡ ይህ ማለት በዘፈን መልክ መልዕክትን ማስተላለፍ፣በሙዚቃ መሳሪያ በመጠቀም ጉዳያቸውን መወጣት እና በውዝዋዜ ሀገር በቀል እውቀታቸውን ያንጸባርቃሉ፡፡ የሀገር በቀል እውቀቶች በሙዚቃ ከሚገለጹት ውስጥ ከዚህ በታች ያሉት ናቸው፡፡

### ሀ. የገዳ ስርዓት ሙዚቃ

የገዳ ስርዓት በኦሮሞ ማህበረሰብ ውስጥ ካሉት ስርዓቶች ወስጥ ታላቅ እና

የአስተዳደር ስርዓት ነው፡፡ የኦሮሞ ማህበረሰብ ከጥንት ዘመን አንስቶ በገዳ ስርዓት ሲተዳደር ስለነበር በገዳ ስርዓት ክብረ በዓል እና የስልጣን ርክክብ ቢያደርጉ የባህል ሙዚቃን እየጨፈሩ በሚያምር ስርዓት ይረካከባሉ፡፡ የገዳ ስርዓት ዘፈን በሁሉም የኦሮሞ ማህበረሰብ ጋር ታዋቂ የሆነ እና በአሁኑ ጊዜ ግን በኦሮሚያ ክልል ውስጥ በተወሰኑ ዞኖች ብቻ የሚታወቅ ነው፡፡ ፎሌ በገዳ ስርዓት ውስጥ ሦስተኛ ክፍል ሆኖ ድርሻው የማህበረሰቡን ሰላም መጠበቅ ነው፡፡ ፎሌ የሚባለው የቆይታ ግዜ ውስጥ ፎሌዎች የተለያየ ዘፈኖችን ለመጠቀም በማህበረሰብ

ውስጥ ጥሩ እነ ምግባር ያላቸውን እያሞገሱ፣መጥፎ ስነ ምግባር ያላቸውን እየነቀፉ እና የመሳሰሉትን በመጠቀም ለህብረተሰቡ መልዕክት ያስተላልፋሉ፡፡ በተጨማሪም የፎሌ አባላት የገዳ ስነ ስርዓት ሲያካሂድ እንዲሁም በተለያየ በአሎች ላይ አዲስ ዘፈን እያወጡ በፊት ያለውን እያሻሻሉ ለማህበረሱ በማቅረብ ውስጥ ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ፡

ይህ የማህበረሰቡ ሀገር በቀል ዕውቀት ከሙዚቃ ጋር ከሚያያዝ ውስጥ አንዱ ሆኖ ወጣቶች የገዳ ስርዓት ውስጥ አልፊው እተተካኩ የሚያልፉበት ነው፡፡ ወጣቶች የፎሌ ዘፈን ሊዘፍኑ መሚወጡበት ግዜ የሚጠቀሙበት የሙዚቃ መሳሪያዎች ጡርንባ እና ጋሻ በመምታት ነው፡፡

**ተግባር 2**

በአካባቢያችሁ የፎሌ ዘፈኖች እንዴት እንደሚጫወቱ እና እንዴት መልዕከት እንደሚያስተላልፉበት በቡድን በመወያየት ለክፍል አቅርቡ፡፡

ምሳሌ፡-

የፎሌ ዘፈን

ፎሊዮ ሮባ

ብርብርስ ደራሬ ያ ፎሌ ……ያ ፎሌ ብርብርስ ደራሬ …ያ ፎሌ

ብርብርስ ሳንጎታ ……………..ያ ፎሌ

ምረሚርስ ጋዳ ኬ ----------ያ ፎሌ

ገዳ አቦታ -----------------ያ ፎሌ

ፎልዮ ሮባ ብርብርስ

ደራሬ ያ ፎሌ………..ያ ፎሌ ቢረቢርሳ ደራሬ ያ ፎሌ

ኩኖ አበና ወያ ሮባ

ቢርቢርስ ደራሬ ያ ፎሌ………..ያ ፎሌ ቢርቢርስ ደራሬ ያ ፎሌ

ያ ፎሌ ቢርቢርስ ጀቦታ …………ያ ፎሌ

ሚርሚርስ ገራ ኬ ………………….ያ ፎሌ

ጀቢሲ ገዳ ኬ--------------- ያ ፎሌ

ገዳ አቦታ…………………… ያ ፎሌ

ኩኖ አካና ዋያ ሮባ

ብርብርሲ ዳራሬ ያ ፎሌ…………….ያ ፎሌ ብርብርስ ደራሬ ያ ፎሌ

…………………… ይቀጥላል………………….

**ለ. አቴቴ**

አቴቴ ከኦሮሞ የባህል ሙዚቃ ውስጥ አንዱ እና ሁል ጊዜ በሴቶች የሚጫወቱት

ሲሆን፤ ለተለያዩ ነገሮች የሚውል እና የተፈለገውን መልዕክት ለማስተላለፍ

በጥንቃቄ የሚውል ነው፡፡ አቴቴው የሚጠቅመው

ለሀይማኖት ጉዳይ፡-

- ዝናብ እጥረት ሲኖር ዝናብ እንዲዘንብ ለመለመን፤
- ዝናብ ሲበዛ እንዲቆም ለመለመን ፡፡

ለማህበረሰባዊ ጉዳይ፡-

ሴቶች በአራስነታቸው ከባላቸው ጥቃት ሲደርስባቸው ፤

አዛውንት ሴቶች ሲሰደቡ ወይም ሲሙቱ የሚወጣ ሲሆን፤ ሴቶች አቴቴ ሲወጡ ሲቄና ኤሬሳ ይዘው ሲሆን ፤ ከሙዚቃ መሳሪያዎች የሚጠቀሙት ደግሞ ትንሽ ከበሮ እና ከበላ የመሳሰሉት ናቸው፡፡

**ተግባር 3**

አቴቴ በአካባቢያችሁ ውስጥ በምን አይነት ሁኔታ ይካሄዳል? የሚታውቁ ሰዎችን በመጠየቅ ለክፍል ተማሪዎች አብራሩ፡፡

# ምዕራፍ 4 ማጠቃለያ

- የሀገር በቀል ዕውቀትን ወደ ትያትር ለመቀየር ከትውልድ ወደ ትውልድ ማስተላለፍ ይቻላል፡፡
- የሀገር በቀል እውቀትን በክዋኔ ማሳየት የህብረተሰብ ሰላማዊ ግንኙነትን ለማጠናከር ከፍተኛ ቦታ አለው፡፡
- በሽምግልና የጉማን ስነ ሥርአት መፍታት የኦሮሞ ህብረተሰብ ሀገር በቀል እውቀት ነው፡፡
- የእጅ ስራ በማህበረሰብ ውስጥ የሚገኝ የሀገር በቀል እውቀት ነው፡፡
- የእጅ ስራ የሚሰሩ በተፈጥሮ የሚገኑ ነገሮች በብዛት የሀገር በቀል እውቀት ይጠቀማሉ፡፡
- በሸክላ አፈር ውስጥ የሚገኘው ማዕድን በእሳት ሲቃጠል፤ የመጨማደድ ባህሪ አለው፡፡
- የሽመና ስራ እንዴት እንደሚሰራ እና ለጌጥ የሚሰራበት ነገሮች
- ታሪክን፣እሴትን፣ባህልን፣ማንነትን፣ምንነትን ከሚገልጽበት ውስጥ አንዱ ነው፡፡
- በድሮ ዘመን ወረቀት ሳይሰራ ለፊት ጸሁፍ ለመጻፍና ስዕል ለማንሳት ቆዳን ሲጠቀሙ ነበር፡፡
- በባህላዊ ሙዚቃ ውስጥ የሚጠቀሙት ቃላቶች የተቀናጀበት እና የሚዘፈንበት

  ሁኔታ የማህበረሰቡን ማንነት ብቻ ሳይሆን ስልጣኔን እና የማህበረሰብ ያለውን
- እውቀት የሚያሳይ ነው፡፡
- ባህል የአንድ ማህበረሰብ ማንነት ሲሆን በሁሉም አቅጣጫ መንከባከብ እና በክብር በማስተማር ከትውልድ ወደ ትውልድ መተላለፍ ይችላል፡፡

## የምእራፍ አራት መልመጃ

I. ከዚህ በታች ያሉትን አረፍተ ነገሮች ትክክል ከሆነ "እውነት" ትክክል ካልሆነ ደግሞ "ሐሰት" በማለት በጹሁፍ መልሱ፡፡

1. የሀገር በቀል እውቀት በትያትር ማሳየት የማህበረሰቡን ሰላምን እና ግንኙነትን አያጠናክርም፡፡
2. የማህበረሰቡን ሀገር በቀል እውቀት ወደ ትያትር መቀየር ይቻላል፡፡
3. የእጅ ስራ በማህበረሰቡ ውስጥ የሚገኝ ሆኖ፤ በዘመናዊ ዘዴ የሚሰራ ነው፡፡
4. በሸክላ አፈር ውስጥ የምናገኘው ማእድን በእሳት ሲቃጠል የመሰባበር ባህሪ አለው፡፡
5. የሰው ልጅ ከጥንት ጊዜ ጀምሮ በእጁ ልብስ ሰርቶ እየለነሰ ነበር፡፡
6. የሰው ልጅ በቆዳ ላይ የተለያዩ ዲዛይን በመስራት፤ ቁሳቁሶችን ሲያሳምርበት ነበር፡፡
7. ወረቀት ከመሰራቱ በፊት በቆዳ ላይ ሲጻፍ ነበር፡፡
8. አቴቴ ሁል ጊዜ በሴቶች ብቻ የሚጫወት ጫወታ ነዉ፡፡
9. የኦሮሞ ማህበረሰብ ከጥንት ጊዜ ጀምሮ የረሱን ባህል እና ታሪኩን በሙዚቃ እየገለጸ ቆይቷል፡፡

## II. ከዚህ በታች ያሉትን ጥያቄዎች በደንብ አንብባችሁ ትክክለኛ መልስ የያዘውን መልስ መርጣችሁ በጽሁፍ መልሱ፡፡

1. የኦሮሞ ማህበረሰብ ሀገር በቀል እውቀት የሆነ የቱ ነው?

ሀ. ጅላ ለ. ሽምግልና ሐ. ጋብቻ

መ. ሁሉም መልስ ናቸው፡፡

2. የእጅ ስራ የሚሰሩ ሰዎች በብዛት የሚጠቀሙበት የቱ ነው?

ሀ. ሀገር በቀል እውቀት የሆኑትን ነገሮች ለ. በአካባቢያቸው የሚገኙትን ነገሮች ሐ. ዘመናዊ የሆኑትን ነገሮች መ. ሁሉም መልስ ናቸው፡፡

3. ከዚህ በታች ካሉት ምርጫዎች ውስጥ የእጅ ስራ ውጤት የሆነው የቱ ነው?

ሀ. እሴት ለ. ማንነት ሐ. ታሪክ መ. ሁሉም መልስ ናቸው

4. የእጅ ስራ ሙያ በምን ላይ ተሞርኩዘው ይከፈላሉ?

ሀ. በሚሰሩበት ሙያ ለ. ከሚሰራበት ቁሳቁስ ሐ. በተሰራ አመት/ጊዜ

መ. ሀ እና ለ መልስ ናቸው፡፡

5. ከዚህበታች ከተዘረዘሩት ውስጥ የሰው ልጅ ሲለብስ የነበረው የቱ ነው?

ሀ. ሰፋፊ ቅጠል ለ. የአራዊቶች ቆዳ ሐ. የተሸመነ ልብስ

መ. ሁሉም መልስ ናቸው፡፡

6. የሽመናን ስራ ለማጌጥ የሚሰራበት ያልሆነ የቱ ነው?

ሀ. ታሪክ ለ. ምንነት ሐ. ባህል መ. እምነት

7. የቆዳ ውጤት ያልሆነ የቱ ነው?

ሀ. ትራስ ለ. አንሶላ ሐ. ቀበቶ መ. ሁሉም መልስ ናቸው፡፡

# ምዕራፍ 5

# የስነ-ጥበባት ግንኙነት

**የስነ-ጥበባት ከሌላ ትምህርት ጋር ያለው ግንኙነት**

በዚህ ምዕራፍ መጨረሻ የሚጠበቁ ውጤቶች

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- ስነ-ጥበባት የተፈጥሮ ሀብቷን መጠበቅና መንከባከብ ጋር ያለውን ግንኙነት ትገነዘባላችሁ፡፡
- ስነ-ጥበባትን ከተለያዩ ነገሮች ጋር በማያያዝ መግለጽ ትችላላችሁ፡፡
- ስነ ጥበባት በሌሎች ትምህርት ውስጥ ያለውን ሚና ትገነዘባለችሁ፡፡
- ስነ ጥበባት በመጠቀም ፡- የትራፊክ አደጋን፣ኤች አይ ቪ(HIV)፣አእምሮን የሚያደነዝዙ ነገሮች የሚገልጽ እና የመሳሰሉትን ትገልጻላችሁ፡፡
- ስለ ትራፊክ አደጋ፣ስለ ኤች አይ ቪ(HIV)፣የሰውን አእምሮን የሚያደነዝዙን የሚገልጽ መዝሙር ትዘምራላችሁ፡፡

## መግቢያ

የስነ-ጥበባት ትምህርት በቀጥታ ሆነ በተዘዋዋሪ ሎሎችን ት/ት ለማስተማር የሰው ሚና ከፍተኛ ነው፡፡ ከዚህ ውጭም የስነ ስዕል ሚና የተፈጥሮ እንክብካቤን እና በተለያዩ ነገሮች ላይ ግንዛቤን ለመስጠት ከፍተኛ ቦታ አለው፡፡ በአጭሩ ስነ ጥበባት በማህበረሰቡ አኗኗር ውስጥ

ያለው ፋይዳ ቀላል አይደለም፡፡

## 5.1.ስነ-ጥበባት ከሌላ የትምህርት አይነት ጋር ያለው ትስስር

ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎናጸፉ የሚገባው የመማር ብቃት

ከዚህትምህርት ርዕስ በኋላ ተማሪዎች፡-

- ስነ ጥበባት በሌላ ትምህርት በመማር ውስጥ ያለውን ፋይዳ ትገነዘባላችሁ ፡፡
- ስነ ጥበባት የተፈጥሮ ሀብት በመንከባከብ ውስጥ ያለውን ጠቀሜታ ትናገራላችሁ፡፡
- ስነ ጥበባት ከሌላ ትምህርት ጋር ያለውን ትስስር ትናገራለችሁ፡፡

**ውይይት 1**

❖ ስነ ጥበባት ለሌላ ትምህርት መማር ውስጥ ያለው ፋይዳ ምንድን ነው? ጥንድ ለጥንድ ተወያዩበት እና ለክፍል አቅርቡ፡፡

ሌሎች ትምህርትን ለመማር የስነ ጥበብ ሚና በጣም ብዙ ነው፡፡ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ሎሎችን ትምህርት ለመማር ስነ ጥበብን እንጠቀማለን፡፡ በተለይ የመጀመሪያ ደረጃ እና መካከለኛ ደረጃ ትምህርትን ለማሳካት ስነ-ጥበብ የሚጫወተው ሚና እንዲህ ነው ተብሎ የሚገፅ አይደለም፡፡ ሙሉ በሙሉ ለማለት በሚቻል መልክ ያለ ስነ ጥበብ የአንደኛ ደረጃን እና የመካከለኛ ትምህርትን መማርም ሆነ ማሳካት የማይታሰብ ነው፡፡ ትምህርት ሳይንስ ነው፡፡ ሳይንስ ደግሞ አርት /ጥበብ ነው፡፡

እንጽፋለን የተለያዩ የመስመር አይነቶችን ተጠቅመን የምንጽፈው ጽሁፍ አርት ነው፡፡ እናነባለን፡፡ ድምጻችንን ከፍ አድርገን ዜማ ፈጠረንበት አሳምረን የምናነበው አርት ነው፡፡ የተለያዩ ጭውውቶች ተጠቅመን የሚንማረው ጥበብ ነው፡፡ በአጭር ስነ ጥበብ በሌሎች

ትምህርት ዘርፎች ውስጥ ያለው ህዋሳታችን ነው፡፡ የስሜት ህዋሳት የምንላቸው አምስት ናቸው፡፡ እነሱም፡- በእጅ መንካት፣በአይን ማየት፣በጆሮ መስማት፣ እና በአፍንጫ ማሽተት ነው፡፡ እነዚህም አምስቶች መረጃ ወደ አእምሮአችን እንዲሄዱ በአፈጣጠር ሁኔታዎች እና ጸባያችው ለመለየት የሚያስችሉን ናቸው፡፡ ስለዚህ የስነ ምልከታ እና የስሜት ህዋሳታችን መካከል ያለውን ግንኙነት ስናይ ከዚህ በታች እንደተገጸው ይሆናል፡፡

**ስነ ምልከታ፡**

- የቀለም ቅብ (በዓይን እናያለን)፡፡
- ቅርጻ-ቅረጽ (በዓይን እናያለን፣በእጅ እንዳስሳለን) ፡፡
- ንድፍ (በዓይን እናያለን) ፡፡
- ህትመት (በዓይን እናያለን) እና የመሳሰሉትን ማየት እንችላለን፡፡
- ሙዚቃ በጆሮ እነሰማለን፣በዓይንም እናያለን ፡፡
- በትያትር ጥበብ - በዓይን እናያለን፣በጆሮም እንሰማለን፡፡
- ስነ-ጥበብ (አርት) ከተለያዩ ትምህርት ዘርፎች ጋር ግንኙነት አለው፡፡ ስለ ጤና ጉዳይ ላይ የተዘጋጀ ትያትር ይዘቱ ስለ በሽታ እና መተላለፍ ሁኔታው ሊሆን ይችላል፡፡
- የመማር ማስተማር ዘዴ ላይ የተዘጋጀ ትያትር ደግሞ ስለትምህርት ሊያነሳ ይችላል፡፡ በሁሉም አቅጣጫ ስነ-ጥበብ ከማንኛውም ትምህርት ዘርፍ ጋር ብንኙነት አለው፡፡

(ጊዜው ኮሮና ቫይረስ አለምን በወረረ ወቅት ነው፡፡ ጫላ እና ጫልቱ በጠዋት ስለ ኮሮናው አጨናንቋቸው ይታያሉ፡፡)

**ጫላ ፡** በጠዋት ሚዲያ እያዳመጥሁ ያየሁት ነገር ..... ጆሮዬን ደፍኜ አይኔን መክደን ብቻ ነው የቀረኝ፡፡

**ጫልቱ፡** እኔ ደግሞ የኮረና በሽታ ፍራቻ እና እንግልት በቁሜ ይዞኝ ሊያልፍ ነው፡፡

**ጫላ** ፡ አይ እንግዲህ ጫልቱ፡፡ እነዲሁ ፈርቶ መሰቃየት ሳይሆን የበሽታውን መከላከያ ዘዴዎችን በደንብ ከተጠቀምን እና ህጎቹን ካከበርን ኮሮና እኛንም የመያዝ ደራጃው ትንሽ ነው፡፡

**ጫልቱ፡-** አንተ ተው ደግሞ ትቀልዳለህ? ያደጉ ሀገራት የተለያዩ የመከላከያ ዘዴዎችን የሚጠቀሙ ራሱ እንደ ጎመን በስብሰው እያለቁ እኮ ነው፡፡ሀገራችን ደግሞ እንዴት ትሆናለች ብለህ ታስባለህ ?

(ጫላ እና ጫልቱ እያወሩ ሳለ በአካባቢያችሁ የህክምና ባለሙያ ይመጣል) ፡፡

**ዶክተር** ፡ ከእርስ በእርሳችሁ ተራርቃችሁ ተቀመጡ፡፡

**ጫላ**፡ እሺ

**ጫልቱ** ፡ እንዲህ ቤተሰብን የሚያራርቅ በሽታ የጥላቻ በሽታ ቢባል ይቀላል፡፡

ዶክተር ፡ አይ አስተውሉ፡- ይህ በሽታ በንክኪ እና በትንፋሽ የሚተላለፍ ነው፡፡ ርቀታችን ጠብቀን የዚህን በሽታ ስርጭት አብረን መቀነስ እንድላለን፡፡ ከባድ ሳል እና ትንፋሽ እጥረት ከተሰማችሁ በአካባቢያችሁ የበሚገኝ ጤና ጣቢያ ሄዳችሁ መታየት አለባችሁ፡፡

በአጠቃላይ ከዚህ በላይ ያየነው የአጭር ድራማ ምሳሌ የስነ ተውኔት እና የጤና ትምህርት ግንኙነት እና ትያትር ተጠቅመን እንዴት ማስተማር እንደምንችል ያሳያል፡፡

**ተግባር 1**

1. ስነ-ትያትር እና ስነ ፊልም ከሌላ ትምህርት ጋር ያለውን ትስስር ከጓደኞቻችሁ ጋር ተወያዩ እና ለክፍል ተማሪዎች ንገር?

2. ስነ-ጥበባት ከሌላ ትምህርት ጋር ያለው ትስስር ሚና ምንድን ነው ?

## 5.2 ስነ-ጥበባት የተፈጥሮ ሀብትን በመጠበቅ እና በመንከባከብ ውስጥ ያለው ጠቀሜታ

**ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎናጸፉት የሚገባ የመማር ብቃት**

**ከዚህ ትምህርት ርዕስ በኋላ ተማሪዎች :-**

- ስነ-ጥበባት የተፈጥሮ ሀብትን በመጠበቅ እና በመንከባከብ ውስጥ ያለውን ሚና ትለያላችሁ፡፡
- የተፈጥሮ ሀብትን መጠበቅ እና መንከባከብ የሚገልፅ መዝሙር ትዘምራላችሁ፡፡
- ስነ-ጥበባት የተፈጥሮ ሀብትን መጠበቅና ያላቸው ጠቀሜታ ከፍተኛ ሚና አለው፡፡
- ተፈጥሮን ለማድነቅ፣እየዘመሩ፣በግጥም፣ውበትን እየገለጸ ትኩረት በመስጠት፣ለመግለጽ አርት ከፍተኛ እገዛ ይሰጣል፡፡
- እንዲሁም የተፈጥሮ ሀብት ላይ የጥበብ ስራን በመጨመር ለቱሪዝም መስዕብ እንዲውሉ ለማድረግ ስነ-ጥበብ ከፍተኛ ሚና አለው፡፡

**ተግባር 2**

ሀ. የተፈጥሮ ሀብትን የሚገልጹ መዝሙር በቡድን ሆናችሁ አዘጋጅታችሁ ለክፍል አቅርቡ ፡፡

ለ. የተፈጥሮ ሀብንን የሚያሞግስ ግጥም ፅፋችሁ በማዜም ለክፍል ተማሪዎች አቅርቡ፡፡

### የተፈጥሮ ሀብት

ከስሙ እንደሚንረዳው የተፈጥሮ ሀብት ማለት፡- በተፈጥሮ የሚገኙ በሰው ልጅ የማይሰሩ ናቸው፡፡ በተፈጥሮ የሚገኙ ማንኛውም ነገር ሁሉ የተረጥሮ ሀብት ተብሎ ይታወቃል፡፡ ለምሳሌ፡- አራዊት፣አእዋፋት፣ማዕድኖች፣ውሃ፣መሬት፣ብርሃን፣አፈር፣አየር፣የተፈጥሮ

ሀይል እና የመሳሰሉት ሁሉ የተፈጥሮ ሀብት ይባላሉ፡፡

## የተፈጥሮ ሀብትን መጠበቅና መንከባከብ

**ተግባር 3**

የተፈጥሮ ሀብትን መጠበቅ ማለት፡- የተፈጥሮ ሀብትን ለአሁኑም ሆነ መጪው ትውልድ ተንከባክቦ ማቆየት ማለት ነው፡፡ የሰው ልጅ አኗኗር ሙሉ በሙሉ በተፈጥሮ ሀብት ላይ የተመሰተረተ ነው፡፡ የተረጥሮ ሀብት ባይኖር ኖሮ የሰው ልጅ መኖር አይችልም፡፡ ምክንያቱም ከተፈጥሮ ሀብት ውስጥ የማይታደሱ ስላሉ ነው፡፡ የሚንመገበው ምግብ፣ውሃ፣አየር እና የሚንኖርበት ቦታ ሁሉ ከተፈጥሮ ሀብት የተገኙ ናቸው፡፡ ከሰው ልጅ ስራ ውስጥ በብዛት የማይታደሱ ነገሮች አጠቃቀም እንደ ጭስ፣ ከፋብሪካዎች የሚወጡ ጭስ እና የመሳሰሉትን ወደ ሰማይ በመልቀቅ የአካባቢውን አየር እንዲበከል ያደርጋል፡፡

ለዚህም የምንኖርበት ምድር ጥሩ አየር ንብረት እንዲኖረው እና የሰው ልጂ ጤናማ እንዲሆን የተፈጥሮ ሀብትን መንከባከብ ለሁሉም ትውልድ አስፈላጊ ነው፡፡

**ተግባር 4**

1. የስነ-ስዕል ስራ ተግባር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በአኗኗራቸው ውስጥ ያለው ሚና ምንድን ነው?
2. የተፈጥሮን ሀብት መጠበቅ እን መንከባከብ ውስጥ ስነ ስዕል ያለው ደረጃ ምንድን ነው?
3. ስነ-ስዕል የተፈጥሮ ሀብት መጠበቅ እና መንከባከብ ውስጥ እንዴት ከፍተኛ ሚና ሊጫወት ይችላል በቡድን በቡድን ተወየዩ እና ለክፍል አቅርቡ?

የእኛ አኗኗር በሁሉም ጊዜ በአርት (በስነ-ጥበብ) የታገዘ እና በእኛ ኑሮ መሠረትም በስነ ጥበብ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ነገር ግን ብዙ ሠዎች

ስነ-ጥበብ በአኗኗራቸው ውስጥ የሚጫወተው ሚና እና አኗኗራቸውም በስነ-ጥበብ ላይ የተመረኮዘ መሆኑን አይረዱም፡፡ በእለት ከእለት አኗኗራችን ውስጥ ስነ ስዕል ያለው ፋይዳ ከሙዚቃ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ስነ ስዕል ኑሮአችን እያስደሰተ፣እያዝናና እና የተረጋጋ እንዲሆን ያደርጋል፡፡ ከባድ የሆነ ችግር ሲያጋጥመን ወይም የድካም ስሜት ሲሰማን ሙዚቃ ካዳመጥን እየተነቃቃን ወደ ትክክለኛው መስመር ይመልሰናል፡፡ እንዲሁም ስነ ስዕልም ያነቃቃናል፡፡

አስተውለንም ሆነ ሳናስተውል የስነ-ስዕል ስራዎች በእለት ከእለት የህይወታችን ተግባር ውስጥ ለሚገኘውም ሁኔታ ተጽእኖ አለው፡፡ የሚያደርገው ተፅእኖ ደግሞ ለመልካም ሆነ ለክፋት ሊሆን ይችላል፡፡ አንዳንድ የስነ-ስዕል ስራዎች የሰዎችን ስሜት የሚረብሹ፣የሚያናድዱ እና ጭንቀት ውስጥ የሚያስገቡ አሉ፡፡ ስለዚህ ጥሩ ስሜት እንዲሰጠን በአካባቢያችን ሆነ በቤታችን ምን አይነት የስነ ስዕል ስራ ያለ መሆኑን ማወቅ አለብን፡፡ ጥሩ የሆነ ስሜት የሚፈጥርልን የስነ-ስዕል ስራዎች እንድንደሰት፣ እንድንረጋጋ፣ጥሩ ሀሳብ እንድናስብ፣እንድንሰራ እና ለመስራት ተነሳሽነት እንዲኖረን ያደርጋል፡፡

የትም ቦታ ቢንሄድ ስነ-ጥበብ አለ፡፡ በተለያዩ ፓርኮች ውስጥ የቅርጻ ቅርጽ ስራን በመጠቀም ፍላጎትን መጨመር እና ለሰዎች መረጃ ማስተላለፍ ይቻላል፡፡ በመንገድ ዳር ወይም በግድግዳ ላይ የተሰሩ የፖስተር ስራዎች መልእክትን ለማስተላለፍ እና ሠዎች ውስጥ መነቃቃትን ይፈጥራል፡፡ በሬድዮ የሚጫወተው ሙዚቃ ሞራል ይሰጠናል፡፡ በአጠቃላይ ሳናውቅ፣ብዙው ጊዜ በጥበብ ውቅያኖስ ውስጥ ተከበን እራሳችንን እናገኛለን፡፡

ስነ-ስዕል የአካባቢ ጥበቃ እና እንክብካቤ ውስጥ ከፍተኛ ሚና አለው፡፡ የስነ- ስዕል ስራ የሚሰራበት ርእሶች ብዙ ናቸው፡፡ እነርሱም፡-

- የመሬትአቀማመጥ(እንጨቶች፣ተራራዎች፣ሸለቆዎች፣አእዋፍት፣አራ

ዊቶች፣መንገድ እና የመሳሰሉትን በውስጡ ይይዛል፡፡)

- የከተማ አቀማመጥ (ህንጻዎች፣መንገድ፣መኪና፣ገብር፣እንጨት እና የመሳሰሉት)
- የባህር አቀማመጥ (ባህር፣በርከብ፣አሳዎች እና የመሳሰሉት)
- የሠማይ አቀማመጥ ሁኔታ (ደመና፣ጸሀይ፣ጨረቃ እና የመሳሰሉን በውስጡ ይይዛል) እና የመሳሰሉት ላይ በመመስረት የሰራል፡፡ በዚህ ምክንያት የቀለም ቅብ ስራ የሚሰሩት አርቲስቶች እንደ እነጨት፣ተራራዎች፣ሀየቅ፣ደመና፣ሸለቆ እና የመሳሰሉት የራሳቸው ርዕስ አድርገው በቀለም ቅብ ንድፍ እና የመሳሰሉት ነገሮች ትኩረት እንዲያደርጉ አድርጓል፡፡ በተጠቀሱት ርዕሶች ላይ መስራት ከጀመሩ፤

በ19 ኛክፍለ ዘመን አካባቢ ለህዝብ ከጀመሩ ወዲህ የእነርሱ ስራ ሰዎች ለተፈጥሮ ያላቸውን አመለካከት እንዲቀይሩ አድርጓል፡፡ በተለያዩ ሀገሮች ውስጥ ከእነዚህ ሰዎች ስራ በኋላ ማራኪ ቦታዎች አስፈላጊነት እና ውበት ለብዛት ዕውቀት እያገኙ መጡ፡፡ ዛሬም የስነ-ስዕል ስራ በተፈጥሮ ሀብት እና እንክብካቤ ውስጥ ይህ ነው የማይባል ድርሻ አለው፡፡



ስዕል 1 የአካባቢን ጽዳት የሚያሳይ የቀለም ቅብ ስራ ስዕል

**የዱር አራዊት እና አእዋፋትን መጠበቅ**

የዱር አራዊት እና አእዋፋት ጥበቃ ያስፈለገበት ዋና ምክንያት የዱር እንስሳት እንዳይሰደዱ ለመጠበቅ ነው፡፡እንዲሁም እንዲራቡ ይረዳል፡፡ የዱር አራዊቶች እና የአእዋፋት ዓይነቶች በብዛት ከአለም ላይ እየጠፉ ስላሉ በህይወት ኖረው ተራብተው ለትውልድ እንዲተላለፉ ጥበቃ እና እንክብካቤ ሊደረግላቸው ይገባል፡፡ በተለይም በሌላ አካባቢ (ሀገር) የማይገኙ አእዋፋትን የተለያየ ትኩረት ሊደረግላቸው ይገባል፡፡ ለምሳሌ፡- ቀይ ቀበሮ፣ኒያላ፣ዋሊያ አየቤክስ፣ጭላዳ ዝንጀሮ እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡



ስዕል 2 የቀይ ቀበል ምስል የሚያሳይ ስዕል

**ልምምድ አንድ**

ከዚህ በላይ የተሰጠው የቀይ ቀበሮ የሚያሳየውን ስዕል በፈለከው ነገር ሠርታችሁ አሳዩ፡፡

**የመሬት አጠባበቅ እና እንክብካቤ**

የአካባቢ አየር ሁኔታ መቀያየር ጋር ተያይዞ ወደ ፊት ፕላቶ

ለመሬታችን በጣም አሳሳቢ ነው፡፡ ይህቺን ምድር ለመጪው ትውልድ ለማቆየት፣የሰው ልጅ የመሬት እንክብካቤ ላይ ሊያመጡ የሚችሉ ችግሮች ለማስቀረት መስራት አለበት፡፡



ስዕል 3 በቀለም ቅብ ስራ የመሬትን አቀማመጥ የሚያሳይ ስዕል

### የሰውን ልጅ ጤንነት መጠበቅ


የተፈጥሮን ሀብት መጠበቅና መንከባከብ ያስፈለገበት ምክንያት የሰው ልጅ ጤንነት መዛባት ላይ ትልቅ ተፅእኖ ስላለው ነው፡፡ የዱር አራዊቶችን ለብቻ እንዲኖሩ ለይቶ መጠበቅ ከዱር አራዊቶች ወደ ሰው በሽታ እንዳይተላለፍ ያደርጋል/ያግዛል፡፡ ይህ ካልተደረገ ግን የዱር አራዊት እና የቤት እንሰሳት በአንድ ላይ የሚውሉበትን እድል ይከፍታል ማለት ነው፡፡ ይህ ማለት ደግሞ ከዱር አራዊት ወደ የቤት እንሰሳት ከቤት እንሰሳት ወደ ሰው ተላላፊ የሆኑ በሽታዎች እንዳይተላለፉ መንገድ ይረጥራል፡፡ በዚህ ዓይነት ሁኔታ ለአእዋፍ፣ለአራዊት እና ለቤት እንሰሳት የተለያየ እንክብካቤ የማናደርግ ከሆነ፣ የሰው ጤንነት ሊዛባ ይችላል ማለት ነው፡፡

እንዲሁም የሰው ልጅ ከእንሰሳት እና ከተለያዩ እጽዋት ላይ መድሃኒት እያዘጋጀ መጠቀም ሊከብደው ይችላል ማለት ነው፡፡



ስዕል 4 የአካባቢ ብክለት የሰው ልጅ ጤና እንዴት ሊጎዳ እንደሚችል የሚያሳይ ስዕል

**የአካባቢ ብክለት በጣም እየከፋ ከሄደ የሰው ልጅ ጤና ላይ ትልቅ እደጋ ሊያስከትል ይችላል፡፡ በአጠቃላይ የአካባቢን የአየር ብክለት እና የተፈጥሮ ሀብትን መንከባከብ ማለት የወደፊታችንን /ነጋችንን/ መንከባከብ ማለት ነው፡፡**



ስዕል 5 የአካባቢን ብክለት የሚያሳይ ስዕል

**ልምምድ 2**

ከዚህ በላይ የተሰጠውን የአካባቢን ብክለት የሚያሳየውን ስዕል በደብተር ላይ አንስታችሁ አሳዩ ፡፡

## 5. 3. ስነ - ጥበብ ከተለያዩ ነገሮች ጋር ያለው ትስስር

በዚህ ርዕስ መጨረሻ ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎናጸፉት የሚገባቸው የመማር ብቃት

**ተግባር 5**

የመዝሙሩ ይዘት ስለ

- ስነ-ጾታ
- ስለ - ትራፊክ
- ስለ - HIV
- ስለ ኮረና ወይም ስለጤና የሆነውን አንዱን በመምረጥ በግሩፕ በግሩፕ አዘጋጅና፤ ተራ በተራ ለክፍል ተማሪዎች አቅርቡ፡፡

ስነ-ጥበብ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ትልቅ ትስስርት አለው፡፡ በይበልጥ በ "HIV" ፣በትራፊክ አደጋ ፣በተለየዩ ተላላፊ በሽታዎች፣የሴቶች እና የወንዶች እኩልነት እና የሀገር ሰላም እና የመሳሰሉት በመዝሙረ፣በተግባር እና በምስል መግለጽ ይቻላል፡፡ ይህም እነዚህ ነገሮች በማህበረሰቡ ውስጥ የሚያደርሱትን ችግር መፍትሄአቸውን ለመዘመር በሰፊው ማህበረሰቡን ለመድረክ ስነ-ጥበብ ትልቅ ቦታ አለው፡፡ ለምሳሌ፡-የትራፊክ አደጋ እና በተላላፊ በሽታዎች ላይ ማህበረሰቡ ግንዛቤ አግኝቶ እራሱን እንዲጠብቅ በማድረግ ረገድ በሚዲያ መዝሙርን በማቀናጀት ማህበረሰቡን በማስተማር ውስጥ ትልቅ ሚና አለው፡፡ ከዚህም ሌላ የጾታ እኩልነት በመዝሙር፣በስዕላዊ እና በተግባር ማሳየት ይቻላል፡፡

## 5.3.1 ስነ-ስዕል ከተለያዩ ነገሮች ጋር መተሳሰር

ስነ-ስዕል በትያትር እና በፊልም ተላላፊ በሽታ እነደ "HIV" ኤድስ ፣ ኮቪድ -19፣ የወባ ትንኝ ወረርሺኝ፣የትራፊክ አደጋ እና የመሳሰሉት ላይ ትምህርት በመስጠት እና በማስተማር ከበሽታው ሊጠነቀቁ የሚገባቸው ግንዛቤ ከሚሰጥበት መንገድ አንዱ ነው፡፡

በመዝናኛ ዝግጅቶች ውስጥ በሀገር ደረጃ ያሉትን የተለያዩ ኮንፈረስ፣የመንግስት እና የመንግስት ያልሆኑ አጀንዳ ውስጥ በአጭር ትያትር እና በፊልም ማቅረብ ይቻላል፡፡ በቴሌቪዥን የሚተላለፍ ማስታወቂያ እና የመሳሰሉት ነገሮች ውስጥ ትያትር እና ፊልም ይገኛሉ፡፡

## የምዕራፍ ማጠቀለያ

- ስነ -ጥበባት በሌላ ትምህርት አይነት ውስጥ ያለው ድርሻ ብዙ ነው፡፡
- የተለያዩ መስመሮችን ተጠቅመን የምንጽፈው ጹሁፍ ስነ-ጥበባት ነው፡፡
- የተፈጥሮን ሀብት መጠቀም ማለት ለአሁኑም ለሚቀጥለው ትውልድ ተንከባክቦ ጠብቆ ማሳለፍ ማለት ነው፡፡
- የትም ስንሄድ ስነ-ጥበብ አለ፡፡
- የተፈጥሮ ሀብት ባይኖር የሰው ልጅ መኖር አይችልም፡፡
- ስነ-ስዕሎች በአካባቢ ጥበቃ እና እንክብካቤ ውስጥ ከፍተኛ ሚና ይጫወታል፡፡

## የምእራፍ 5 መልመጃ

**ከዚህ በታች ያሉትን አረፍተ ነገሮች በማንበብ ትክክል ከሆኑ እውነት ትክክል ካልሆነ ደግሞ ሀሰት በማለት በጽሁፍ መልሱ፡፡**

1. ስነ-ጥበብ በሌሎች ትምህርት ውስጥ ያለው ድርሻ ብዙ ነው፡፡
2. የሌላ አይነት ትምህርት ለመማር ስነ-ስዕል አይጠቅምም፡፡
3. የተለያዩ መስመሮችን ተጠቅመን የምንጽፈው ጽሁፍ ጥበብ ነው፡፡
4. የቀለም ቅብ ሥራን በእጅ እንዳስሳለን፡፡
5. በስነ-ጥበብ መጠቀም የተማሪዎችን በራስ መተማመንን ያዳብራል፡፡
6. የኛ ኑሮ ሁልግዜ በጥበብ የተሞላ ነው፡፡
7. በስነ-ስዕል እና በስሜት ህዋሳት መካከል ግንኙነት የለም፡፡
8. የስነ-ትያትር ስራን በዓይናችን እናያልን፣በጆሮአችን እነሰማለን፡፡
9. የተፈጥሮ ሀብት በሰው እጅ የተሠራ ነው፡፡
10. የተፈጥሮ ሀብት ባይኖር ኖሮ የሰው ልጅ ሊኖር አይችልም
11. በእለት እለት አኗኗር ውስጥ ያለው የስነ-ስዕል ጥቅም ሙዚቃ ካለው ጥቅም ጋር ከፍተኛ ተመሳሳይነት አለው፡፡
12. የሁል ግዜ የእኛ ኑሮ በስነ-ጥበብ የተሞላና ኑሮአችንም በጥበብ ላይ የተመሠረተ ነው፡፡
13. የስነ-ስዕል ስራዎች በሁሉም ጊዜ ጥሩ ስሜት ይፈጥርብናል፡፡
14. ስነ-ስዕሎች ለአካባቢ ጥበቃ እና እንክብካቤ ውስጥ ከፍተኛ ድርሻ አላቸው፡፡